# አማርኛ

# እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## 5ኛ ክፍል


### አዘጋጆች

ትንሳኤ ጀምበሬ

ንጉሴ ዴአታ

### አርታኢ

ግርማ በቀለ

### የጥራት ተቆጣጣሪዎች

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

### ግራፊክስ

ሰለሞን አለማየሁ ጉተማ

© የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ 2014 ዓ.ም.

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም. በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የቅጂ መብቶችን ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማውጫ


| | | |
|---|---|---|
| መግቢያ | ........................................................................ | iv |
| ምዕራፍ አንድ | ........................................................................ | 1 |
| ጓደኝነት | ........................................................................ | 1 |
| ምዕራፍ ሁለት | ........................................................................ | 10 |
| ንፅህናና ፅዱነት | ........................................................................ | 10 |
| ምዕራፍ ሶስት | ........................................................................ | 18 |
| ትውፊት | ........................................................................ | 18 |
| ምዕራፍ አራት | ........................................................................ | 27 |
| የመንገድ ደህንነት | ........................................................................ | 27 |
| ምዕራፍ አምስት | ........................................................................ | 37 |
| አካባቢ ጥበቃ | ........................................................................ | 37 |
| ምዕራፍ ስድስት | ........................................................................ | 46 |
| አደንዛዥ ንጥረነገሮች | ........................................................................ | 46 |
| ምዕራፍ ሰባት | ........................................................................ | 54 |
| ምግብ | ........................................................................ | 54 |
| ምዕራፍ ስምንት | ........................................................................ | 62 |
| የዱር እንስሳት | ........................................................................ | 62 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ፡ | ........................................................................ | 70 |
| ባህላዊ ጨዋታዎች | ........................................................................ | 70 |
| ምዕራፍ አስር | ........................................................................ | 79 |
| መርሃ ትምህርት | ........................................................................ | 88 |

## መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያ የተዘጋጀው በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች ማስተማሪያ የተዘጋጀውን የተማሪ መፅሐፍ መሠረት በማድረግ ነው። በመሆኑም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች እንዴት ማስተማርና ተግባራቱን እና መልመጃዎቹን እንዴት ማሠራት እንደሚገባ ሁሉአቀፍ የሆነ ጥቆማ ለመምህር ያቀርባል። ከዚህም ሌላ የክፍል አደረጃጀትና አስተዳደሩ ምን መሆን እንደሚገባው አቅጣጫ ያስቀምጣል። በዚህም መምህራን የየክፍላቸውንና የየተማሪዎቻቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት መምሪያውን ተግባራዊ ያደርጉታል ተብሎ ይጠበቃል።

## የመምሪያው አደረጃጀትና ይዘት

ይህ የመምህር መምሪያ ከላይ እንደተገለፀው የተማሪ መጽሐፍን በመንተራስ የተዘጋጀ በመሆኑ የይዘት አደረጃጀቱም ይህንኑ የተከተለ ነው። ስለሆነም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተቀመጡት ምዕራፎች በቅደም ተከተል ቀርበውበታል። በየምዕራፉ ለሚከናወኑ የማዳመጥ ተግባራት የተዘጋጁት ምንባቦችም በመምህር መምሪያው ተካተዋል። አስፈላጊ ይሆናሉ ተብለው በታሰቡ ይዘቶች ላይም ተጨማሪ ማስታወሻዎች የተሰጡ ሲሆን፣ በየደረጃው ለቀረቡ መልመጃዎችም ናሙና መልሶች እንዲካተቱ ሆኗል። እነዚህ ናሙና መልሶች የቀረቡትም በቋንቋ ትምህርቱ አሰጣጥ ወቅት ወጥነት ያለው አካሄድ እንዲኖር ታስቦ ሲሆን፣ መምህርና ተማሪዎቹ እንደየሁኔታው (አውዱ) የሚያቀርቧቸው ተጨማሪ ምላሾችም ከግምት የሚገቡ ናቸው።

## ልዩ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች

- የየትኛውም ክፍል ጊዜ ትምህርት ሲቀርብ አራቱን የቋንቋ መሠረታዊ ክሂሎች በተመጣጠነና በተቀናጀ መልኩ ያካተተ ሊሆን ይገባል፤
- የትምህርቱ አቀራረብ አሳታፊ፣ ትብብራዊ እና ተግባቦታዊ የማስተማር ዘዴ መርህን የተከተለ ሊሆን ይገባል (ለምሳሌ ተማሪን ማዕከል ያደረገ መሆን)፤
- የልሥራ፣ እንሥራ፣ ሥሩ አካሄድ ሁልጊዜም ይተግበር፤ በተለይ አዲስ ርዕሰ ጉዳይ እና መልመጃ ሲቀርብ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፤
- ሁሉም ተማሪዎች ከተመሳሳይ ዳራ ያልመጡ ወይም ተመሳሳይ ልምድ የሌላቸው ስለሚሆን በመማር ወቅት የሚቸገሩ ተማሪዎችን ቀስ በቀስ የማብቃት ስልትን (scaf-folding) በመተግበር ማገዝ ያስፈልጋል፤
- ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ተማሪዎችና ላቅ ያለ አፈፃፀም የሚያሳዩ ተማሪዎች ሲያጋጥሙንም ችሎታዎቻቸውን ለማዝለቅ ማበረታትና ተጨማሪ ተግባራትን እያዘጋጀን በመምጣት ማትጋት ይገባል፤
- በክፍል ተሳትፎ ወቅት ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድን መከተል ይገባል (የባህል፣ የሀይማኖት፣ የፆታ ወዘተ አካታችነትን ከግምት ማስገባት)
- ተማሪዎቹ በሚማሩበት አካባቢ በሌላ መልኩ የሚተረጎም ቃል ወይም አገላለፅ ወይም ምስል ሲያጋጥም (ታቡ የሆነ) በሌላ መተካት/ማለዘብ
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የአካቶ ትምህርትን መርህ በመከተል ተገቢ እገዛ ሊያደርጉላቸው ይገባል።

# ምዕራፍ አንድ

## ጓደኝነት (የክፍል ጊዜ ብዛት 18)

### የሚጠበቁ ውጤቶች

### 1. ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የቀረበላቸውን ጽሁፍ በማንበብ ዋናውን ሐሳብ ይገልፃሉ፤
- ስለጓደኞቻቸውና ስላሳለፉት ጊዜ ቀለል ያሉ ዓረፍተነገሮችን በመጠቀም አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- ያነበቡትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ተዛማጅ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍችዎችን ይናገራሉ፤
- የወልና የተፀውዖ ስሞችን ይለያሉ።

### 2. የትምህርት ይዘቶች

#### 2.1 ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች፣
- አዶዬ በሚል ርዕስ ስለጓደኝነት የቀረበ ምንባብ፣
- የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች፣

#### 2.2 ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- ተማሪዎች የእረፍት ጊዜያቸውን እንዴት እንደሚያሳልፉ መናገር፣
- ተማሪዎች ጓደኞቻቸውን እንዴት እንደሚመክሩ መናገር፣
- የሰዎችን የትርፍ ጊዜ አጠቃቀም ጠይቆ መናገር፣
- ጥንድ ጥንድ እየሆኑ የእርስ በርስ ትውውቅ ማድረግ፣
- የሰላምታን አጠቃቀም ከጊዜ አንፃር መናገር፣

#### 2. 3 ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

- የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ፣
- &ጓደኝነት& በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ፣
- የቃል ምላሽ የሚፈልጉ የምንባብ ጥያቄዎች ፣
- እውነት/ሐሰት በማለት የሚመለሱ ጥያቄዎች፣
- ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች የሚፈለግላቸው ከምንባብ የወጡ ቃላት ፣

## 2.4 ትምህርት አራት፡ መፃፍ

- አንቀጽ መፃፍ ፣
- በአንቀጽ ውስጥ የሚገኙ አረፍተነገሮች፣
- የውሎ ማስታወሻ መፃፍ፣

## 2.5 ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ለቃላት ቀጥተኛ ፍች መፈለግ፣
- የስፖርት ስዕላዊ መግለጫዎችን ከቃላት ጋር ማዛመድ፣

## 2.6. ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

- የወልና የተፀውዖ ስሞችን መለየት፣
- በወልና በተፀውዖ ስሞች ዓረፍተነገር መመስረት፣

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የቀደመ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ማድረግ ፣
- የቅድመማዳመጥ ፣ የማዳመጥ ጊዜና የድህረማዳመጥ ተግባሮችን እንዲፈፅሙ ማበረታታት፣
- ተማሪዎች ከሚደመጥ፣ ከሚነገር፣ ከተፃፈ ነገር ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፣
- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆነው ተግባሮችን እንዲፈፅሙ ማበረታታት፣
- ማህበራዊ አገላለፆችን በተመለከተ መምህራቸውን ተከትለው እንዲሉ / እንዲናገሩ ማድረግ፣
- የቅድመንባብ፣ የንባብ ጊዜና የድህረንባብ ተግባሮችን እንዲፈፅሙ ማድረግ፣
- ተማሪዎች በንባብ ጊዜ ድምፅ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ማድረግ ፣
- የሚቀርበውን ትምህርት ግልፅ ለማድረግ አጫጭር ማስታወሻዎችን መስጠት፣
- የመልመጃ አሰራርን በተመለከተ ምሳሌዎች መስጠት፣
- የክፍልና የቤት ስራዎችን መስጠት፣ የተሰሩትን መከታተልና ግብረመልስ መስጠት፣
- ተማሪዎች ተሳትፏቸውን እንዲያሰፉ ማበረታታትና ገንቢ አስተያየት መስጠት፣

**ክፍለጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**አዶዬ**

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በመፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ የታሰበ ነው። በመሆኑም ጥያቄዎቹን ከመመለሳቸው በፊት አስቀድመው ለአምስት ደቂቃ እርስ በርስ ሆነው እንዲወያዩበት ያድርጉ። ከዚያም ጥያቄዎቹን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። ለሚሰጧቸው መልሶችም ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

&አዶዬ& በሚል ርዕስ ስለጓደኝነት የቀረበውን ምንባብ ከመምህሩ መምሪያ ላይ ያንብቡላቸው። በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች ፅሑፉን እያዳመጡ አዳዲስ ቃላትንና ጓደኛን ለመምረጥ እንደመስፈርት የሚያገለግሉ ምን እንደሆኑ በማስታወሻቸው ላይ እንዲይዙ ያድርጉ። ንባቡንም አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ ገታ እያደረጉ ገለፃ ያድርጉላቸው። የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችንም አንቀፅ ሁለትን አንብበው ከጨረሱ በኋላ ንባብዎን ያቁሙና ይጠይቋቸው፤ ምላሻቸውንም ይቀበሏቸውና አስተያየት ይስጧቸው። ፅሑፉም ቀጥሎ ያለው ነው።

**አዶዬ**

የሰው ልጅ ወደዚህ አለም ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በኑሮና በስራ አጋጣሚ ግንኙነት ያደርጋል። በዚህ ግንኙነት ውስጥ መዋደድ እና መዛመድ እንዳለ ሁሉ መጠላላት እና መራራቅም ሊኖር ይችላል። ሰዎች በፆታ፣ በዕድሜ፣ በትምህርት ደረጃ፣ በአካባቢ፣ በሥራ፣ ወዘተ. ተመሳሳይነት ጓደኞች ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ሁኔታ የሰዎችን የመቀራረብ ደረጃ የተለያየ ሊያደርገው ይችላል። ስለሆነም ከሁሉም ሰው ጋር ጓደኛ መሆን አይቻልም። ሁሉም ሰው ጓደኛውን የሚመርጥበት የራሱ መስፈርት አለው። ከመስፈርቶቹ ውስጥ አንዱ የሰውየው ተግባቢነትና ጥሩ ጠባይ ያለው መሆን ነው።

በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ጓደኝነት ትልቅ አክብሮት የሚሰጠው ነው። በተለይ አዶዬ በኦሮሞ ልጃገረዶች ዘንድ በእውነተኛ ፍቅርና መከባበር ላይ የተመሰረተ ጓደኝነትን የሚያሳዩበት ነው። አዶዬ በዕድሜና በመኖሪያ አካባቢ የሚቀራረቡ ልጃገረዶች በመፈቃቀርና በመደጋገፍ አብሮ ለመኖር ቃለመሃላ የሚፈጽሙበት ሥርዓት አለው። በቅድሚያ ሁለቱ ልጃገረዶች የእጆቻቸውን ትንሽን ጣት በመያያዝ እንዲህ በማለት ይማማላሉ። &አዶዬ& &አዶዬ& "አቤት! ስምሽን ዳግም ብጠራው ስሜን ሞት ይጥራው፤ የኔንም ሞት ይጥራው" ይባባላሉ። ከዚህ ቃለመሃላ በኋላ ሁለቱም ጓደኛማ ች &አዶዬ& ይባባላሉ እንጂ በስማቸው አይጠራሩም።

አዶዬዎች በደስታም ይሁን በሐዘን ጊዜ አይለያዩም። የእረፍት ቀናቸውንም አብረው ያሳልፋሉ፤ በተለያዩ ጉዳዮችም ላይ ውይይት ያደርጋሉ። የጋብቻ ጥያቄ ቢቀርብላቸው በጠያቂው ማንነት

ላይ በቅድሚያ ጥናት በማድረግ ይወያያሉ። ውይይታቸውም፣ በባህሪው፣ በስራው፣ በሀብቱ ላይ ያተኮረ ነው። በዚህ መሰረት የእጮኛ መስፈርት ማሟላቱን ወይም አለማሟላቱን ያረጋግጣሉ። በተጨማሪም በወላጆቻቸው የደስታም ይሁን የችግር ጊዜ ተሳትፎ የሚያደርጉት በጋራ ነው። ይህንንም የሚያደርጉት ያለአንዳች መሰላቸት በመረዳዳት ነው።

(ከአፋን አሮሞ የመማሪያ መጽሐፍ 9ኛ ክፍል ካለው ተተርጉሞና ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተደርጎ የቀረበ)

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ተማሪዎች ስለ&አዶዬ& ቀደም ሲል የተነበበላቸውን ፅሑፍ እያስታወሱ እንዲመልሱ ሁለት ዓይነት  ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል። በዚህም መሰረት ተማሪዎች በቡድን ሆነው እየተወያዩ የጥያቄዎቹን መልሶች በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። ገንቢ አስተያየትም ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ ሶስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር አንድ

በዚህ ስር ሁለት የመናገር ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ቁጥር 1 ጥያቄ ተማሪዎች የግል ተሞክሯቸውን የሚሰጡበት ነው። ስለዚህም ጥያቄውን ለተማሪዎች ያቅርቡና የእያንዳንዳቸውን ሀሳብ በመጠየቅ ያሰሯቸው።

የቁጥር 2 ጥያቄን በቅድሚያ ተማሪዎችን በቡድን ይመድቧቸውና ጊዜ ወስደው እንዲወያዩበት ያድርጉ። ከዚያም ከየቡድናቸው አንድ አንድ ተወካይ ይምረጡና የተወያዩበትንና የተስማሙበትን ሃሳብ እንዲያቀርቡ ይንገሯቸው። እርስዎም አስተያየት ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ አራት**

## ተግባር  ሁለት

ተማሪዎች ሰዎች የትርፍ ጊዜ አጠቃቀማቸውን በሚመለከት ጠይቀው የሚነግሯቸውን ማስታወሻ በመያዝ እንዲናገሩ ታዘዋል። በቅድሚያ የሚጠይቋቸው ሰዎች በጊዜ አጠቃቀማቸው አርአያ ይሆናሉ የተባሉትን እንዲመርጡ ይንገሯቸው። የሚጠይቋቸውንም ጥያቄዎች የትኩረት ነጥቦች አስቀድመው ያስይዟቸው። ጥያቄዎቻቸውንም ተራ በተራ ለተጠያቂው እንዲያቀርቡና ምላሹንም በቅደም ተከተል ማስታወሻ እንዲይዙ ያሳስቧቸው።ከዚያም በማስታወሻቸው ላይ ያሰፈሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ተግባር ሶስት

ተግባሩን በሚመለከት ተማሪዎች የርስ በርስ ትውውቅ በክፍል ውስጥ እንዲያከናውኑ ያድርጉ። የትውውቅ ሂደቱንም ጥንድ ጥንድ እየሆኑ እንዲተገብሩ ይንገሯቸው። ትኩረት የሚያደርጉባቸው ነጥቦችም ለመነሻ እንዲሆኑ በመፅሐፋቸው ላይ ይገኛሉ። እርስዎም የትውውቁን ሂደት እየተከታተሉ አስተያየት ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## ተግባር አራት

ይህን ተግባር በሚከተለው መሰረት ይፈፅሙ። በቅድሚያ ሰላምታ ከጊዜ አንፃር የጧት፣ የረፋድ፣ የቀን፣ የማታ፣ የመሰንበቻ እንደሚባል ይንገሯቸው። የጧት ሰላምታ ተለያይተው ያደሩ ሰዎች የሚያቀርቡት እንደሆነ ይግለፁላቸው። በዚህ ወቅት &እንደምን አደርክ@ ወይም እንደምን አደርሽ@& እንደሚባል ያስረዷቸው። የአክብሮት ሰላምታ ከሆነ &እንደምን አደሩ@&መባሉን ይጠቁሟቸው። ከቁጥርም አንፃር ሰላምታ የሚቀርብላቸው ከአንድ በላይ ከሆኑ &እንደምን አደራችሁ@& እንደሚባል ይንገሯቸው። ሌሎቹንም በተመሳሳይ መንገድ ይግለፁላቸው። የሰላምታ አጠቃቀሙን ተግባር ተማሪዎች እርስዎን ተከትለው እንዲሉ ያድርጉ።

ቀጥሎ የቀረበው ማስታወሻ ሌሎቹን የሰላምታ አጠቃቀሞች ለማለማመድ የሚያግዝ ስለሆነ ይጠቀሙበት።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## ትምህርት ሶስት፡ማንበብ

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

በቅድሚያ የቀደመ እውቀታቸውን ለመቀስቀስ ጥያቄዎቹን እንዲወያዩባቸውና ምላሽ እንዲሰጡባቸው ያድርጉ። እርስዎም የራስዎን ሃሳብ ያክሉበት። የምንባቡን አዳዲስ ቃላትም ይተረጉሙላቸው። ከዚያም ተማሪዎች &ጓደኝነት& በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጉ። አንቀፅ አንድን አንብበው እንደጨረሱ የንባብ ጊዜ ጥያቄውን እንዲመልሱ ይዘዟቸው። በሚያነቡበትም ጊዜ በየአንቀጾቹ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ሃሳቦች ለይተው ማስታወሻ እንዲይዙ ይንገሯቸው። እርስዎም በተራዎ ምንባቡን በማንበብ ሀሳቡን ይግለፁላቸው።

**ክፍለጊዜ ስምንት**

# የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ ሁለት

በዚህ ክፍል ምንባቡን መሰረት ያደረጉ በቃል የሚመለሱ ሰባት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ከነዚህ ውስጥ ከተራቁጥር 5 እስከ 7ያሉት የየአንቀጹን ዋና ሃሳብ የሚጠይቁ ናቸው። ስለሆነም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን ከመስራታቸው በፊት ምንባቡን እንደገና ለአምስት ደቂቃ እንዲያነቡ ይንገሯቸው። ከዚያም ጥያቄዎቹን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ።

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## መልመጃ ሶስት

የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎችን ምንባቡን መሰረት አድርገውና በምክንያት አስደግፈው እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። ምላሻቸውም ትክክል ስለመሆኑ ያረጋግጡላቸው።

# ተግባር አምስት

ተግባሩን በሚመለከት ተማሪዎች በቅድሚያ በቡድን እንዲወያዩበት ያድርጉ። ከዚያም የተስማሙበትን ሀሳብ በተወካያቸው አማካኝነት ተራ በተራ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። እርስዎም የግልዎን አስተያየት ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ አስር**

## መልመጃ አራት

በዚህ ክፍል ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች የሚፈለግላቸው ቃላት በማዛመድ መልክ ቀርበዋል። በፊደል&ሐ&ጥያቄ በምድብ &ሀ& ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸው የሚፈለግላቸው ምንባቡ ውስጥ ባላቸው ፍች ነው። በመሆኑም መልመጃው አገባባዊ ፍች የሚጠይቅ ስለሆነ እግረ መንገድዎን ስለአገባባዊ ፍች ይግለፁላቸው ። ከዚያም የፊደል &ሐ& እና የፊደል &መ&ን የቃላት መልመጃዎች በደብተራቸው ላይ ገልብጠው እንዲሰሩ ያድርጉ፤ ደብተራቸውንም በማረም ግብረ መልስ ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

# ትምህርት አራት፡ መፃፍ

# ተግባር አምስት

በዚህ ክፍል ያለውን ጥያቄ የቤት ስራ በመስጠት ማሰራት የተሻለ ነው። ምክንያቱም ጥያቄው የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል እንዲጠቀሙበት የሚያደርግ በመሆኑ ሰፊ ጊዜ ይፈልጋል ። በቅድሚያ ግን ስለአንቀጽ ምንነት በተማሪው መጽሐፍ ላይ በማስታወሻ መልክ የቀረበውን ያብራሩላቸው። ከዚያም ተማሪዎች ጽፈው ያመጡትን በትክክል መስራታቸውን ይከታተሉና ናሙና ሥራዎችን መርጠው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፤ አስተያየትም ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ተግባር ስድስት

በቅድሚያ በመፅሐፋቸው ላይ የቀረበውን "በአንቀጽ ውስጥ የሚገኙ ዓረፍተነገሮች" የሚለውን ማስታወሻ ይግለጹላቸው። ከዚያም ጥያቄውን በትዕዛዙ መሰረት እቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ይዘዟቸው። ተማሪዎች ፅፈው ያመጡትን በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ሀይለቃልና ዘርዛሪ ዓረፍተነገሮችን መለየታቸውን ያረጋግጡ። ስለስራቸውም ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

በዚህ ስር የውሎ ማስታወሻን የሚመለከት በአንድ አንቀፅ የተዋቀረ ናሙና ፅሁፍ ቀርቧል። ፅሁፉ ቀጣዩን ተግባር እንዲሰሩ ለማድረግ የሚያስችላቸው ስለሆነ በክፍለ ጊዜው ልምምድ እንዲያደርጉ ያመቻቹላቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ተግባር ሰባት

በዚህ ሥር ያለውን ጥያቄ ለመስራት በቂ ጊዜ የሚፈልግ ስለሆነ አስቀድመው የቤት ስራ ይስጧቸው። ፅሁፉም በአንድ ሳምንት ውስጥ ያከናወኗቸውን የየዕለት የተለያዩ ተግባራት የሚገልፅ &የውሎ ማስታወሻ& በሚል ርዕስ የሚፃፍ እንደሆነ ይንገሯቸው። ከዚያም ተማሪዎች የቤት ስራውን ሰርተው መምጣታቸውን ያረጋግጡ። ናሙና ሥራዎችንም በመምረጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ማስተካከያ ለሚፈልጉ ስራዎችም ተገቢውን እርማት ይስጡና ትምህርቱን ያጠቃልሉ

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## ተግባር ስምንት

በዚህ ስር ለቀረቡት ቃላት ተማሪዎች መዝገበቃላት ተጠቅመው ቀጥተኛ ፍቻቸውን እንዲፈልጉ ያድርጉ። በቅድሚያ ግን ስለመዝገበቃላት አጠቃቀምና የቃላት ቀጥተኛ ፍች ምንነት ይግለፁላቸው። ከዚያም ጥያቄዎቹን ሰርተው እንዲመጡ ይዘዟቸው። ሰርተው ያመጡትንም ተመልክተው ደብተራቸውን በማረም ግብረ መልስ ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

### መልመጃ አምስት

ይህ መልመጃ ተማሪዎች የስፖርት ስዕላዊ መግለጫዎችን ምንነት ከቃላት ጋር እንዲያዛምዱ የታዘዙበት ነው። በዚህ መሰረት በመፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ስዕላዊ መግለጫዎችንና ቃላቱን በደብተራቸው ላይ ከገለበጡ በኋላ በመስመር እያገናኙ እንዲያዛምዱ ይንገሯቸው። በትክክል መስራታቸውንም አረጋግጠው አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

## ክፍል ስድስት፡ ሰዋስው

## ተግባር ዘጠኝ

የወልና የተፀውኦ ስሞችን መለየት በተመለከተ በተማሪው መፅሐፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ ያብራሩላቸው። ሌሎችንም ምሳሌዎች እየሰጧቸው ግንዛቤያቸውን ያስፉላቸው። በተለይ የተፀውኦ ስሞች የተራራ፣ የባህር፣ የውቅያኖስ፣ የመሳሰሉት እንዳሉ በምሳሌ ያሳዩዋቸው። ከዚያም የፊደል "ሀ"ን እና "ለ "ን ጥያቄዎች እቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ያድርጉ። ለአሰራር መነሻ እንዲሆናቸው የተሰጡትን ምሳሌዎች እንዲመለከቱ ይንገሯቸው። ተማሪዎች ሰርተው ያመጡትን የቤት ስራ እርስ በርስ ደብተራቸውን በመቀያየር እንዲተራረሙ ይዘዟቸው። እርስዎም ከተማሪዎች ጋር እየተወያዩ ትክክለኛውን ግብረመልስ ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## ተግባር አስር

በዚህ ሥር ያሉትንም የፊደል "ሐ "ን እና የፊደል "መ" ን ጥያቄዎች በተግባር ዘጠኝ ሥር ባለው የአሰራር መመሪያ መሰረት ያሰሯቸውና አፈፃፀሙን ይከታተሉ።

## መርጃ መሳሪያዎች

- የሰዎችን የትርፍ ጊዜ አጠቃቀም የሚያሳዩ የተለያዩ ስዕላዊ መግለጫዎች፣
- የተለያዩ የስፖርት ስዕላዊ መግለጫዎች፣
- የተለያዩ ማስታወሻዎችን የያዙ የፅሁፍ ቅንጫቢዎች፣

## ግምገማ

- የተነበበላቸውን ፅሁፍ አዳምጠው አድናቆታቸውን መግለፅ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የመናገር ተግባራትን በትክክል መፈፀማቸውን መከታተል ፣
- ያነበቡትን ፅሁፍ መረዳታቸውን ማረጋገጥ ፣
- አንቀጽ መፃፍ መቻላቸውን ማየት ፣
- በአንቀጽ ውስጥ የሚገኙ አረፍተነገሮችን መለየት መቻላቸውን መፈተሽ፣
- የውሎ ማስታወሻ መፃፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣

- የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቾች በትክክል ማዛመዳቸውን ማየት ፣
- የወልና የተፀውኦ ስሞች መለየት መቻላቸውን ማየት ።

# በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## መልመጃ ሶስት

**ለ. እውነት /ሐሰት**

1. እውነት 2. ሐሰት 3. እውነት 4. እውነት 5. ሐሰት 6. ሐሰት

## መልመጃ አራት

**ሐ. ማዛመድ(ተመሳሳይ ፍች)**

**1. ሠ 2. ሸ 3. ሀ 4. ረ 5. ለ 6.መ 7. በ 8. ሰ 9. ቸ 10. ቀ**

**መ. ማዛመድ (ተቃራኒ ፍች)**

| | |
|---|---|
| 1.ሠ | 6. ሀ |
| 2. ቀ | 7. ሐ |
| 3. ተ | 8. ሸ |
| 4. ለ | 9. መ |
| 5. ቸ | 10. ረ |

# ትምህርት አምስት ፡ ቃላት

# ተግባር ስምንት

**መዝገበቃላዊ ፍች**

1. ድንገት፣ በድንገት የሚሆን
2. ሁልጊዜ
3. ምክንያት፣ መነሻ
4. ጠባይ፣ አመል
5. መቀየር፣ በሌላ መተካት

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**መ. የወልና የተፀውኦ ስሞች መለየት**

| | | |
|---|---|---|
| 1. የወል | 5. የተፀውዖ | 9. የተፀውዖ |
| 2. የወል | 6. የተፀውዖ | 10. የወል |
| 3. የወል | 7. የወል | 11. የተፀውዖ |
| 4. የተፀውዖ | 8. የወል | 12. የተፀውዖ |

# ምዕራፍ ሁለት

## ንፅህናና ፅዱነት (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-
- ከምንባቦች የወጡ ጥያቄዎችን አዳምጠው ይመልሳሉ፤
- ፅዳትን በተመለከተ ሰዎች የሚያከናውኑትን ይናገራሉ፤
- በክፍል ደረጃው ትክክለኛውን ንባብ ይለማመዳሉ፤
- ተገቢ ርዕስን በመጠቀም አጭር አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- የይዘትና አዳዲስ ቃላትን ይተዋወቃሉ/ይወያያሉ፤
- የቀለም መዋቅርንና ምዕላድን ይረዳሉ።

## 2. የትምህርት ይዘቶች

### 2.1 ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች ፣
- “የእነአረጋ መማሪያ ክፍል” የሚል ምንባብ
- የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች ፣

### 2.2 ትምህርት ሁለት፡መናገር

- ከምንባብ የተረዱትን መናገር፣
- የቡድን ውይይት በማድረግ የስምምነት ሃሳብ መናገር፣
- ፅዳትን ለመጠበቅ የሚከናወኑ ተግባራትን መናገር ፣
- የንፅህና አጠባበቅን በተመለከተ በምልክት የሚገለፀውን ገምቶ መናገር ፣

### 2.3 ትምህርት ሶስት፡ማንበብ

- የቅድመንባብ ጥያቄዎች፣
- የቀረበውን ምንባብ ማንበብ፣
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች፣
- አቀላጥፎ ማንበብ፣

### 2.4 ትምህርት አራት፡ መፃፍ

- አጭር አንቀጽ መፃፍ፣
- የተጓደሉ ዓረፍተነገሮችን ማሟላት፣

### 2.5 ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መስጠት፣
- የተሰመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት በሌሎች መተካት ፣

### 2.6 ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

- የቀለማት መዋቅሮችንና ምዕላዶችን ማጣመርና መነጠል፣

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የቀደመ እውቀታቸውን መቀስቀስ፣
- ሶስቱን የማዳመጥ ተግባራት እንዲሰሩ ማድረግ፣
- የመናገር ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ፣
- ተማሪዎች ከተለያዩ ምንጮች የሚያገኙትን ሃሳብ በማስታወሻቸው ላይ እንዲመዘግቡ ማድረግ፣
- የግል፣ የጥንድ እና የቡድን ተግባሮችን እንዲሰሩ ማድረግ ፣
- ሶስቱን የማንበብ ተግባሮች እንዲሰሩ ማድረግ ፣
- አንቀፅ እንዲፅፉ ማድረግ ፣
- የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች እንዲሰጡ ማድረግ፣
- አጫጭር ማስታወሻዎችን መስጠት፣
- የቀለማት መዋቅርና ምዕላዶችን እንዲለዩ ማድረግ፣
- የመልመጃዎችን አሰራር በምሳሌዎች አስደግፎ ማቅረብ ፣
- የክፍልና የቤት ስራዎችን መስጠት፣
- ለተግባሮች አስተያየትና ግብረመልስ መስጠት።

**ክፍለጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ ፡ ማዳመጥ

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

በዚህ ክፍል ምስል ተመልክተው የተገነዘቡትን እንዲናገሩና ስለምን እንደሚያዳምጡ አስቀድመው እንዲገምቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በዚህም መሰረት በጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩባቸውና የተስማሙባቸውን መልሶች በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ። እርስዎም የግልዎን አስተያየት በመስጠት ግንዛቤ Wእንዲጨብጡ ያድርጉ ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

በዚህ ሥር ተማሪዎች የሚነበብላቸውን ፅሑፍ እያዳመጡ የሚያሟሏቸው የተጓደሉ አረፍተነገሮች ተሰጥተዋል። በዚህም መሰረት ጥያቄዎቹን አስቀድመው በደብተራቸው ላይ ይገልብጡና በማዳመጥ ሂደት ውስጥ እንዲያሟሉ ያድርጉ። በትክክል መስራታቸውንም ያረጋግጡላቸው።

## የእነአረጋ መማሪያ ክፍል

አረጋ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነው። መማሪያ ክፍሉ ሁልጊዜ ጽዱ ነው። አረጋ እና የክፍል

ጓደኞቹ በየቀኑ ክፍላቸውን ያጸዳሉ። ቆሻሻዎቹን ከወለሉ ያስወግዳሉ። እንዲሁም ጠረጴዛና ወንበሮችን ይወለውላሉ። ቁርጥራጭ ወረቀቶችን በቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ ይጥላሉ። ከዚያም የተሰበሰበውን ቁርጥራጭ ወረቀቶች ከመማሪያ ክፍላቸው አርቀው ጉድጓድ ቆፍረው ይቀብራሉ።

በተጨማሪም አረጋ እና ጓደኞቹ የክፍላቸውን መስኮቶችና ኮርኒስ ያጸዳሉ። ለማጽጃም ቁርጥራጭ ጨርቆችን በውሃ በማራስ መስኮቶቹን ያጸዳሉ። ጣራውን ለማጽዳት የቁም መጥረጊያ ይጠቀማሉ። በዚህም ምክንያት ሁልጊዜ መማሪያ ክፍላቸው ጽዱ ስለሆነ ሁሉም ተማሪዎች ደስተኞችና ጤነኞች ናቸው። መምህራንም እነአረጋ ክፍል ገብቶ ለማስተማር ደስተኞች ናቸው። ተማሪዎቹም በደስታ ትምህርታቸውን ይከታተላሉ፡

### ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

የመልመጃ አንድን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩባቸውና በጋራ የተስማሙባቸውን መልሶች በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የተግባር አንድን ጥያቄም ጥንድ ጥንድ እየሆኑ እንዲወያዩበትና የደረሱበትን ድምዳሜ ለክፍል ተማሪዎች በቃል እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው። እርስዎም የውይይታቸውን ሂደት እየተከታተሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው። በመጨረሻም በቀረቡት ሐሳቦች ላይ ተገቢ የሆነ አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር ሁለት

በዚህ ሥር ተማሪዎች የሚወያዩባቸው ሁለት የመነሻ ሐሳቦች ቀርበዋል። በዚህም መሰረት መነሻ ሐሳቦቹን በቅደም ተከተል እንዲወያዩባቸው ያድርጉ። በሚወያዩበት ጊዜም ሂደቱን ይከታተሉ። በመጨረሻም የውይይታቸውን የተጠቃለለ ሐሳብ እንዲናገሩ እድል ያመቻቹላቸው። እርስዎም የራስዎን ሐሳብ ያክሉበትና ተግባሩን ያጠቃልሉ።

### ክፍለጊዜ አራት

## ተግባር ሦስት

ተማሪዎች ሰዎች ቆሻሻ በሚያስወግዱበት ጊዜ ማድረግ ስለሚገባቸው ነገር የተጠየቁበት ስለሆነ በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጉ። ከዚያም የየቡድኑ አባላት የተስማሙበትን ሃሳብ በተወካያቸው አማካኝነት ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ። እርስዎም በተማሪዎች ሃሳብ ላይ በመመርኮዝ የግልዎን አስተያየት ይስጧቸውና ተግባሩን ያጠቃልሉ።

### ክፍለጊዜ አምስት

## ተግባር አራት

ተማሪዎች ጥያቄውን ሰርተው እንዲመጡ አስቀድመው የቤት ስራ ይስጧቸው። ከዚያም

በክፍለጊዜው ሰዎችን ጠይቀው ያገኙትን ምላሽ በዘገባ መልክ ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ እድል ያመቻቹላቸው፤ ሃሳባቸውንም ተራ በተራ ይቀበሏቸው። እርስዎም ዋና ዋና የተባሉትን ተግባራት ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸውና የጋራ ግንዛቤ ያስጨብጧቸው።

## ክፍለጊዜ ስድስት

## ተግባር አምስት

በዚህ ስር ያለውን ተግባር ለማሰራት በመጀመሪያ የፆታ ስብጥር ያሉባቸውን የጥንድ ቡድኖች ያደራጁ ። ከዚያም በመፅሐፋቸው ላይ ባለው ጥያቄ መሰረት አንዳቸው ያለ ድምፅ በምልክት ብቻ ድርጊቱን እያሳዩ ጥያቄ እንዲጠይቁ ያድርጉ። ሌላኛቸው ደግሞ የምልክት ጥያቄውን ገምተው መልዕክቱን በቃል እንዲናገሩ ያድርጉ። ምላሹም ትክክል ስለመሆኑ ጠያቂዎች እንዲያረጋግጡ ያሳስቧቸው። ሌሎቹም በተመሳሳይ አኳኋን እንዲጠያየቁ ያድርጉ። አንድ ቡድን መጠየቅ የሚችለው አንድ ጥያቄ ብቻ መሆኑንም ያሳስቧቸው።

## ክፍለጊዜ ሰባት

## ትምህርት ሶስት ፡ማንበብ

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

በዚህ ስር ተማሪዎች ዳራዊ እውቀታቸውን በመጠቀም በቡድን ውይይት መልስ የሚሰጡባቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። በዚህም መሰረት በጥያቄዎቹ ላይ ተወያይተው ምላሽ እንዲሰጡ የ5 ደቂቃ ጊዜ ይስጧቸውና ከውይይቱ በኋላ ምላሻቸውን ይቀበሉ። እርስዎም የምላሻቸውን ትክክለኛነት ያረጋግጡላቸው። ተማሪዎች ንባብ ከመጀመራቸው በፊት የምንባቡን አዳዲስ ቃላት ይተርጉሙላቸው። ከዚያም ምንባቡን በየግላቸው ድምፅ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጉ። በሚያነቡበት ጊዜም ፊደላትን ሳይዘሉ፣ ቃላትን ሳይደጋግሙ፣ ፊደላትን ሳይነጣጥሉ ሙሉውን ቃል ለማንበብ እንዲሞክሩ እና ዋና ዋና ሃሳቦችንም በማስታወሻቸው ላይ እንዲመዘግቡ ያሳስቧቸው። ሁለተኛውን አንቀፅ አንብበው እንደጨረሱ ንባባቸውን ገታ እንዲያደርጉና የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጉ። ከዚያም የቀረውን ንባብ እንዲጨርሱ ይንገሯቸው። እርስዎም በተራዎ ምንባቡን እያነበቡ ይግለፁላቸው። ያልገባቸውንም እንዲጠይቁ ያድርጉና ምላሽ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ ስምንት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

በዚህ ስር ሁለት ዓይነት ጥያቄዎች ቀርበዋል። እርስዎም እንደመመሪያዎቹ ቅደም ተከተል በምንባቡ መሰረት ለጥያቄዎቹ ምላሻቸውን በቃል እንዲሰጡ ያድርጉ። የምላሻቸውንም ትክክለኛነት ያረጋግጡላቸው።

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

### መልመጃ ሶስት

በዚህ ስር ሶስት የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበዋል ፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች ቀደም ሲል በተነበበላቸው ምንባብ መሰረት በክፍል ሥራ ምላሽ እንዲሰጡባቸው ያድርጉ። እርስዎም ትክክለኛውን ግብረ መልስ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስር

## ተግባር አምስት

በዚህ ክፍል በቅድሚያ ስለአቀላጥፎ ማንበብ የቀረበውን ማስታወሻ ይግለፁላቸው። ከዚያም ከ3 - 5 የሚሆኑ ተማሪዎችን በቡድን ያደራጁቸውና የምንባቡን አንቀጽ ሁለት ተራ በተራ ድምፅ እያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጉ ፡፡ እርስዎም ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የየቡድኑን ክንውን ምልከታ በማድረግ ድጋፍ ያድርጉላቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ተግባር ስድስት

በዚህ ስር ተማሪዎች የቀረበውን ዕለታዊ ፅሑፍ በትክክል፣ በፍጥነትና በተገቢው ድምፀት እንዲያነቡ ታዘዋል። በዚህም መሰረት ፅሑፉን ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድርጉ። እርስዎም ተማሪዎቸ በትዕዛዙ መሰረት ማንበባቸውን ይከታተሉና ተገቢ የሆነ አስተያየት ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት አራት፡መፃፍ

## ተግባር ሰባት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የሰዎችን የግል ንጽህና አጠባበቅ በተመለከተ በመሪ ሐሳቦች ላይ ተመርኩዘው አጭር አንቀጽ እንዲጽፉ ታዘዋል ፡፡ ስለሆነም በቅድሚያ በምዕራፍ አንድ ስር ስለአንቀጽ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያድርጉ። በመቀጠልም አስቀድመው አንቀጹን እቤታቸው ጽፈው እንዲመጡ ይዘዟቸው። በክፍለጊዜውም ጽፈው ያመጡትን እያንዳንዳቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ። በመጨረሻም ለተማሪዎች ስራ ገንቢ አስተያየት በመስጠት ያጠቃልሉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

### መልመጃ አራት

በዚህ ስር ያለውን መልመጃ በደብተራቸው ላይ በመጻፍ የተጓደሉ ዓረፍተነገሮችን እንዲያሟሉ ያድርጉ። በትክክል መስራታቸውንም ደብተራቸውን በማረም ያረጋግጡላቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት ፡ ቃላት

### መልመጃ አምስት

በፊደል &ሀ& ስር የተሰጠውን መልመጃ የክፍል ስራ በመስጠት ያሰሯቸው። ከዚያም ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ደብተራቸውን እንዲቀያየሩ ካደረጉ በኋላ ከተማሪዎችዎ ጋር እየተወያዩ ትክክለኛ መልስ ሲሰጥ እንዲተራረሙ ያድርጉ።

### ክፍለጊዜ አስራ አምስት

### መልመጃ ስድስት

በፊደል &ለ& ስር የተሰጠውንም መልመጃ በመልመጃ አምስት ስር ባለው የአሰራር መመሪያ በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲሰሩ ያድርጉ። ገንቢ አስተያየትም ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

### መልመጃ ሰባት

በዚህ ስር በዓረፍተነገሮች ውስጥ ደምቀው የተፃፉትን ቃላትና ሀረጋት ከተሰጡት ቃላትና ሀረጋት በመምረጥ ተክተው እንዲያሳዩ የታዘዙበት ነው። ስለሆነም በመመሪያው መሰረት ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ ገልብጠው እንዲሰሩ የክፍል ስራ ይስጧቸው። ሰርተው ከጨረሱ በኋላም ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ደብተራቸውን በመቀያየር የጋራ መልስ ሲሰጥ እንዲተራረሙ ያድርጉ።

### ክፍለጊዜ አስራ አስራ ሰባት

## ትምህርት ስድስት ፡ ሰዋስው

### መልመጃ ስምንት

በቅድሚያ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያለውን ማስታወሻ በሚገባ ይግለጹላቸው። የማስታወሻውም አቀራረብ ተማሪዎች አሁን ላሉበት የክፍል ደረጃ ይመጥናል ተብሎ የታሰበ ነው። ስለሆነም ስለቀለም እና ስለምዕላድ ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ መግባት አይገባዎትም። ከዚህ በኋላ በፊደል &ሀ& ስር ያለውን መልመጃ የክፍል ስራ በመስጠት ያሰሯቸው። በትክክል መስራታቸውንም በማረጋገጥ ግብረ መልስ ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### መልመጃ ዘጠኝ

በፊደል &ለ& ስር ያለውን መልመጃ ከማሰራትዎ በፊት ስለዋና ቃል እና ቅጥያዎች(ምዕላድ) የቀረበውን ማብራሪያ ያስታውሷቸው። ዚያም የክፍል ስራ ይስጧቸው። ሰርተው የጨረሱትን ተማሪዎች ደብተር ያርሙላቸው። እገዛ የሚፈልጉ ተማሪዎችም ካሉ ይደግፏቸው። በመጨረሻም ከተማሪዎች ጋር በመወያየት ትክክለኛውን ግብረመልስ ይስጧቸው።

## መርጃ መሳሪያዎች

- ልዩ ልዩ የግል እና የአካባቢ ንፅህና መጠበቂያ እቃዎች፣
- የግልና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅን የሚያሳዩ ስዕላዊ መግለጫዎችና የተዘጋጁ ጽሁፎች፣

## ግምገማ

በምዕራፉ ስር የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በተጨማሪም በይዘቶቹ ስር የቀረቡትን መልመጃዎች በትክክል መስራታቸውን መገምገም ተገቢ ነው። በዚህም መሰረት ትኩረት ሊያደርጉባቸው የሚገቡ ነጥቦች ፡-

- የቡድን፣ የጥንድና የግል ተግባራትን በትክክል መፈጸም መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የግልና የአካባቢ ንጽህና ለመጠበቅ የሚፈጸሙ ተግባራትን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- አቀላጥፎ ማንበብ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- አጭር አንቀጽ መፃፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የተጓደሉ ዓረፍተነገሮችን ማሟላት መቻላቸውን ማረጋገጥ‹
- የቃላት ዕውቀታቸውን ማስፋት  መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የቀለማት መዋቅሮችን እና ምዕላዶችን ማጣመርና መነጠል መቻላቸውን ማረጋገጥ።

# በናሙናነት የተመረጡ መልሶች

# ትምህርት ሶስት ፡ ማንበብ

# የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ለ. እውነት /ሐሰት**

1. ሐሰት 2. እውነት 3. ሐሰት 4. እውነት 5. ሐሰት

### መልመጃ ሶስት

**ሐ. ምርጫ**

1. መ 2. ሀ 3. መ

# ትምህርት አራት፡ መፃፍ

### መልመጃ አራት

**ለ. የተጓደሉ አረፍተነገሮችን ማሟላት**

1. በተናጠል
2. እንዳይዛመት
5. እንዳይራቡ
6. ማስወገድ

3. መንስኤ
4. በጋራ
7. መተላለፍ

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ አምስት

**ሀ. በተመሳሳይ ፍች ማዛመድ**

1. መ
2. ሰ
3. በ
4. ሀ
5. ለ
6. ቀ
7. ሐ
8. ሠ

## መልመጃ ስድስት

**ለ. በተቃራኒ ፍች ማዛመድ**

1. ሠ 2. መ 3. ሀ 4. ሐ 5. ለ

## መልመጃ ሰባት

ደምቀው የተፃፉትን ቃላትና ሀረጋት በሌሎች ቃላትና ሀረጋት መተካት

1. ንጽህና
2. መፈጸም
3. በመደባለቅ
4. በዘልማድ
5. ችግር

# ትምህርት ስድስት፡ሰዋስው

## መልመጃ ስምንት

**ሀ. ቃላትን በድምፅ (በቀለም) መነጣጠል**

1. ገ - በ - ሬ
2. ተ - ራ - ራ
3. መ - ኪ - ና
4. ዘ - ዴ
5. ባ - ቄ - ላ

**ለ. ቃላትን በምዕላድ መነጣጠል**

1. ገበሬ -ዎች
2. ተራራ -ኣማ
3. መኪና -ኤ
4. ዘመን -ኣዊ

# ምዕራፍ ሶስት

## ትውፊት (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

### 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

### ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ታሪክን አዳምጠው መልሰው ይናገራሉ፤
- በተገቢው ቅላፄ ድምፅን ከፍ አድርገው ያነባሉ፤
- የአንቀጽ አይነቶችን ይለያሉ፤
- ለቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ፤
- ተውሳከግሶችን ከዓረፍተነገሮች ውስጥ ይለያሉ።

### 2. የትምህርት ይዘቶች

#### 2.1 ትምህርት አንድ፡ማዳመጥ

- የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች፣
- የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ፣
- “የባህል ምንነት” በሚል የቀረበ የምልልስ ፅሑፍ፣
- የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች፣

#### 2.2 ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- የቡድን ውይይት ፣
- ምልልስ መተረክ፣
- ስለአንድ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ጠቀሜታ መግለፅ፣

#### 2.3 ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

- የቅድመንባብ ጥያቄዎች፣
- ምንባብ ማንበብ፣
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች፣

#### 2.4 ትምህርት አራት፡ መፃፍ

- የአንቀጽ ዓይነቶችን መለየት፣
- አንቀጽ መፃፍ፣

## 2.5 ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ለቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት፣
- አዳዲስ ቃላትን በዓረፍተነገሮች ውስጥ በማስገባት አገባባዊ ፍቻቸውን መግለፅ፣
- ለቃላት መዝገበቃላዊ ፍች መፈለግ፣

## 2.6 ትምህርት ስድስት፡ሰዋስው

- ተውሳከግሶችን መለየት፣

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የቀደመ ዕውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
- የማዳመጥ ተግባራትን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ፣
- ከሚቀርበው የትምህርት ይዘት ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፣
- የግል፣ የጥንድ እና የቡድን ስራዎችን እንዲሰሩ ማድረግ፣
- የመናገር ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ፣
- የማንበብ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ፣
- የአንቀጽ ዓይነቶችን በመለየት አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ፣
- ለቃላት አገባባዊና መዝገበቃላዊ ፍች እንዲሰጡ ማድረግ፣
- ተውሳከግሶችን እንዲለዩ ማድረግ፣
- አጫጭር ማስታወሻዎችን መስጠት፣
- የመልመጃዎችን አሰራር በምሳሌዎች አስደግፎ ማቅረብ፣
- የክፍልና የቤት ስራዎችን መስጠት፣
- ለተለያዩ ተግባራት ድጋፍ፣ አስተያየትና ግብረመልስ መስጠት።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ
## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ለማሰራት በቅድሚያ አምስት አባላት ያሏቸው ቡድኖች ያደራጁ። ከዚያም የ6 ደቂቃ ጊዜ ይስጧቸውና የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩበት ያድርጉ ። በውይይታቸው ጊዜ በየቡድኑ እየተዘዋወሩ በማየት ድጋፍ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ድጋፍ ይስጧቸው። ከውይይቱ በኋላም ተማሪዎች በጋራ የተስማሙበትን መልስ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። እርስዎም በምላሻቸው ላይ አስተያየት ይስጧቸው።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ

በቅድሚያ ተማሪዎች የሚነበብላቸውን ምልልስ በጥሞና እንዲያዳምጡ ያሳስቧቸው። በማዳመጥ ሂደት ዋና ዋና ሃሳቦችን በማስታወሻቸው ላይ እንዲመዘግቡ ይንገሯቸው። በመቀጠል "የባህል ምንነት" የሚለውን ምልልስ ማንበብ ይጀምሩ። መሐል ላይ ሲደርሱ ንባብዎን ገታ ያድርጉና የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄውን ይጠይቋቸው። ምላሻቸውንም ይቀበሏቸው፤ አስተያየትም ይስጧቸው። ከዚያም ንባብዎን ይቀጥሉና ይጨርሱ። በመጨረሻም ከምልልሱ ያልገባቸው ነገር ካለ ጥያቄ እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው። ተገቢ የሆነ ምላሽም ይስጧቸው።

## የባህል ምንነት

**ኤባ፡-** "ባህል ምንድን ነው ?"

**ሐዋ፡-** "ባህል የአንድ ህብረተሰብ መለያና መገለጫ ባህሪ ሲሆን፣ የሚታየውንና የማይታየውን የህብረተሰብ አሻራ ያጠቃልላል"

**ኤባ፡-** "ባህል የአንድ ህብረተሰብ መለያና መገለጫ ነው ሲባል ምን ማለት ነው ? "

**ሐዋ፡-** "ይህ ማለት ባህል የአንድ ህብረተሰብ የአኗኗር፣ የሃሳብ፣ የእምነት፣ የቋንቋና የልማድ ነፀብራቅ ነው ማለት ነው።"

**ኤባ፡-** "የባህል ምንጬ ምንድን ነው?"

**ሐዋ፡-** "ባህል ምንጬ ህብረተሰቡ ራሱ የፈጠረው ወይም ከሌላው ህብረተሰብ ያገኘው እውቀት ነው። ይህም ማለት ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ ህብረተሰቡ ከቀደሙት እናቶቹና አባቶቹ በሂደት የተማረውና የወረሰው ነው።"

**ኤባ፡-** "ባህል የሚያጠቃልላቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?"

**ሐዋ፡-** "ባህል ብዙ ነገሮችን ያጠቃልላል። ለምሳሌ የአንድን ህብረተሰብ የሠርግና የለቅሶ ክንውን ሥነ-ሥርዓት፣ ምርቃት፣ የበዓላት አከባበር የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።"

**ኤባ፡-** "ባህልን መንከባከብ ያለበት ማን ነው?"

**ሐዋ፡-** "ባህልን መንከባከብ ያለበት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ነው።"

**ኤባ፡-** "ባህልን ለትውልድ ማስተላለፍ የሚቻለው እንዴት ነው ?"

**ሐዋ፡-** "ባህልን ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ በርካታ ዘዴዎች ቢኖሩም ባህልን መዝግቦ ማስተላለፍ አንዱ ዘዴ ነው።"

(ብርሃኑ ገ/ፃዲቅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መመሪያ ከሚለው መጽሐፍ መነሻ ሐሳብ ተወስዶ ተሻሽሎ የቀረበ፣)

## ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምልልስ አዳምጠው ስለመረዳታቸው ለመገምገም የሚያስችሉ አራት ጥያቄዎች ቀርበዋል። በዚህም መሠረት በጥያቄዎቹ ላይ በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጉና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው። እርስዎም የበኩልዎን አስተያየት ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር አንድ

በፊደል “ሀ” የቀረበውን ጥያቄ ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩበት ያድርጉ። ውይይት ሲያደርጉም በክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ ሂደቱን ይከታተላሉ። ከውይይቱ በኋላም ተወያይተው የተስማሙበትን እንዲናገሩ ያድርጉ። እርስዎም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አራት

## ተግባር ሁለት

በፊደል 'ለ' የቀረበውን ጥያቄ ለማሠራት በቅድሚያ የፆታ ስብጥር ያላቸውን የጥንድ ቡድኖች ይመስርቱ። ከዚያም ቀደም ሲል ምልልሱ ሲነበብላቸው በማስታወሻቸው ላይ የያዙትን እያስታወሱ አንዳቸው እንደጠያቂ፣ አንዳቸው ደግሞ እንደመላሽ ሆነው ምልልሱን እንዲተርኩ ያድርጉ። ምናልባት የያዙት ማስታወሻ ለምልልሱ በቂ ካልሆነ የምልልሱን የተወሰነ ክፍል ሠሌዳ ላይ በመጻፍ ተግባሩን እንዲከውኑ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አምስት

## ተግባር ሦስት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስለሚታወቅ አንድ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ምንነት፣ ከምን እንደሚሰራና የመሳሪያውን ጠቀሜታ ጠይቀው እንዲናገሩ የታዘዙበት ነው። በዚህም መሠረት ጠይቀው የተረዱትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

### ቅድመንባብ ጥያቄዎች

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በቀረቡት ቅድመንባብ ጥያቄዎች ላይ በቡድን እንዲወያዩባቸው የተወሰነ ጊዜ ይስጧቸው። በሚወያዩበት ጊዜም በክፍል ውስጥ በመዘዋወር ውይይታቸውን ይከታተሉ፤ ተወያይተው የተስማሙበትንም ምላሽ በቃል እንዲሰጡ ያድርጉ። ተማሪዎች ንባቡን ከመጀመራቸው በፊት በምንባቡ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላትንም ይተረጉሙላቸው። በመቀጠልም ምንባቡን ተገቢነት ባለው ቅላፄ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ እንዲያነቡ ይዘዟቸው። በምንባቡ ውስጥ ያለውን የንባብ ጊዜ ጥያቄም እንዲመልሱ ያድርጉ። እርስዎም በተራዎ ምንባቡን እያነበቡ ይግለፁላቸው። በመጨረሻም ተማሪዎች ባነበቡት ጽሑፍ ላይ የተከሰቱ አደናጋሪ ነገሮች ካሉ ማብራሪያ እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ ሰባት

### የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

በዚህ ስር ቀደም ብለው ያነበቡትን ምንባብ የ5 ደቂቃ ጊዜ ይስጧቸውና እንደገና እንዲያስታውሱ ያድርጉ። ከዚያም በጥያቄዎች ላይ በቡድናቸው እንዲወያዩባቸውና ምላሾቹንም በመጽሐፋቸው ላይ በተጠቀመው መሠረት አሰሳ በማድረግ እንዲመልሱ ያድርጉ። በምላሻቸውም ላይ አስተያየት ይስጧቸው። ይህንንም ተግባር በክፍል ውስጥ ያሰሯቸው።

## ክፍለጊዜ ስምንት

### መልመጃ ሶስት

በ "ለ" ስር ያሉትን የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች በቡድን ውይይት በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። ትክክለኛውንም ግብረመልስ ይስጧቸው። ተግባሩንም በክፍለጊዜው በክፍል ውስጥ ያሰሯቸው።

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

### መልመጃ አራት

በ "ሐ" ስር ያሉትን የማዛመድ ጥያቄዎች ተማሪዎች ደብተራቸው ላይ በመገልበጥ በክፍል ስራ እንዲሰሩ ያድርጉ። ከዚያም ደብተራቸውን እርስ በርስ ከተለዋወጡ በኋላ የጋራ መልስ ሲሰጥ እንዲተራረሙ በማድረግ ክንውኑን ይፈፅሙ።

## ክፍለጊዜ አስር

### መልመጃ አምስት

በ "መ" ስር ያሉትን የምርጫ ጥያቄዎች ከላይ በ "ሐ" ስር ባለው ትዕዛዝ መሠረት በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲፈጸም ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የአንቀጽ ዓይነቶችን እንዲለዩ ለማድረግ የቀረበ ማስታወሻ አለ። በማስታወሻውም መሠረት በእያንዳንዱ የአንቀጽ ዓይነት ላይ በምሳሌ የተደገፈ ገለጻ ያድርጉላቸው። ያልገባቸውንም እንዲጠይቁ ያድርጉና ግብረመልስ ይስጧቸው። በቀጣይ ያለውንም ተግባር የቤት ስራ ሰርተው እንዲመጡ አስቀድመው ያሳስቧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ተግባር አራት

በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች የተሰጣቸውን የቤት ስራ ሰርተው መምጣታቸውን ያረጋግጡ። የተወሰኑ ተማሪዎችንም ስራ መርጠው ያስቀርቡ፤ ከዚያም በቀረቡት አንቀጾች ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጧቸው። በመጨረሻም በተግባር 5 ሥር ያለውን ጥያቄ እቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ይዘዟቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## ተግባር አምስት

በዚህ ሥር ያለውን ጥያቄ ከላይ ባለው ተግባር 4 የአሰራር ትዕዛዝ መሠረት በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲፈጸም ያድርጉ፡፡

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### መልመጃ ስድስት

በዚህሥር ያሉትን ጥያቄዎች የ10 ደቂቃ ጊዜ ይስጧቸውና የክፍል ስራ እንዲሰሩ ያድርጉ። ከዚያም ደብተራቸውን በመሰብሰብ ያርሙላቸውና ትክክለኛውን ግብረ መልስ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ተግባር ስድስት

በቅድሚያ ሁለት ምልልሶችን ከራስዎ ያዘጋጁ። ምልልሶቹንም በቅደም ተከተል ያንብቡላቸው። ተማሪዎችም በምልልሶቹ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት ለይተው እንዲመዘግቡ ይንገሯቸው። ቃላቱንም ዓረፍተነገሮች ውስጥ እያስገቡ አገባባዊ ፍቻቸውን እንዲገልፁ ያድርጉ። በትክክል መሥራታቸውንም ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ተግባር ሰባት

በዚህ ሥር መዝገበቃላዊ ፍች የሚፈለግላቸው ቃላት ቀርበዋል። በመሆኑም ለጥያቄዎቹ መልስ እንዲፈልጉላቸው አስቀድመው የቤት ስራ ይስጧቸው። በክፍለጊዜውም በጋራ ውይይት ጥያቄዎቹ ምላሽ እንዲሰጥባቸው ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

## ትምህርት አምስት፡ ሰዋስው

በዚህ ክፍል ተውሳከግሶችን ስለመለየት የቀረበውን ማስታወሻ ይግለፁላቸው። ተጨማሪ ምሳሌዎችንም እየሰጧቸው ግንዛቤያቸውን እንዲያሰፉ ያድርጉ። ያልገባቸውንም እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው። ተገቢ የሆነ ምላሽም ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## መልመጃ ሰባት

በዚህ ሥር ያሉትን ጥያቄዎች ከመስራታቸው በፊት ቀደም ሲል ስለተውሳከግሶች የቀረበውን ትምህርት በድጋሚ ያስታውሷቸው። ከዚያም ጥያቄዎቹን በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ያድርጉና የጋራ መልስ ሲሰጥ ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያሳስቧቸው።

### *መርጃ መሳሪያዎች*

- *ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች*

### *ግምገማ*

*በዚህ ምዕራፍ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዱና በይዘቶቹ ስር የተካተቱት መልመጃዎች በትክክል መስራታቸውን መገምገም ያስፈልጋል። በዚህም መሠረት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ነጥቦች ፡-*

- *የባህልን ምንነት ስለማወቃቸው ማረጋገጥ፣*
- *ታሪክን አዳምጠው መልሰው መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ፣*
- *በተገቢው ቅላፄ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ማንበብ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣*
- *የአንቀጽ ዓይነቶችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣*
- *ለቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣*
- *ተውሳከግሶችን ከዓረፍተነገሮች ውስጥ መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣*
- *የግል፣ የጥንድ እና የቡድን ተግባሮችን በትክክል መስራት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣*
- *የክፍልና የቤት ስራዎችን በትክክል መስራት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣*

## በናሙናነት የተመረጡ መልሶች

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

### በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎች

1. ህብረተሰብ
2. ህብረተሰቡ ራሱ ከፈጠረው ወይም ከሌላ ህብረተሰብ ያገኘው እውቀት
3. የአንድን ህብረተሰብ የሠርግና የለቅሶ ክንውን ሥነሥርዓት፣ ምርቃት፣ የበዓላት አከባበር የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።
4. ባህልን መዝግቦ ማስተላለፍ

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

### መልመጃ ሶስት

### ለ. እውነት/ሐሰት

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሐሰት

### መልመጃ አራት

### ሐ. ማዛመድ

1. መ
2. ረ
3. ሀ
4. ሰ
5. ሐ
6. ሠ

### መልመጃ አምስት

መ. ምርጫ

1. መ
2. ሀ
3. መ

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### መልመጃ ስድስት

### አገባባዊ ፍች መስጠት

1. ሳይጠነክሩ
2. ማቃለል፣ መፍትሔ መስጠት
3. ተቀባይነት አገኘ፣ ይሁን ተባለ
4. በዘላቂነት

## ተግባር ሰባት

## መዝገበቃላዊ ፍች መፈለግ

1. ባረከ፣ ጥሩ ነገር ይስጥህ፣ ያጋጥምህ ብሎ ምኞቱን ገለፀ
2. ጥሩ ጥሩ ሸተተ
3. አረጀ፣ በዕድሜ ገፋ፣ አስታረቀ፣ ገላገለ፣ አስማማ
4. የመረዳጃ ማህበር
5. ጥሩ፣ ተፈላጊ፣ የሚያገለግል

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### መልመጃ ሰባት

ተውሳከግሶችን ከስራቸው አስምሩ

1. ገመቹ ዛሬ መጣ።
2. ፍሮምሳ ወደ አዳማ ሄደ።

# ምዕራፍ አራት

## የመንገድ ደህንነት (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

## የሚጠበቁ ውጤቶች

## 1. ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ምልልስን አዳምጠው የምልልሱን ጠቀሜታ መልሰው ይናገራሉ፤
- ፍች ላይ ለመድረስ የተለያዩ የአዳምጠ መረዳት ብልሃቶችን ይጠቀማሉ፤
- ማህበራዊ አገላለፆችን ይጠቀማሉ (ግብዣ መጋበዝ፣ሲጋበዙ ደግሞ መልስ መስጠትን)፤
- የቀረበውን አንቀፅ ጭብጥ ፣ፍች እና /ወይም አላማ ያስረዳሉ።

## 2. ትምህርት ይዘቶች

### 2.1 ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች፣
- የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች፣
- የመንገድ ትራፊክ አደጋና የመከላከያ ጥንቃቄዎች& የሚል የምልልስ ፅሑፍ፣
- የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች፣

### 2.2 ትምህርት ሁለት፡መናገር

- ከቀረበው ምልልስ ያገኙትን ጠቀሜታ መናገር፣
- የትራፊክ አደጋ የተመለከቱ የተለያዩ ስዕሎችን በመመልከት የተረዱትን መናገር፣
- የትራፊክ መብራቶችን በተመለከተ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ መስጠት፣

### 2.3 ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

- የቅድመንባብ ጥያቄዎች፣
- የመንገድ ትራፊክ ደህንነት የሚል ምንባብ፣
- ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎች፣
- እውነት /ሐሰት በማለት የሚመለሱ ጥያቄዎች፣
- ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መስጠት፣

### 2.4 ትምህርት አራት፡ መፃፍ

- ስለመንገድ ደህንነት መፃፍ፣

- የገላጭ አንቀፅ ጽሁፍ ናሙና፣
- የቡድን ውይይት ማድረግ፣
- የቀረበውን የገላጭ አንቀጽ ዋና ሀሳብ መፃፍ፣
- ገላጭ አንቀጽ መፃፍ፣

## 2.5 ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ለቃላት መዝገበቃላዊ ፍች መፈለግ፣
- የተሰመረባቸውን ቃላት በሌሎች ቃላት መተካት፣

## 2.6 ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

- በሁኔታ ተውሳከግሶች ዓረፍተነገሮች መመስረት፣
- የሁኔታ ተውሳከግሶችን ከዓረፍተነገሮች ውስጥ መለየት፣
- የዓረፍተነገር ክፍሎችን ማዛመድ፣
- ጅምር የዓረፍተነገር ክፍሎችን ማሟላት፣

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የቀደመ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
- ቅድመማዳመጥ፣ የማዳመጥ ጊዜና ድህረማዳመጥ ተግባሮችን እንዲሰሩ ማድረግ፣
- ተማሪዎች ከሚደመጥ ፣ ከሚነገር እና ከተፃፈ ነገር ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፣
- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድ እና በቡድን ሆነው ተግባሮችን እንዲፈጽሙ ማድረግ፣
- ስዕላዊ መግለጫዎችን በመመልከት ስለትራፊክ አደጋ እንዲናገሩ ማድረግ፣
- የትራፊክ መብራቶችን አገልግሎት እንዲናገሩ ማድረግ፣
- ቅድመንባብ፣ የንባብ ጊዜ እና ድህረንባብ ተግባሮችን እንዲፈጽሙ ማድረግ፣
- አጫጭር ማስታወሻዎችን መስጠት፣
- የመልመጃዎችን አሰራር በምሳሌዎች አስደግፎ ማቅረብ፣
- ገላጭ አንቀፅ እንዲፅፉ ማድረግ፣
- የክፍል እና የቤት ስራዎችን መስጠት፣
- ለተሰሩ ስራዎች ግብረመልስ መስጠት።

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ ፡ ማዳመጥ
## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

በዚህ ክፍል ሥር ያሉትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ የተወሰነ ጊዜ ይስጧቸውና በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጉ። ተማሪዎች በሚወያዩበትም ጊዜ ውይይታቸውን እየተከታተሉ አስፈላጊውን እገዛ ያድርጉላቸው። ከዚያም በውይይታቸው የተስማሙበትን ሃሳባቸውን በተወካያቸው አማካይነት እንዲገልፁ ይንገሯቸው። በሀሳባቸውም ላይ ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

በማዳመጥ ጊዜ ተማሪዎች ሙሉ ትኩረታቸውን በሚደመጠው የምልልስ ፅሑፍ ላይ እንዲያደርጉ ይንገሯቸው። በተጨማሪም ዋናውን ሐሳብ ከዝርዝር ሐሳቦች እየለዩ በማስታወሻቸው ላይ እንዲመዘግቡ ይዘዟቸው። ከዚያም &የመንገድ ትራፊክ አደጋና የመከላከያ ጥንቃቄዎች& የሚለውን ፅሑፍ ያንብቡላቸው። የፅሑፉን ግማሽ ክፍል እንዳነበቡ ንባብዎን ገታ ያድርጉና የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው። ምላሻቸውንም ይቀበሏቸውና ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

### የመንገድ ትራፊክ አደጋና የመከላከያ ጥንቃቄዎች

**ጠያቂ፡-** “የመንገድ ትራፊክ አደጋ ማለት ምን ማለት ነው?”

**መላሽ፡-** “የመንገድ ትራፊክ አደጋ በአሽከርካሪዎች ወይም በእግረኞች ስህተት ምክንያት በሰዎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ የሚከሰት አደጋ ነው።”

**ጠያቂ፡-** “የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመከላከል እግረኞች ምን ማድረግ አለባቸው?”

**መላሽ፡-** “እግረኞች ለእግረኞች የወጡትን የትራፊክ ህጎች ማክበር አለባቸው። ለምሳሌ መንገድ ላይ በሚጓዙበት ጊዜ በእግረኞች መንገድ ላይ ብቻ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።&

**ጠያቂ፡-** “የእግረኞች መንገድ ሲባል ምን ማለት ነው@”

**መላሽ፡-** &የእግረኞች መንገድ ማለት እግረኞች ብቻ እንዲሄዱበት ተብሎ የተሰራ መንገድ ነው።”

**ጠያቂ፡-** “የእግረኞች መንገድ ለእግረኞች የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?&

**መላሽ፡-** “የእግረኞች መንገድ ተሽከርካሪዎች የማይተላለፉበት በመሆኑ እግረኞች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ያስችላቸዋል።”

**ጠያቂ፡-** “እግረኞች ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል@”

**መላሽ፡-** “መንገዱ የእግረኞች መንገድ አለው ወይስ የለውም የሚለውን ማስተዋል ይጠበቅባቸዋል።”

**ጠያቂ፡-** “የእግረኞች መንገድ ከሌለስ እግረኞች ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል?”

**መላሽ፡-** “እግረኞች የመንገዱን የመጨረሻ ጠርዝ በመያዝ በግራ በኩል ባለው መንገድ መጓዝ ይኖርባቸዋል።”

**ጠያቂ፡-** “እግረኞች” ከአንዱ አቅጣጫ ወደ ሌላ አቅጣጫ መንገድ ለመሻገር ቢፈልጉ ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል::

**መላሽ፡-** “እግረኞች መንገድ ለማቋረጥ ተብሎ በተዘጋጀው “ዜብራ” ላይ መጠቀም ይኖርባቸዋል።

(በትምህርት ቤቶች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማኑዋል ከሚለው በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

በዚህ ስር ተማሪዎች በማዳመጥ ጊዜ ከመምህር መምሪያ ላይ የተነበበላቸውን ምልልስ እያስታወሱ በቃል የሚመልሷቸው አራት ጥያቄዎች ቀርበዋል። እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች የምልልሱን ሀሳብ መረዳታቸውን ለመገምገም የሚያስችሉ በመሆናቸው በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጉ። እየተወያዩ ባሉበትም ጊዜ ሂደቱን ለመከታተል ይሞክሩ። ከውይይቱም በኋላም በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ከስምምነት የደረሱበትን መልስ እንዲናገሩ ያድርጉ። ከዚያም የእርስዎን ምላሽ በመስጠት የመልሳቸውን ትክክለኛነት ያረጋግጡላቸው።

## ክፍለጊዜ ሶስት

## ተግባር አንድ

በዚህ ሥር ያሉትን ጥያቄዎች በቅደም ተከተል እንዲወያዩባቸው ያድርጉ። የውይይታቸውንም ክንውን ይከታተሉና አስፈላጊውን እገዛ ያድርጉላቸው። ከዚያም ተወያይተው የደረሱባቸውን ድምዳሜዎች በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ እድል ይስጧቸው። በመጨረሻም የእርስዎን ሐሳብ ያክሉበትና ያጠናቅቁ።

## ክፍለጊዜ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር ሁለት

በዚህ ክፍል ሁለት የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። የፊደል& ሀ &ን ጥያቄ በሚመለከት ቀደም ሲል ምልልሱ ሲነበብላቸው በያዙት ማስታወሻ መሰረት ከምልልሱ ያገኙትን ጠቀሜታ እንዲናገሩ ያድርጉ። እርስዎም የግልዎን አስተያየት ያክሉበት።

በፊደል “ለ” ጥያቄ ስር የትራፊክ አደጋን የሚያሳዩ የተለያዩ ስዕሎች ቀርበዋል ። ተማሪዎችም በቡድን ሆነው እነዚህን ስዕሎች በቅደም ተከተል እየተመለከቱ እንዲነጋገሩበት ያድርጉ። ከዚያም ስለእያንዳንዱ ስዕል የተረዱትን በተወካያቸው አማካኝነት እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው። እርስዎም የበኩልዎን አስተያየት በማቅረብ ስለስዕሎቹ በትክክል መግለፅ መቻላቸውን ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ አምስት

## ተግባር ሶስት

በፊደል &ሐ& ተማሪዎች የትራፊክ ህጎችን በተመለከተ ምልልስ አዘጋጅተው ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲያቀርቡ የታሰበ ነው። ስለዚህ በቅድሚያ የፆታ ስብጥር ባላቸው በጥንድ ቡድኖች ያደራጇቸውና ምልልሱን ከክፍል ውጪ ተለማምደው እንዲመጡ ያሳስቧቸው። ከዚያም በክፍለጊዜው ተራ በተራ ምልልሱን እንዲያቀርቡ ያድርጉ። በመጨረሻም ገንቢ አስተያየት ይስጧቸውና ያጠቃልሉ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

## ተግባር አራት

በፊደል &መ& ስር በምስል 1 ላይ የሚታዩት የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ የትራፊክ መብራቶች እያንዳንዳቸው የየራሳቸው አገልግሎት ስላላቸው በተማሪ መጸሐፍ ላይ በቀረቡት ጥያቄዎች መሰረት ስለአገልግሎታቸው እንዲናገሩ ያድርጉ። ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ትክክል መሆኑን የተለያዩ ማጣቀሻዎችን ዋቢ በማድረግ ማረጋገጫ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ ሰባት

በምስል 2 ላይ የሚታዩት የእግረኛ ማስተላለፊያ የትራፊክ መብራቶችም የየራሳቸው አገልግሎት ስላላቸው ተግባሩን በፊደል “መ” ሥር ባለው የአፈፃፀም መመሪያ መሰረት እንዲሰሩ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ ስምንት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

በቅድሚያ ከንባብ በፊት የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው ቅድመንባብ ጥያቄዎችን በቡድን ተወያይተው በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። እርስዎም በጥያቄዎቹ ላይ አስተያየት ይስጡባቸው። ከዚያም “የመንገድ ትራፊክ ደህንነት” የሚለውን ምንባብ በመፅሐፋቸው ላይ ባለው የሉኖሳስ መመሪያ መሰረት በየግላቸው እንዲያነቡ ይዘዟቸው። በንባብ ወቅት ድምፅ ማሰማት፣ ከንፈር ማንቀሳቀስ፣ ዕሁፉን በጣታቸው መጠቆም እንደሌለባቸው ይንገሯቸው፤ ምክንያቱንም ያስረዷቸው። ሁለተኛውን አንቀፅ አንብበው እንደጨረሱ ንባባቸውን ገታ አድርገው የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጉ። እርስዎም በተራዎ ምንባቡን እያነበቡ ይግለጹላቸው። አዳዲስ ቃላትንም ይተርጉሙላቸው። የመልመጃ ሁለት ጥያቄዎችንም በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ የሚሰሩ እንደሆነ ይንገሯቸውና ተዘጋጅተውባቸው እንዲመጡ ያሳስቧቸው።

### ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

በዚህ ስር ሁለት አይነት ጥያቄዎች ይገኛሉ። በፊደል &ሀ& ስር ምንባቡን መሰረት አድርገው በቃል የሚመለሱ ስድስት ጥያቄዎች ቀርበዋል። እነዚህን ጥያቄዎች ከማሰራትዎ በፊት የአምስት ደቂቃ ጊዜ ይስጧቸውና ምንባቡን በድጋሚ በየግላቸው እንዲያነቡ ይንገሯቸው። ከዚያም ጥያቄዎቹን በቡድን ተወያይተውባቸው በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ ። እርስዎም በምላሻቸው ላይ ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

በፊደል &ለ& ስር ያሉትን የእውነት /ሐሰት አምስት ጥያቄዎች በተመሳሳይ ሁኔታ በቡድን ተወያይተው እንዲመልሱ ያድርጉ። እርስዎም የራስዎን አስተያየት በመስጠት የመልሳቸውን ትክክለኛነት ያረጋግጡላቸው።

## ትምህርት አራት ፡ መፃፍ

### ክፍለጊዜ አስር

## ተግባር አምስት

በዚህ ስር ተማሪዎች ቀደም ሲል ከቀረበላቸው ትምህርት ስለመንገድ ደህንነት የተረዱትን ነገር ከ30 ባላነሱ ቃላት ገላጭ አንቀፅ ፅፈው እንዲያቀርቡ ያድርጉ። በትክክል መፃፋቸውንም አረጋግጠው ግብረመልስ ይስጧቸው። ይህንንም ተግባር በክፍል ውስጥ ያሰሯቸው ።

### ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ተግባር ስድስት

በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች በመፅሀፋቸው ላይ በገላጭ ስልት የተፃፈውን አንቀጽ ጊዜ ይስጧቸውና እንዲያነቡ ያድርጉ። በመቀጠልም በአንቀፁ ውስጥ ያሉትን አያያዦች እንዲለዩና አገልግሎታቸውን እንዲገልፁ፣ በተጨማሪም ሐሳቡን በቅደም ተከተል አሳጥረው እንዲፅፉ ያሳስቧቸው። በመጨረሻም ከተሰሩት ፅሑፎች መካከል ናሙና ይምረጡና ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ። እርስዎም ገንቢ አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ተግባር ሰባት

በዚህ ስር በተማሪ መጽሐፍ ላይ ባለው ናሙና ጽሁፍ መሰረት &የእግረኛ ማስተላለፊያ የትራፊክ መብራት አጠቃቀም& በሚል ርዕስ በስምንት ዓረፍተነገሮች የተዋቀረ አንድ ገላጭ አንቀጽ እንዲጽፉ ታዘዋል። በዚህ መሰረት አንቀጹን ለመፃፍ በቂ ጊዜ ማግኘት እንዲችሉ አስቀድመው የቤት ስራ ይስጧቸው። ከዚያም በክፍለጊዜው ፅፈው ያመጡትን እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ትክክለኛውን ቅደም ተከተል ጠብቀው መፃፋቸውንም ያረጋግጡ። በመጨረሻም ለስራቸው ገንቢ አስተያየት ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሦስት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### ተግባር ስምንት

በቃላት ትምህርት ስር መዝገበቃላዊ ፍች የሚፈለግላቸው ስምንት ቃላት ቀርበዋል ። በዚህም መሰረት ተማሪዎች ለተሰጡት ቃላት መዝገበቃላት ተጠቅመው ተመሳሳይ ፍች እንዲፈልጉላቸው ይንገሯቸው። ለዚህም አስቀድመው የቤት ስራ ሰጥተው እንዲሰሩ ያድርጉ። ይህም መዝገበቃላት ለመጠቀም ወደ ቤተ መፃህፍት የሚሄዱ ስለሆነ በቂ ጊዜ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። ከዚያም በክፍለጊዜው ደብተራቸውን ያርሙላቸው፤ የጋራ የሆነ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

### መልመጃ ሦስት

በዚህ ክፍል በፊደል "ሀ" ሥር ለተዘረዘሩት ቃላት ቀጥተኛ ፍቻቸውን እንዲሰጡ፣ እንዲሁም ቃላቱ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ፍች እንዲገልፁ ታዘዋል። በዚህም መሰረት ጥያቄውን በትዕዛዙ መሰረት እንዲሰሩ ያድርጉ። በጋራ ውይይት ትክክለኛውንም ግብረመልስ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

በፊደል "ለ" ተማሪዎች በዓረፍተነገሮች ውስጥ ደምቀው የተፃፉትን ቃላት ፍቻቸውን በሚያሳዩ ሌሎች ቃላት ተክተው እንዲያሳዩ ታዘዋል። በዚህም መሰረት የነዚህን ቃላት ፍቻቸውን ማግኘት የሚችሉት ቃላቱ በገቡበት ሁኔታ እንደሆነ ይንገሯቸው። ፍቻቸውም አንድና የተወሰነ ብቻ እንደሆነ ጨምረው ይግለፁላቸው። በመቀጠልም ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ ገልብጠው እንዲሰሩ ይዘዟቸው። ከዚያም የሰሩትን ተማሪዎች ደብተር ያርሙላቸውና የጋራ የሆነ ግብረመልስ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ትምህርት ስድስት ፡ ሰዋስው

### መልመጃ አራት

በዚህ ክፍል ስር ስለሁኔታ ተውሳከግስ የሚገልፅ ማስታወሻ ቀርቧል። እርስዎም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ያለውን ማስታወሻና ምሳሌ በዝርዝር ያስረዷቸው፤ ተጨማሪ የሁኔታ ተውሳከግስ ቃላትና ሀረጋትን በመጠቀም ዓረፍተነገሮች እየመሰረቱ ያሳዩዋቸው። ከዚያም በመጽሃፋቸው ላይ በ "ሀ" ሥር በተሰጡት ቃላትና ሀረጋት ዓረፍተነገሮች እንዲመሰርቱባቸው አስቀድመው የቤት ስራ ይስጧቸው። በክፍለ ጊዜውም የሰሩትን እንዲያቀርቡ ያድርጉ። በትክክል መስራታቸውንም ግብረመልስ በመስጠት ያረጋግጡላቸው።

## ክፍለ ጊዜ አስራ ሰባት

## መልመጃ አምስት

በዚህ ስር ተማሪዎች በዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን የሁኔታ ተውሳከግስ አመልካች የሆኑትን ከስራቸው በማስመር እንዲለዩዋቸው ታዘዋል። በዚህም መሰረት በመጽሐፋቸው ላይ ያለውን ምሳሌ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያስረዷቸው። ከዚያም የፊደል "ለ"ን ጥያቄዎች በደብተራቸው ላይ ጽፈው በክፍል ስራ እንዲሰሩ ያድርጉ። የሰሩትንም በማረም ትክክለኛውን ግብረ መልስ ይስጧቸው።

## ክፍለ ጊዜ አስራ ስምንት

## መልመጃ ስድስት

በፊደል " ሐ " ትዕዛዝ ሥር በአንድ ምድብ የተሰጡትን ጅምር የዓረፍተነገር ክፍሎች ከሌላ ምድብ በመምረጥ እንዲያዛምዱ ተፈልጓል። ስለሆነም በቅድሚያ ስለትምህርቱ በምሳሌ የተደገፈ ማብራሪያ ይስጧቸው። ጅምር ዓረፍተነገሮች የሆኑበትንም ምክንያት ያስረዷቸው። የተሟላ ሐሳብ እንዲሰጡ ማሟያ እንደሚያስፈልጋቸውም ይግለጹላቸው። ከዚያም ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ ገልብጠው በክፍል ስራ እንዲሰሩ ያድርጉ። በመጨረሻም የሰሩትን በማረም ግብረመልስ ይስጧቸው ።

## ተግባር ዘጠኝ

በፊደል " መ " ትዕዛዝ ሥር ያለውም ቀደም ሲል ጅምር አረፍተ ነገሮችን ስለ ማሟላት የቀረበውን ትምህርት የሚያጠናክር ነው። በዚህም መሰረት በመጀመሪያ በመጽሐፋቸው ላይ ያለውን ምሳሌ ሰሌዳ ላይ ጽፈው ይግለጹላቸው። ከዚያም የተሰጡትን ጅምር የአረፍተነገር ክፍሎች በራሳቸው ሃሳብ እንዲያሟሉ ያድርጉ። ይህንንም ተግባር የክፍል ስራ በመስጠት ያከናውኑ። በመጨረሻም የሰሩትን በማረም ግብረመልስ ይስጧቸው።

## መርጃ መሳሪያዎች

- የመንገድ ትራፊክ አደጋን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች፣
- የትራፊክ መብራት ምልክቶችን የሚያሳዩ ስዕላዊ መግለጫዎች፣
- ስለመንገድ ደህንነት በመቅረፀድምፅ የተቀረፀ ትምህርት፣

## ግምገማ

በየክፍሉ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ መስጠታቸውን መከታተልና ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በመሆኑም ተማሪዎቹ ምን ያህል የምዕራፉን ትምህርት ይዘት እንደተረዱ በተለያዩ መንገዶች መገምገም የሚጠበቅ ተግባር ነው። በዚህም መሰረት

- የመንገድ ትራፊክ አደጋ የሚከላከሉበትን ዘዴ ማወቃቸውን ማረጋገጥ፣
- የመንገድ ትራፊክ አደጋ አይነቶችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የትራፊክ መብራት ምልክቶችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣

- አንብበው የተረዱትን ሀሳብ በቃል መግለጽ መቻላቸውን መከታተል፣
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መስጠት መቻላቸውን ማየት፣
- በገላጭ ስልት አንቀጽ መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ ፣
- የሁኔታ ተውሳከግሶችን ምንነት ማወቃቸውን መፈተሽ፣
- የዓረፍተነገር ክፍሎችን ማዛመድ መቻላቸውን ማየት ፣

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**በቃል የሚመለሱ**

1. እግረኞች ለእግረኞች የወጡትን የትራፊክ ህጎች በማክበር
2. እግረኞች የመንገዱን የመጨረሻ ጠርዝ በመያዝ በግራ በኩል ባለው መንገድ መጓዝ ይኖርባቸዋል ።
3. በእግረኞች መንገድ ላይ
4. መንገድ ለማቋረጥ የሚያገለግል የእግረኞች መሻገሪያ

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

### መልመጃ ሁለት

**ለ. እውነት /ሐሰት**

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት
5. ሐሰት

## ትምህርት አምስት ፡ ቃላት

### መልመጃ ሦስት

**ለ. ደምቀው የተፃፉትን ቃላት በሌሎች ቃላት መተካት**

1. ከፍተኛውን
2. መከሰት
3. ማሳጣት/ማጥፋት
4. የሚታይ
5. በመጣስ / በማፍረስ
6. ጥፋቶች / ጉድለቶች

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### መልመጃ ስድስት

**ሐ .የአረፍተነገር ክፍሎችን ማዛመድ**

1. ለ
2. ሠ
3. መ
4. ሀ
5. ሐ
6. ሰ
7. ረ

## ተግባር ዘጠኝ

**መ. ጅምር የአረፍተነገር ክፍሎችን ማሟላት**

1. ከክፍል አንደኛ ወጣች።
2. ጉልበቷ ተብረከረከ።
3. ነገ ትመጣለች።
4. ብዙ ምርት አገኘ።
5. ገመቹ ይተኛ ነበር።
6. ፍርሀቴ ለቆኛል ።

# ምዕራፍ አምስት

## አካባቢ ጥበቃ (ክፍለጊዜ ብዛት 18)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ጽሑፍ ከቀደመ እውቀታቸውና ልምዶቻቸው ጋር ያዛምዳሉ፤
- መዝገበቃላትን ወይም የቃላት ዝርዝርን በመጠቀም የሆሂያት አሰዳደርን፣ ፍችንና የቃላት እርባታን ይለያሉ፤
- በክፍል ደረጃው የመፃፍ ተግባር ወቅት ድምፀት አመላካቾችን ይጠቀማሉ።

## 2. የትምህርት ይዘቶች

### 2.1 ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች፣
- "የተፈጥሮና የአካባቢ ሚዛን መጠበቅ" የሚል ምንባብ፣
- የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ፣
- የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች፣

### 2.2 ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- የቀረበውን ምንባብ እንደገና መተረክ፣
- የቡድን ውይይት በማድረግ የስምምነት ሐሳብ መናገር፣

### 2.3 ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

- ቅድመንባብ ጥያቄዎች፣
- "አካባቢ ጥበቃ" የሚል ምንባብ ማንበብ፣
- የንባብ ጊዜ ጥያቄ፣
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች፣
- ቃላትን በምዕላድ ደረጃ በመነጠልና በማጣመር ማንበብ፣

### 2.4 ትምህርት አራት፡ መፃፍ

- ከአንቀጽ ውስጥ ኃይለቃሎችን ለይቶ መፃፍ፣
- ሆሂያትን በትክክል ሰድሮ ቃላት መፃፍ፣
- ድምፀት አመላካቾችን መጠቀም፣

### 2.5 ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- የቃላትን መዝገበቃላዊ ፍች መግለፅ፣
- ቃላትን ማደን፣

### 2.6 ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

- ነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞችን መለየት፣
- የስሞችን ነጠላ እና ብዙ ቁጥር መፃፍ፣

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ዳራዊ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
- ሶስቱን የማዳመጥ ተግባራት እንዲሰሩ ማድረግ፣
- የትምህርት ይዘት ማስታወሻዎችን እንዲይዙና ከመፅሐፋቸው ላይ እንዲፅፉ ማድረግ፣
- የግልና የቡድን ሥራዎችን እንዲሠሩ ማድረግ፣
- የመናገር ተግባራትን በትክክል እንዲሠሩ ማድረግ፣
- ቅድመንባብ፣ የንባብ ጊዜና ድህረንባብ ተግባሮችን በትክክል እንዲሠሩ ማድረግ፣
- ቃላትን በምዕላድ ደረጃ በመነጠልና በማጣመር እንዲያነቡ ማድረግ፣
- የመልመጃዎችን አሠራር በምሳሌዎች አስደግፎ ማቅረብ፣
- የመፃፍ፣ የቃላትና የሰዋስው መልመጃዎችን በትክክል እንዲሠሩ ማድረግ፣
- የክፍልና የቤት ሥራዎችን መስጠት፣
- ለተለያዩ ተግባሮች ድጋፍ፣ አስተያየትና ግብረመልስ መስጠት።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎችን ለማሠራት በቅድሚያ ተማሪዎችን አምስት አምስት አባላት ባሏቸው ቡድኖች ያደራጇቸው። ከዚያም የ5 ደቂቃ ጊዜ ይስጧቸውና በጥያቄዎቹ ላይ ተወያይተው ምላሻቸውን በቃል እንዲሰጡ ያድርጉ።እርስዎም ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

በቅድሚያ የሚነበብላቸውን ምንባብ በጥሞና እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በማዳመጥ ሂደት ዋና ዋና ሐሳቦችን ለይተው በማስታወሻቸው ላይ እንዲይዙ ያሳስቧቸው። የአካባቢ ሚዛን መጠበቅ" የሚለውን ምንባብ ማንበብ ይጀምሩ። የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን አንቀጾች ካነበቡ በኋላ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲያሚሉ ያድርጉ። ከዚያም የቀሩትን ሁለቱን አንቀጾች ያንብቡና ማንበብዎን ያጠናቅቁ። ተማሪዎች ያልተረዱት ነገር ካለ እንዲጠይቁ ዕድል ያመቻቹላቸው፤ ምላሽም ይስጧቸው።

## የተፈጥሮና የአካባቢ ሚዛን መጠበቅ

የሀገራችን የተፈጥሮ ሀብትና አጠቃላዩ የአካባቢ ይዞታ የህዝብ ብዛት ከሚያመጣው ለውጥ ጋር ተገናዝቦ አልተራመደም። ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ በአካባቢና በተፈጥሮ መካከል ያለው ግንኙነት ተጠብቆ አለመራመዱ ቀውስን በማስከተል የተለያዩ ችግሮች እንዲከሰቱ አድርጓል። የድርቅ መባባስና ያስከተለው እልቂት ከዚህ ከሚመነጩ ችግሮች መካከል ሊጠቀስ የሚችል ነው።

ለተፈጥሮ ሀብት ብክነትና ለአካባቢ አየር መቃወስ የደን መጨፍጨፍ ጉልህ ድርሻ አለው። የእርሻ መሬትን ለማስፋፋት፣ ለግጦሽ፣ ለማገዶ እንጨት፣ ለቤት መሥሪያና ለቁሳቁስ ወዘተ. ሲባል በደን ላይ ጭፍጨፋ ሲካሄድ ኖሯል፤ አሁንም እየተካሄደ ነው።

የመሬት መራቆት የዱር እንስሳትን ሕይወትና ጠቃሚ ዕፀዋትን ያጠፋል፤ የአፈር መሸርሸርንና የውሃ ብክነትን ያፋጥናል። የአፈር መሸርሸር የቀረውን አፈር ለምነት እንዲያጠፋና ምርት እንዲቀንስ ያደርጋል። ጉዳቱ ተደራራቢ ነው። በመሆኑም ያለውን የመጠበቅ፣ የጠፋውንም የመተካትና የአካባቢን ጥበቃ የማጠናከር ጥረት በአዲስ መልክ መራመድ ይኖርበታል።

ይህ ሁኔታ በአዲሱ የልማት መርሃግብር ትኩረት ያገኘ በመሆኑ ጥፋቱ ከልማቱ ሊቀድም አይገባም። በተፈጥሮና በአካባቢ ያለውን የተዛባ ሚዛን ለማስተካከልና ለመጠበቅ በሚደረገው ጥረት ሁሉም ሊረባረብ ይገባል። በተለይ ወጣቱ ትውልድ ለአሁኑም ሆነ ለወደፊት ህይወቱ ወሳኝ ድርሻ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ለማጠናከርና ልማትን ለማፋጠን በሚደረገው ጥረት ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆን ይጠበቅበታል።

(ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፤ የአማርኛ መርጃ መጽሐፍ፣ 2002 ዓ.ም።)

### ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

በዚህ ሥር ተማሪዎች የተነበበላቸውን ምንባብ መረዳታቸውን ለማወቅ የመልመጃ እና የተግባር ጥያቄዎች ቀርበዋል። በዚህም መሰረት በጥያቄዎቹ ላይ ተወያይተውባቸው መልሳቸውን በቃል እንዲሰጡ ያድርጉ። ተገቢ የሆነ አስተያየትም ይስጧቸው። በተግባር 1 ሥር ያለውን 2ኛ ጥያቄ በተመለከተ የህብረተሰብ ሳይንስ መምህራቸውን ጠይቀው ያገኙትን መረጃ በማደራጀት ሐሳቡን ለክፍላቸው ተማሪዎች በቃል እንዲያቀርቡ እድል ይስጧቸው። በመጨረሻም ለሥራዎቻቸው ገንቢ አስተያየት ይለግሷቸው።

**ክፍለጊዜ ሶስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር ሁለት

በዚህ ሥር ያለውን የፊደል "ሀ" ጥያቄ ተማሪዎች እንዲሰሩ ቀደም ሲል የተነበበላቸውን ምንባብ አንድ ጊዜ ደግመው ያንብቡላቸው። ከዚያም ያዳመጡትን በቃል መልሰው እንዲተርኩ ያድርጉ። በአቀራረባቸው ላይ ገንቢ የሆነ አስተያየት ይለግሷቸው።

**ክፍለጊዜ አራት**

## ተግባር ሦስት

በዚህ ሥር ስለአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከተለያዩ ምንጮች መረጃ እንዲያሰባስቡ ይዘዟቸው። ከዚያም በቡድን እንዲደራጁ ያድርጉና ባሰባሰቧቸው መረጃዎች ላይ ውይይት እንዲያደርጉ ሁኔታውን ያመቻቹላቸው። በመቀጠልም ወጥ የሆነ የተደራጀ መረጃ ለክፍል ጓደኞቻቸው በተወካያቸው አማካኝነት እንዲናገሩ ያድርጉ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

በዚህ ሥር የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስ በቡድን ውይይት ምላሽ የሚሰጥባቸው ሶስት ጥያቄዎች ቀርበዋል። በዚህም መሠረት ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲወያዩና ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ። እርስዎም በምላሻቸው ላይ አስተያየት ይስጧቸው።

## የማንበብ ሂደት

በዚህ ክፍል "አካባቢ ጥበቃ" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድርጉ። በሚያነቡበት ጊዜ ደምቀው በተፃፉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ድምፆች በመነጠልና በማጣመር እንዲያነቡ ያሳስቧቸው። የምንባቡን ሁለተኛ አንቀፅ አንብበው ከጨረሱ በኋላም ንባባቸውን ገታ አድርገው የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጉ። በመጨረሻም እርስዎም ምንባቡን እያነበቡ ይግለፁላቸዉ። ያልገባቸው ካለ እንዲጠይቁ ያድርጉና ምላሽ ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

በዚህ ሥር ያሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ተገቢ የሆነ መልስ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። እርስዎም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ ሰባት

### መልመጃ ሦስት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የምንባቡ አንቀጾች ከሚያስተላልፉት መልዕክት ጋር እንዲያዛምዱ የታዘዙበት ነው። በዚህም መሠረት እያንዳንዱ አንቀጽ የራሱ መልዕክት እንዳለው ገለጻ ይስጧቸውና መልመጃውን በትዕዛዙ መሠረት እንዲሰሩ ያድርጉ። ተማሪዎች የሰጡት መልስ ትክክል ስለመሆኑም ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ ስምንት

### መልመጃ አራት

በዚህ ክፍል ሥር የቀረቡትን የምርጫ ጥያቄዎች ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ ገልብጠው በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ያድርጉ። ከዚያም ደብተራቸውን በመሰብሰብ ያርሙላቸው። በመጨረሻም በጋራ ውይይት ግብረመልስ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

### መልመጃ አምስት

በዚህ ሥር ምንባቡን መሰረት አድርገው የቀረቡትን ሐሳቦች እውነት/ሐሰት በማለት እንዲመልሱ ተፈልጓል። በመሆኑም ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡና እንዲሰሩ ይዘዟቸው። ከዚያም ተማሪዎች እርስ በርስ ደብተራቸውን በመቀያየር የጋራ መልስ ሲሰጥ እንዲተራረሙ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አስር

### መልመጃ ስድስት

በዚህ ሥር ያሉትን የማዛመድ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ይዘዟቸው። ከዚያም ሰርተው ከጨረሱ በኋላ ደብተራቸውን እንዲቀያየሩ ያሳስቧቸውና ትክክለኛ መልስ ሲሰጥ እንዲተራረሙ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

### መልመጃ ሰባት

በዚህ ክፍል ሥር ያለውን መልመጃ ለማሠራት በቅድሚያ በምዕራፍ ሁለት ስለቀለም መዋቅር እና ምዕላድ የተማሩትን ያስታውሷቸው። በመቀጠልም የተሰጡትን ቃላት በምዕላድ ደረጃ በመነጠልና በማጣመር እንዲያነቡ ያድርጉ። ተማሪዎች እያነበቡ ባሉበት ጊዜ ድጋፍ የሚፈልጉ ካሉ ተገቢውን ድጋፍ ያድርጉላቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት አራት፡ መፃፍ

## ተግባር አራት

በፊደል "ሀ" ትዕዛዝ ተማሪዎች በምዕራፍ አንድ ስር በአንቀፅ ውስጥ ስለሚገኙ ዓረፍተ ነገሮች የተማሩትን ያስታውሷቸው። ከዚያም "አካባቢ ጥበቃ" በሚለው ምንባብ ውስጥ ያሉትን የአንቀጽ አንድ፤ ሁለትና ሶስት ኃይለቃሎች ለይተው በደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ይዘዟቸው። ፅፈው ከጨረሱ በኋላም ተማሪዎች ደብተራቸውን እርስ በርስ በመቀያየር በጋራ ውይይት ግብረመልስ ሲሰጥ እንዲተራረሙ ያድርጉ። በመጨረሻም የታረመውን ደብተር በመሰብሰብ አፈፃፀሙን ይገምግሙ። ገንቢ አስተያየትም ይስጧቸው።

በፊደል "ለ" ትዕዛዝ ሥር ከታች የቀረበውን አንቀፅ አንብበው ኃይለቃሉንና ዘርዛሪ አረፍተነገሮችን ለይተው እንዲፅፉ የታዘዙ ስለሆነ በዚሁ መሰረት በደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲያሳዩ ያድርጉ። እርስዎም በጋራ ውይይት ትክክለኛውን ግብረመልስ ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ሦስት

## ተግባር አምስት

በቅድሚያ ተማሪዎች እንዲፅፏቸው ያሰቡትን ቃላት ያዘጋጁ። በመቀጠል ቃላቱን አንድ በአንድ ያንብቡላቸው። ተማሪዎችም የሚያደምጧቸውን ቃላት ሆሄያት በትክክል ለመፃፍ እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው። ቃላቱን ፅፈው ከጨረሱ በኋላም እርስ በርስ ደብተራቸውን እንዲለዋወጡ ያሳስቧቸው። እርስዎም ቃላቱን በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎች እሱን እያዩ እርማት እንዲያደርጉ ይንገሯቸው። ከዚያም የታረመውን ደብተር በመሰብሰብ አፈፃፀሙን ይመዝኑ። ተገቢ አስተያየትም ይስጧቸው፡

### መልመጃ ስድስት

በዚህ ሥር ድምፀት አመላካች ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተነገር ውስጥ አስገብተው እንዲያሳዩ ታዘዋል። በዚህም መሠረት የተሰጠውን ምሳሌ በማየት የተዘረዘሩትን ቃላት በዓረፍተነገር ውስጥ አስገብተው ማሳየት እንዲችሉ አስቀድመው የቤት ሥራ ይስጧቸው። ከዚያም በክፍለጊዜው ደብተራቸውን በመሰብሰብ የሠሩትን ያርሙላቸው። በመጨረሻም በጋራ ተሳትፎ ትክክለኛውን ግብረመልስ ይስጧቸው። በቀጣይ ያለውንም የቤት ሥራ ሰርተው እንዲመጡ ይዘዟቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### መልመጃ ሰባት

በዚህ ሥር አካባቢ ጥበቃ ከሚለው ምንባብ ውስጥ የወጡ ቃላት ተዘርዝረዋል። በዚህም መሰረት ቃላቱን ከምንባቡ ውስጥ እየፈለጉ አውዳዊ ፍቻቸውን እንዲገልፁ ያድርጉ። የመልሶቻቸውን ትክክለኛነትም ያረጋግጡ።

### ክፍለጊዜ አስራ አምስት

### መልመጃ ስምንት

በዚህ ሥር ያለውን ለማሠራት በቅድሚያ ቃላቱን አድነው የሚያገኟቸው አካባቢ ጥበቃ በሚለው ምንባብ ውስጥ እንደሆነ ይጠቁሟቸው። በመቀጠል ከ1-6 ያሉትን ሐሳቦች የያዘውን ሰንጠረዥ ደብተራቸው ላይ በመገልበጥ በምሳሌው መሠረት ቃላቱን እያደኑ ከጎናቸው እንዲፅፉ ያድርጉ። ከዚያም በክፍል ውስጥ በመዘዋወር የሠሩትን ያርሙላቸው። በመጨረሻም ትክክለኛውን መልስ ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ስህተት ካላቸው እንዲያስተካክሉ ያድርጉ።

### ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

### መልመጃ ዘጠኝ

በቅድሚያ በዚህ ስር ያለውን ማስታወሻ በሚገባ ይግለፁላቸው። ምሳሌዎችም እየሰጧቸው ያስረዷቸው። ከዚያም በ "ሀ" ሥር ያሉትን አረፍተነገሮች እንዲፅፉና በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ነጠላ ቁጥር ስሞችንና ብዙ ቁጥር ስሞችን ከስራቸው በማስመር ለይተው እንዲያመለክቱ ያድርጉ። እርስዎም ቶሎ ሠርተው የጨረሱትን ተማሪዎች ደብተር እየተዘዋወሩ ያርሙላቸው። ትክክለኛውንም መልስ ሰሌዳ ላይ በመፃፍ እርማት እንዲወስዱ ይጠቁሟቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ አስር

በዚህ ሥር ለተሰጡት የነጠላ ቁጥር ስሞች የብዙ ቁጥር ስሞቻቸውን በተሰጠው ምሳሌ መሠረት በክፍል ውስጥ እንዲሠሩ ያድርጉ። ሠርተው የጨረሱትንም ተማሪዎች ደብተር ያርሙላቸው። ትክክለለኛውን መልስ ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማስተካከያ እንዲወስዱ ይንገሯቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### መልመጃ አስራ አንድ

በዚህ ክፍል ለተሰጡት የብዙ ቁጥር ስሞች የነጠላ ቁጥር ስሞቻቸውን በተሰጠው ምሳሌ መሠረት በክፍል ውስጥ እንዲሠሩ ያድርጉ። ቶሎ ሠርተው የጨረሱትን ተማሪዎች ደብተር ያርሙላቸው። ትክክለኛውንም መልስ ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ስህተት ካላቸው እንዲያስተካክሉ ያሳስቧቸው።

## የመርጃ መሳሪያዎች

የአካባቢ ጥበቃን የሚያሳዩ የተለያዩ ስዕላዊ መግለጫዎች

## ግምገማ

በዚህ ምዕራፍ ሥር የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዱ፣ እንዲሁም የተሰጡትን መልመጃዎች በትክክል ስለመስራታቸው መገምገም ተገቢ ነው። በዚህም መሠረት

ትኩረት ሊያደርጉባቸው የሚገቡ ነጥቦች፡-

- የተፈጥሮና የአካባቢ ሚዛን አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ችግርና ውጤት ማወቃቸውን ማረጋገጥ፣
- ያዳመጡትን በቃል መልሰው መተረክ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የቀረበውን ምንባብ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያለስህተት ማንበብ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- ቃላትን በምዕላድ ደረጃ በመነጠልና በማጣመር ማንበብ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የአንቀፅ ኃይለቃልን ለይቶ ማውጣትና መፃፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- ቃላትን ለመፃፍ ትክክለኛ የሆሄያት አሰዳደር መጠቀም መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- ከፅሑፍ ውስጥ ቃላት አድኖ ማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- ድምፀት አመላካች ቃላትን በዓረፍተነገር ውስጥ አስገብተው ማሳየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- በዓረፍተነገሮች ውስጥ ነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞችን ለይተው ማመልከት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- ቃላትን በነጠላና በብዙ ቁጥር ስሞች ማርባት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የግልና የቡድን ተግባሮችን በትክክል መስራት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የክፍልና የቤት ሥራዎችን በትክክል መስራት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

# በናሙናነት የተመረጡ መልሶች

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሦስት

**አዛምድ**

1. ለ 2. ሀ 3. ሐ

### መልመጃ አራት

**ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. ሐ 2. መ 3. ሀ 4. ሐ

### መልመጃ አምስት

**እውነት/ሐሰት በሉ**

1. እውነት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. እውነት

## መልመጃ ስድስት

**ማዛመድ**

1. ሠ
2. ሀ
3. ሰ
4. ለ
5. ሐ
6. መ

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ ስምንት

ቃላት ማደን

2. አረንጓዴ
3. እርከን
4. ችግኞች
5. ድርቅ
6. ተሞክሮ

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

## መልመጃ አስር

**ለ. የብዙ ቁጥር ስሞችን መፃፍ**

1. ዛፎች
2. መፅሐፎች፣ መፃህፍት
3. ቦታዎች
4. ከብቶች
5. ሀገሮች፣ ሀገራት

## መልመጃ አስራ አንድ

**ሐ. የነጠላ ቁጥር ስሞችን መፃፍ**

1. አካባቢ
2. ቃል
3. ችግር
4. መምህርት፣ መምህር
5. ሐረግ

# ምዕራፍ ስድስት

# አደንዛዥ ንጥረነገሮች (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-
- አደገኛ ዕፆችን ማስወገጃ መንገዶችን በተመለከተ አዳምጠው ይረዳሉ፤
- የቀረበላቸውን ጽሁፍ አውድ ይተነብያሉ፤
- አንድን ጽሁፍ ለመረዳት ምልክቶችን፣ መግለጫዎችንና ወካዮችን ያነባሉ።
- የዓረፍተነገር መሸጋገሪያዎችን ይገነዘባሉ፤
- ቃላትን ያጎለብታሉ፤ ፍቾቻቸውን ይናገራሉ፡፡

## 2. የትምህርቱ ይዘቶች

### 2.1 ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መመለስ
- የተነበበላቸውን ምንባብ አዳምጠው ፍሬሀሳቡን መናገር

### 2.2 ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- በቃል ውስጥ ያሉትን ቀለሞችን መለየት
- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች በቃል መልስ መስጠት
- ንጥረነገሮች የሚያደርሷቸውን ጉዳቶች ዘርዝሮ መናገር
- የቀረቡትን መልመጃዎች ሰርተው በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻቸው በቃል መናገር

### 2.3 ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- ቅድመንባብ ጥያቄዎችን በቃል መመለስ
- ምንባቡን በግል አንብበው የጫትን ጥቅምና ጉዳት መግለጽ

### 2.4 ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መመለስ
- በተሰጡት ሀሳቦች ላይ በመወያየት ዋና ዋና ነጥቦችን መጻፍ
- በቡድን ሆነው እየተነጋገሩ ማስታወሻ መያዝ
- በተሰጠው መነሻ ሀሳብ መሠረት አጫጭር ጽሁፎችን መጻፍ
- በአንቀጽ ውስጥ ያሉትን ሐረጋት የአገባብ ፍቾቻቸውን መጻፍ

## 2.5 ትምህርት አምስት፡ቃላት

- ከምንባቡ ለወጡ የተለያዩ ቃላት የመዝገበቃላት ፍች መጻፍ
- ለቃላት ተቃራኒ ፍች መስጠት
- ለቃላት መዝገበቃላዊ ፍች መስጠት
- የተሰጡትን ቃላት በተገቢ ቦታ በማስገባት የተስተካከለ አንቀጽ መጻፍ

## 2.6 ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

- በተሰጠው ማስታወሻ መሠረት የዓረፍተነገር መሸጋገሪያዎችን መለየት
- የዓረፍተነገር መሸጋገሪያዎችን መጠቀም

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ተማሪዎች በንባብ ወቅት የገጠሟቸውን አደናጋሪ ጉዳዮች በተመለከተ ተጨማሪ ገለፃ ከመጠየቅ እንዳይታቀቡ ማበረታታት፣
- ተማሪዎች በቀጥታ ለተገለፁ ቀጥተኛ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ፣
- ድህረ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማድረግ፣
- አንቀፅ ሲፅፉ የተማሯቸውን መሸጋገሪያ ምዕላዶች፣ አያያዥ ቃላት እና ሀረጋትን እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
- ለቃላት አውዳዊ ፍች ለመስጠት ምንባቡን በአሰሳ እንዲያነቡ ማድረግ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄቹን አስቀድመው በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጉ። ከዚያም በቃል እንዲመልሱ ዕድል ይስጧቸው። ጥያቄዎቹን በመመለስ ላይ ሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ ማድረግ ስላለባቸው ከሁሉም መልስ ይቀበሉ። እርስዎም ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

በቅድሚያ "ትምባሆ ማጨስ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ያንብቡላቸው። በመካከል ንባብዎን ገታ ያድርጉና የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ዕድል ይስጧቸው። በተማሪዎች ምላሽ ተገቢውን አስተያየት ከሰጡ በኋላ ምንባቡን ካቆሙበት ጀምሮ እስከመጨረሻው ያንብቡላቸው።

## ትምባሆ ማጨስ

ትምባሆ **ሱስ በማስያዝ** በሰዎች ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ **እጾች** አንዱ ሲሆን ጎጂ ንጥረነገሮች ይዟል። እነዚህ ንጥረነገሮች ብዛት ያላቸው ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ **ኒኮቲን፣ ካርቦንሞኖኦክሳይድና ታርም** በመባል ይታወቃሉ። ኒኮቲን በትምባሆ ውስጥ የሚገኝ ንጥረነገርና ትምባሆ የሚያጨስን

ሰው ሱስ የሚያስይዝ ነው። ካርቦን ሞኖኦክሳይድ ደግሞ በትምባሆ ውስጥ የሚገኝ ሆኖ በሰው ላይ ጉዳት የሚያደርስ ነው። ታርም እንደኒኮቲንና ካርቦንሞኖኦክሳይድ በሚጨስ ትምባሆ ውስጥ የሚገኝ ሆኖ ጉዳት የሚያደርስ ነው። እነዚህ ንጥረነገሮች ወደ ሰውነት የሚገቡት በአብዛኛው ትምባሆን በማጨስ ነው።

በትምባሆ ውስጥ ያሉት ንጥረነገሮች በሰው ላይ የሚደርሷቸው ጉዳቶች በርካታ ናቸው። ለምሳሌ የልብ ምትና የደም ግፊትን ይጨምራል። ከዚህም ሌላ ጡንቻዎች እንዲጣበቡና አጥንቶች እንዲላቀቁ ያደርጋል። እንደዚሁም ጨጓራ ፈሳሽ አሲዶችን በብዛት እንዲያመነጭና አእምሯችን በትክክል እንዳይሰራ በማድረግ የአካላችንን ሥርዓት ያቃውሳል። በመሆኑም ትምባሆን በማንኛውም መልክ መጠቀም በመተው ራስን ከጉዳት መጠበቅ ያሻል።

(ት/ሚኒስቴርና ኦ/ት/ቢ.ሮ፣Afaan Oromoo፣የተማሪ መጽሐፍ፣7ኛ ክፍል ተተርጉሞና ለክፍሉ እንዲመጥን ተደርጎ የቀረበ)

### ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

በዚህ ስር ካዳመጡት ጽሁፍ የተረዱትን ለመገምገም በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹንም በቡድን እንዲሰሩ ያድርጉ። ከዚያም ጥያቄዎቹን በትክክል መመለሳቸውን ተገቢ አስተያየት በመስጠት ያረጋግጡላቸው።

### ክፍለጊዜ ሦስት

## ተግባር አንድ

በዚህ ተግባር ስር ሁለት ጥያቄዎች ቀርበዋል። በትዕዛዙ መሠረት ተማሪዎች በጥያቄዎቹ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ። ተማሪዎችም ሲወያዩ እየተዘዋወሩ ተገቢውን ድጋፍ ያድርጉላቸው። በመጨረሻም በቡድን ተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች የተስማሙበትን ሀሳብ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። እርስዎም ገንቢ አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አራት

### መልመጃ ሁለት

በዚህ ስር ለቃላት አውዳዊ ፍች እንዲሰጡ ታዘዋል። በቅድሚያ መልመጃውን ለማሰራት ቃላቱን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው። ከዚያም ጽሁፉን አንድ ጊዜ በተገቢው ፍጥነት ያንብቡላቸው። ከዚያም ለተሰጡት ቃላት አውዳዊ ፍች እንዲጽፉ ያድርጉ። ደብተራቸውንም በመሰብሰብና በማረም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው።

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ተግባር ሁለት

በዚህ ስር ሁለት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን እንደአጠያየቃቸው ተገቢውን ምላሽ አዘጋጅተው በቃል እንዲናገሩ ያድርጉ። ገንቢ አስተያየትም ይስጧቸው።

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

ለትምህርቱ መግቢያ እንዲሆንዎት ተማሪዎቹ መማሪያ መጽሃፋቸው ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በመጠቀም ተማሪዎቹን ያነሳሷቸው። በጥያቄዎቹ ላይ ተወያይተው ምላሻቸውን በቃል እንዲሰጡ ያድርጉ። እርስዎም ለተማሪዎች ምላሽ ገንቢ አስተያየት ይስጧቸው። ቀጥሎም ከመጽሐፋቸው ላይ ያለውን ምንባብ ተረጋግተው እንዲያነቡ ያድርጉ።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

እነዚህን በሚመለከት የምንባቡን የመጀመሪያ ሁለት አንቀጾች ካነበቡ በኋላ ንባባቸውን ገታ በማድረግ በጥያቄዎቹ ላይ የግላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ያድርጉ። እርስዎም ተገቢውን አስተያየት ከሠጡ በኋላ ንባባቸውን እንዲቀጥሉ ያድርጉ።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**መልመጃ ሦስት**

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ያንብቡላቸውና ምላሹን በቃል እንዲሰጡ ያድርጉ። ተገቢውን ግብረመልስም ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ ስምንት**

በ "ለ" ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች በሚመለከት ምንባቡን መሰረት በማድረግ እውነት/ሐሰት እያሉ በምክንያት አስደግፈው በጽሁፍ እንዲመልሱ የታሰበ ነው። በመሆኑም መልመጃውን በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ያድርጉና ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ግብረመልስ ይስጧቸው።

# ትምህርት አራት፡ መፃፍ

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## ተግባር ሦስት

በ "ሀ" ስር ያለውን ተግባር ለማሰራት ተማሪዎችን በቡድን ያደራጇቸውና በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ። ከዚያም ተወያይተው የደረሱበትን ድምዳሜ በማስታወሻ ደብተራቸው

ላይ እንዲጽፉ ይዘዟቸው። ሞዴል የሚሏቸውንም ስራዎችን መርጠው በቡድን ተወካያቸው አማካኝነት በንባብ እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

### ክፍለጊዜ አስር

በ "ለ" ስር በቀረቡት የመነሻ ሀሳቦች ላይ አጫጭር ጽሁፎች አዘጋጅተው እንዲያርቡ ታዘዋል። በዚህም መሠረት መነሻ ሀሳቦቹን መሠረት አድርገው አጫጭር ጽሁፎች እንዲጽፉ ይንገሯቸው። ከዚያም የጻፉትን እንዲያቀርቡ ያድርጉና በጽሁፋቸው ላይ ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።ተግባሩንም በክፍለጊዜው እንዲሰሩ ይንገሯቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አንድ

### መልመጃ አራት

በዚህ ስር ተማሪዎች በመማሪያ መጽሃፋቸው ላይ የቀረበውን ጽሁፍ በማንበብ በጽሁፉ ውስጥ ያሉትን መሸጋገሪያ ቃላትን ሀረጋት እንዲለዩ ታዘዋል። በመሆኑም ጽሁፉን እያነበቡ መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ለይተው እንዲጽፉ ያድርጉ። ከዚያም ተገቢውን ግብረመልስ ደብተራቸውን በማረም ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ተግባር አራት

ተግባር አራት በሚመለከት የተሰጠውን ሀይለቃል የሚዘረዝሩ ዓረፍተነገሮች መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋት በመጠቀም አንቀጽ እንዲጽፉ የታዘዙ ስለሆነ በዚሁ መሠረት አንቀጹን እንዲጽፉ ያድርጉ። በትክክል ስለመጻፋቸውም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው።

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### ክፍለጊዜ አስራ ሦስት

በ "ሀ" ስር በቀረቡት አስር ቃላት በግላቸው ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ። ከዚያም የመሰረቷቸውን ዓረፍተነገሮች በማረም ተገቢ የሆነ ግብረመልስ ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አራት

በ "ለ" ስር የቀረቡትን ቃላት ተጠቅመው የተጓደለውን አንቀጽ እንዲያሟሉ ታዘዋል። ስለሆነም ከቀረቡት ቃላት እየመረጡ ክፍት ቦታዎቹን እንዲያሟሉ በማድረግ አንቀጹን ይጻፉ። ከዚያም ተገቢ ግብረመልስ በጽሁፍ ይስጧቸው።

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

### መልመጃ ስድስት

በዚህ ስር የተዘረዘሩትን ቃላት ስምና ግስ እያሉ እንዲለዩ መልመጃ ቀርቧል። ስለሆነም ቃላቱን ስምና ግስ እያሉ እንዲመድቡ ያድርጉ።ትክክለኛነታቸውንም ያረጋግጡላቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

በዚህ ስር ከቀረበው አንቀጽ ውስጥ ስምና ግስ የሆኑትን ቃላት እንዲለዩና በቃላቱም ዓረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ታዘዋል። ስለሆነም በቅድሚያ ስምና ግስ የሆኑትን ቃላት ከለዩ በኋላ ዓረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ያድርጉ። በትክክል መስራታቸውንም አረጋግጠው ገንቢ አስተያየት ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ ሰባት

በዚህ ስር ተማሪዎች በሳጥን ውስጥ ከቀረቡት ስሞች መርጠው የተጓደሉ ዓረፍተነገሮችን እንዲያሟሉ ታዘዋል።በዚህ መሠረት የመጀመሪያውን ጥያቄ ምሳሌ ይስጧቸውና ሌሎቹን ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ያሰሯቸው። ከዚያም ደብተራቸውን በማረም ትክክለኛውን ግብረመልስ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

በ “ለ” ስር የተጓደሉ ዓረፍተነገሮችን ሊያሟሉ የሚችሉ ግሶችን ከራሳቸው ፈልገው እንዲጽፉ ታዘዋል። ስለሆነም የመጀመሪያውን ዓረፍተነገር ይሰሩላቸውና ሌሎቹን እንዲያሟሉ ያድርጉ።ትክክለኛውን ግብረመልስ ደብተራቸውን በማረም ይስጧቸው።

## መርጃ መሳሪያዎች

- ሱስ አስያዥ የሆኑ ዕጾችን የሚያሣይ ስዕላዊ መግለጫ
- ስምና ግስ የሆኑ ቃላት የተጻፉባቸው ፍላሽ ካርዶች

## ግምገማ

- የማዳመጥ ተግባሮችን በትክክል መስራታቸውን ማረጋገጥ፣
- የመናገር ተግባራትን በትክክል መስራታቸውን ማረጋገጥ፣
- የማንበብ ተግባሮችን በትክክል መተግበራቸውን ማረጋገጥ፣
- ተማሪዎች የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ካርዶች በማውጣት ለጥያቄዎች የተለያዩ ምላሾችን መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣

- መነሻ ሀሳቦችን ተጠቅመው አጫጭር ጽሁፎችን መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- በአንቀጽ ውስጥ የሚገኙ መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ለይተው መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- ለቃላት አውዳዊ ፍች መስጠት መቻላቸውን መመልከት፣
- ቃላትን በስምና ግስ የቃል ክፍል መመደብ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

# በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. ለቃላት አውዳዊ ፍች መስጠት**

1. ያናጋል
2. እንዲፈጥር
3. ትርታ
4. በጭስ መልክ የሚሳብ
5. ልምድ
6. ማስለመድ
7. ተክሎች
8. ቅመሞች

### መልመጃ አንድ

**ለ. ቃላትን በቀለም መከፋፈል**

1. ጎ-ጂ
2. ኣ-ሳ
3. ኣ-ፍ
4. መ-ን-ገ-ድ
5. መ-ን-ግ-ስ-ት
6. ኣ-በ-ባ
7. ል-ብ-ስ

### መልመጃ ሶስት

**ለ. እውነት/ ሀሰት ጥያቄዎች**

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. ሐሰት

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

### መልመጃ አራት

**ከአንቀጽ ውስጥ መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን መለየት**

- ይህም
- በተለይም

- በተጨማሪም
- እንዲሁም
- ከዚህም ባሻገር

# ትምህርት አምስት

## ለ. ቃላትን በመጠቀም አንቀጽ ማሟላት

1. ከቆሻሻ
2. ጤንነት
3. ጥርግራጊ
4. መውረጃ
5. ቅር
6. ፍሳሽ
7. ቢንጣለል

# ትምህርት ስድስት፤ ሰዋስው

መልመጃ ሰባት

## 4. ሀ. በሳጥን ውስጥ የቀረቡትን ስሞች በመምረጥ ዓረፍተነገሮችን ማሟላት

1. መጽሐፍ
2. ዝሆን
3. ኮምፒውተር
4. ዴዴሳ
5. አምፖል

# ምዕራፍ ሰባት

## ምግብ (የክፍል ጊዜ ብዛት 18)

## የሚጠበቁ ውጤቶች

### ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- አስረጅ ጽሁፎችን አዳምጠው ይረዳሉ፤
- ሥርዓተ ነጥቦችን ለይተው በማወቅ ይጠቀሙባቸዋል፤
- ተገቢ ፊደላትን ተጠቅመው ይጽፋሉ፤ ሥርዓተ ነጥቦችን በቦታቸው ይጠቀማሉ፤
- ሂደታዊ ትንተና አንቀጽን ይረዳሉ፤
- ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ለማንበብ የምዕላዳዊ ትርጉሞችን እውቀት ይጠቀማሉ።

## 5. የትምህርቱ ይዘቶች

### 2.1 ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ።
- የተነበበላቸውን ምንባብ አዳምጠው ፍሬ ሀሳቡን ይናገራሉ።
- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።

### 2.2 ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- ምንባቡን አዳምጠው ስለምግብ ጠቀሜታ ይናገራሉ።
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄችን በምንባቡ መሰረት በቃልይመልሳሉ።

### 2.3 ትምህርት ሦስት፡ማንበብ

- ምንባቡን በግል ያነባሉ።

### 2.4 ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች በጽሁፍ ይመልሳሉ።
- የተሰጧቸውን ምሳሌዎች ተከትለው አጫጭር አንቀጾችን ይጽፋሉ።
- ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው አስገብተው ይጽፋሉ።

### 2.5 ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ቃላትን ያነባሉ።
- ለቃላት የተለያዩ ፍችዎች ይሰጣሉ።
- ቃላትን በተገቢ ቦታቸው አስገብተው አንቀጾችን ያሟላሉ።

## ትምህርት ስድስት ፡ ሰዋስው

- የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞችን ይለያሉ።

## 6. የማስተማሪያ ዘዴ

- ተማሪዎች ስለርዕሰ ጉዳዩ አስቀድመው የሚያውቁትን ለጓደኞቻቸው እንዲያጋሩ ማድረግ፣
- ተማሪዎች ምን መማር እንደሚፈልጉ እንዲናገሩና በመጨረሻም ምን እንደተማሩ እየከለሱ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
- የዋና ሀሳብ መግለጫ ሰንጠረዥና ዝርዝሮቹ ስለምን እንደሆኑ እንዲመልሱ ማድረግ፣
- ዋና ዋና የታሪኩን ሁነቶች እንዲመዘግቡ ማድረግ፣
- ሁለት ነገሮችን በማወዳደርና በማነፃፃር እንዲገልጹ ማድረግ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ትምህርቱ የሚሰጠው የተማሪን ተሳትፎ በሚጠይቅ መልክ ስለሆነ በእያንዳንዱ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎቹ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያበረታቷቸው። መጀመሪያ የእለቱን ትምህርት ርዕስ ይንገሯቸው። ከዚያም የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸውና የቀደመ ዕውቀታቸውን ይቀስቅሱ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ቀጥሎ ያለው ለዚህ ክፍል ማስተማሪያ ይሆን ዘንድ የቀረበ ስለሆነ ራስዎ ያንብቡላቸው። መሃል ላይ እንደደረሱ ንባብዎን ቆም አድርገው የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። በመቀጠልም ምላሻቸውን ተቀብለው ገንቢ አስተያየት ይስጧቸው።

## ውሃ

ውሃ ምግብ በመሆኑ የተለያዩ ጥቅሞች አሉት። ከነዚህም ውስጥ ምግቦችን በማዋሃድ ለሰውነት ጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል። የሰውነት ሙቀት ከአካባቢው አየር ጋር እንዲጣጣም ያደርጋል። የሰውነት ቆዳ የአካባቢውን አየር ሙቀትና ቅዝቃዜ እንዲቋቋም ያግዛል። ከዚህም ሌላ የቆዳ

ውበትን ለመጠበቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። የእንቅልፍ መጫጫንን፣ የራስ ምታትን፣ በንባብ ጊዜ ትኩረት ማጣትን ውሃ በመጠጣት ማስወገድ ይቻላል።

ሰዎች ለውሃ ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ውኃ መጠጣት ያወፍራል፤ የደም ግፊትን ያስከትላል፣ በማለት ውሃ ከመጠጣት ይቆጠባሉ። ሆኖም የደም ግፊት ውሃ ከመጠጣት የሚመጣ ችግር አይደለም። እንዲያውም ለደም ግፊት መንስዔ የሚሆኑትን፣ በደም ስር ውስጥ የሚጋገሩትንና የደም ስር ጥበትን የሚያስከትሉትን ያስወግዳል። ምግብ ሳይበላ ሲቆይ የአፍ ጠረን ለውጥ ስለሚፈጠር ውሃ በመጠጣት ችግሩን ማስወገድ ይቻላል። አእምሮ ንቁ እንዲሆን፣ የደም ዝውውር እንዲቀላጠፍ ውሃ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ከዚህም ሌላ ውሃ የምግብ እንሽርሽሪት እንዲጎለብት፣ ተክለ ቁመና እንዲስተካከልም ይረዳል። በተጨማሪም አላስፈላጊ ጎጂ ንጥረነገሮች እንዲወገዱ፣ የቆዳ ውበት እንዲጠበቅና ሌሎች ለሰውነት የሚጠቅሙ ሂደቶች እንዲቀላጠፉ ውሃ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል። በመሆኑም በየቀኑ ከሰባት እስከ ስምንት ብርጭቆ ውሃ መጠጣት እንዳለብን ባለሙያዎች ይመክራሉ።

(ብርሃኑ ገ/ፃድቅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መመሪያ፣ 2003 ላይ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)

## ክፍለጊዜ ሁለት

# የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

በተማሪው መጽሀፍ በመልመጃው የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሁፉ መሰረት በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። በምላሻቸው ላይ ተገቢውን አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉ።

## ክፍለጊዜ ሦስት

## መልመጃ ሁለት

በ “ሀ” ስር የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹ የሚሰሩት ቀደም ሲል በአዳመጡት ጽሁፍ መሠረት እንደሆነ ይንገሯቸው። ከዚያም ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ ገልብጠው በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ያድርጉ። ሰርተው የጨረሱትን ተማሪዎች ደብተር በማረም ግብረመልስ ይሥጧቸው።

## ክፍለጊዜ አራት

በዚህ ስር በተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ ላይ ምሳሌውን ተመልክተው የቀረቡትን ሀሳቦች ተጠቅመው እንዲያወዳድሩና እንዲያጻጽሩ የሚጠይቅ ነው። ስለዚህ ከተሰጡት ሀሳቦች ውስጥ አንዱን መርጠው በግላቸው በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ያድርጉ። ዕገዛ የሚፈልጉ ተማሪዎችንም

ይርዷቸው። በመጨረሻም የጻፉትን እንዲያቀርቡ ያድርጉና ገንቢ አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

ተግባሩን በሚመለከት የምግብ ባለሞያ ወይም ሌላ ሰው ስለውኃ ጠቀሜታ እንዲጠይቁና ያገኙትን ሀሳብ በክፍል ውስጥ ተራ በተራ ለጓደኞቻቸው እንዲናጋሩ ያድርጉ። በሀሳባቸው ላይ አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ ስድስት

### ተግባር ሁለት

በዚህ ክፍለጊዜ ስር ተማሪዎች ስለውኃ ጠቀሜታ በቡድን እንዲወያዩ የታዘዙ ስለሆነ ተግባሩን በንቃት እንዲያከናውኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው። ከዚያም በቡድን ተወካያቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፤ ተገቢ አስተያየትም ይሥጧቸው።

### ክፍለጊዜ ሰባት

### ተግባር ሦስት

በዚህ ስር በተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ ላይ ምሳሌውን ተመልክተው በቀረቡት መነሻ ሀሳቦች ተጠቅመው ተራ በተራ እንዲናገሩ የታዘዙበት ነው። ስለዚህ በተሰጡት ሀሳቦች ላይ ተመርኩዘው ተራ በተራ እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው። ዕገዛ የሚፈልጉ ተማሪዎችንም ይርዷቸው። በመጨረሻም ገንቢ አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ ስምንት

### ተግባር አራት

በዚህ ስር የውይይት መመሪያን ተከትለው በቀረበላቸው የመወያያ ርዕስ ላይ በቡድን ሆነው እንዲወያዩ ታዘዋል። በዚህም መሠረት በርዕሱ ላይ ውይይት እንዲያደርጉ ሁኔታውን ያመቻቹላቸው። ከዚያም ተወያይተው የተስማሙበትን ድምዳሜ ለክፍል ተማሪዎች በተወካያቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ። አስፈላጊ የሆነ አስተያየትም ይስጧቸው።

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

### ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

በቅድሚያ ከንባብ በፊት የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው ቅድመንባብ ጥያቄዎችን በቡድን ተወያይተው በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። እርስዎም በጥያቄዎቹ ላይ አስተያየት ይስጡባቸው። ከዚያም የቀረበውን ምንባብ በየግላቸው እንዲያነቡ ይዘዟቸው።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ሁለተኛውን አንቀፅ አንብበው እንደጨረሱ ንባባቸውን ገታ አድርገው የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጉ። እርስዎም በተራዎ ምንባቡን እያነበቡ ይግለጹላቸው። አዳዲስ ቃላትንም ይተርጉሙላቸው።

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በደብተራቸው ላይ እንዲሰሩ ይዘዟቸው። ከዚያም የጋራ የሆነ መልስ ከተማሪዎችዎ ጋር በመስራት ትምህርቱን ያጠቃልሉ።

### ክፍለጊዜ አስር

በፊደል "ለ" ስር ያሉትን የእውነት /ሐሰት አምስት ጥያቄዎች በቡድን ተወያይተው በምክንያት አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጉ። እርስዎም የራስዎን አስተያየት በመስጠት የመልሳቸውን ትክክለኛነት ያረጋግጡላቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አንድ

በ "ሐ" ስር በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የምግብ አይነቶችን ዘመናዊ ወይም ባህላዊ በማለት እንዲመድቡ ታዘዋል። በመሆኑም ሰንጠረዡን ላይ በመገልበጥ በታዘዙት መሠረት ተግባሩን እንዲያከናውኑ ያድርጉ። ከዚያም የተማሪዎችን ደብተር በማረም በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡላቸው። ተግባር አምስትንም በትዕዛዙ መሠረት እቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ይዘዟቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

በዚህ ስር በክፍለጊዜ አስራ አንድ የተሰጣቸውን የቤት ስራ በሚመለከት ጽፈው ያመጡትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጉ። እርስዎም በሰሩት ስራና በአቀራረባቸው ላይ ተገቢውን አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉ።

### ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

### መልመጃ አራት

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያደርጉ መልመጃዎችና ስርዓተነጥቦችን የተመለከተ ማስታወሻ ቀርቧል። ስለዚህ መልመጃውን ከማሰራትዎ በፊት በማስታወሻው ላይ ገለጻ ያድርጉላቸው። ከዚያም በክፍለጊዜው ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ እንዲሰሩ ይዘዟቸው። ደብተራቸውንም ሰብስበው በማረም ተገቢ የሆነ ግብረመልስ ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ተግባር ስድስት

በዚህ ስር በተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ምሳሌ መሠረት አድርገው አንቀጽ እንዲጽፉ ታዘዋል። በዚህም መሰረት ከተሰጡት ርዕሶች አንዱን በመምረጥ አንቀጽ እንዲጽፉ ያድርጉ። ከዚያም የጻፉትን አንቀጽ በመመልከት ተገቢ አስተያየት በጽሁፍ ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### መልመጃ አምስት

በዚህ ስር ምዕላዶችን/ቅጥያዎችን/ በሚመለከት የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማዳበር የሚያስችል መልመጃ ተሰጥቷል። ስለምዕላዶች ቀደም ሲል የተማሩትን ያስታውሷቸውና በተሠጠው ምሳሌ መሰረት ቃላትን እንዲያፈልቁ ያበረታቷቸው። መልመጃውንም በክፍል ውስጥ ያሰሯቸው። ተገቢ ግብረመልስም ይሥጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

በ "ለ" ስር መዝገበቃላዊ ፍች ፈልገው ዓረፍተነገር የሚመሰርቱባቸው ቃላት ተሰጥተዋል። በመሆኑም መልመጃውን አስቀድመው የቤት ስራ በመስጠት እንዲሰሩና በክፍለጊዜው ሰርተው ያመጡትን በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ከዚያም በቀረበው ስራ ላይ ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

## ክፍለ ጊዜ አስራ ሰባት

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

## መልመጃ ስድስት

በዚህ የትምህርት ክፍል ከተማሪዎች የሚጠበቀው የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞችን መለየት ነው። ለትምህርቱ አሰጣጥ እንዲረዳ አጠር ያለ ማስታወሻ ከውስን ምሳሌዎች ጋር ተሰጥቷል። ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው ምሳሌዎቹን ተከተለው ስሞቹን የሚቆጠር፣ የማይቆጠር ብለው ለይተው መጻፍ ነው። እርስዎም በዚሁ መሰረት ማሰራት አለብዎት።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

በ "ለ" ስር ተማሪዎች የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞች ብለው አምስት አምስት ቃላት እንዲጽፉ የታዘዙ ስለሆነ በዚሁ መሠረት በክፍለ ውስጥ መልመጃውን ያሰሯቸው። ከዚያም ተገቢውን ግብረመልስ ይሥጧቸው።

## መርጃ መሳሪያ

የተለያዩ የምግብ አይነቶችን የሚያሣዩ ስዕላዊ መግለጫዎች

## ግምገማ

- የማዳመጥ ተግባሮችን በትክክል መስራታቸውን ማረጋገጥ፣
- ሀሳቦችን በማወዳደርና በማነጻጸር መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የንግግር መመሪያ ተከትለው ንግግር ማድረግ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የማንበብ ተግባሮችና መልመጃዎችን በትክክል መስራታቸውን ማረጋገጥ፣
- በጽህፈት ውስጥ ተገቢ የሆኑ ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- አንቀጽ መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

# በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

## መልመጃ ሁለት

**ሀ. ምርጫ**

1. ሐ
2. ለ
3. ሀ
4. ሀ

## መልመጃ ሶስት

**ለ. እውነት/ሀሰት**

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት

**ሐ. ምግቦችን ዘመናዊና ባህላዊ በሚል ስር መመደብ**

| | |
|---|---|
| ገንፎ | ባህላዊ |
| የተወቀጠ ኑግ | ባህላዊ |
| የዱባይ ዘይት | ዘመናዊ |
| ገብስ ቂጣ | ባህላዊ |
| የባቄላ ንፍሮ | ባህላዊ |
| ጨጨብሳ | ባህላዊ |
| የታሸገ ዱቄት | ዘመናዊ |
| አጥሚት | ባህላዊ |
| ጭብጦ | ባህላዊ |
| የታሸገ የድንች ጥብስ | ዘመናዊ |
| የተቀቀለ ድንች | ባህላዊ |
| እንጀራ | ባህላዊ |

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ አምስት

**ሀ. ምዕላዶችን በቃላት ላይ በማስጠጋት አዳዲስ ቃላት መመስረት**

1. ዓይናማ፣ ብርማ፣ ቡናማ---
2. ሆዳም፣ አገጫም፣ ልባም---
3. ሁነኛ፣ ወገኛ፣ ብቸኛ---
4. ሰውነት፣ ልጅነት፣ ጅልነት---
5. መጋገሪያ፣ መባረኪያ፣ መዘፍዘፊያ---
6. ፈጣሪ፣ ዘማሪ፣ ገባሪ--

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ሀ. የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞችን መለየት**

| | |
|---|---|
| አገር | የሚቆጠር |
| ዱቄት | የማይቆጠር |
| ልጅ | የሚቆጠር |
| ዘይት | የማይቆጠር |
| ገበሬ | የሚቆጠር |
| ውሃ | የማይቆጠር |

# ምዕራፍ ስምንት

## የዱር እንስሳት (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- የተማሯቸውን ውስብስብ የቀለም መዋቅሮች እንዴት እንደሚያጣምሩ አዳምጠው ይረዳሉ።
- ውስብስብ የቃላት መዋቅሮችን ያነባሉ።
- አንቀጽን በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት ተረድተው ይጽፋሉ።
- የስነምዕላዳዊ ፍች እውቀታቸውን ይጠቀማሉ።
- ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን ይጠቀማሉ።

**7. የትምህርቱ ይዘቶች**

### 2.1 ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መመለስ
- በአካባቢያቸው ያሉትን የዱር እንስሳት ስሞችን ዘርዝረው ጥቅምና ጉዳታቸውን መለየት
- የተነበበላቸውን ምንባብ አዳምጠው ፍሬሀሳቡን መናገር

### 2.2 ትምህርት ሁለት፡መናገር

- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች በቃል መልስ መስጠት
- በቡድናቸው በመሆን ስጋ-በል እና እፀ-በል የሆኑትን እንስሳት በመለየት ስለአካላቸውና ባህሪያቸው ተጠያይቀው በየተራ ለክፍሉ ተማሪዎች ማስረዳት
- የቀረቡትን መልመጃዎች ሰርተው በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻቸው በቃል ማስረዳት

### 2.3 ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

- ቅድመንባብ ጥያቄዎችን በቃል መመለስ
- ምንባቡን በግል አንብበው የዱር እንስሳትን ዓይነትና ባህርይ መናገር

### 2.4 ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄችን በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መመለስ
- በተሰጧቸው ሀሳቦች በመወያየት ዋና ዋና ነጥቦችን መጻፍ
- በተሰጧቸው መነሻ ሀሳቦች ላይ ተመስርተው አንቀጾችን በማወዳደርና በማነጻጸር

መጻፍ

- የተሰጧቸውን መነሻ ሀሳብ ተከትለው አጫጭር ጽሁፎችን ማዘጋጀት
- የተሰጧቸውን ቃላት ቅርጾቻቸውን በመቀያየር አረፍተነገሮችን መመስረት

## 2.5 ትምህርት አምስት፡ቃላት

- ከምንባቡ የወጡ የተለያዩ ቃላትን የመዝገበ ቃላት ፍች መጻፍ
- ቃላትን በምዕላድ በመከፋፈል ቅጥያዎችን መለየት
- የተሰጧቸውን ቃላት በተገቢ ቦታ በማስገባት የተስተካከለ አንቀጽ መጻፍ
- ቃላትን መመስረት

## 2.6 ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

- በማስታወሻው እየተረዱ ተሻጋሪ እና የማይሻገሩ ግሶችን መለየት
- ዓረፍተነገሮችን አንብበው ተሻጋሪና ኢተሻጋሪ በማለት መለየት

## 8. የማስተማሪያ ዘዴ

- የማዳመጥ ተግባሮችን ክንውን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- የመናገር ተግባሮችን ክንውን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- የማንበብ ተግባሮችን ክንውን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- የመጻፍ ተግባሮችን ክንውን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- የቃላት ዕውቀታቸውን እንዲያሰፉ ቃላትን በተለያዩ ዘዴዎች ማስተማር
- ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን እንዲለዩ ማድረግ
- ቃላትን በተለያዩ ቅርጾች እንዲያረቡ ማድረግ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**ክፍለጊዜ አንድ**

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

በዚህ ስር ተማሪዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን ለመቀስቀስ በቀጣይ የሚያዳምጡትን ጽሁፍ እንዲተዋወቁ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ተማሪዎቹ በጥያቄዎቹ ላይ በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጉና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው። እርስዎም የራስዎን አስተያየት ያክሉበትና በቀጣይ ያለውን ጽሁፍ ያንብቡላቸው።

የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በተመለከተ ጽሁፉ በሚነበብበት ጊዜ ተማሪዎች ምላሹን መስራት እንዲችሉ አስቀድመው ጥያቄዎችን በጥቁር ይጻፉላቸው። ጽሁፉንም ዝግ ባለ ፍጥነት ያንብቡላቸው። ጥያቄዎቹንም በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ።

# ስጋ በል የዱር እንስሳት

ስጋ በል እንስሳት አብዛኛውን ጊዜ የሚታወቁት በአስፈሪነታቸው ነው። መብላት የሚፈልጉትን እንስሳ አድፍጠው አለበለዚያም ከፍ ባለ ፍጥነት አሳደው በመያዝ አንገታቸውን ቆልምመው፣ ጉሮሮአቸውን አንቀው፣ ደም ስራቸውን በስተው መላ አካላቸውን በስል ጥፍሮቻቸውና ሹል ጥርሳቸው ገሽልጠው ይበሏቸዋል። አንዳንዴ ሰለባው ሳይሞት ከነሕይወቱ አብዛኛው አካሉ ተግጦ ያልቃል። ስለሆነም ስጋ በል እንስሳት ብዙውን ጊዜ የሚታወቁት በአውሬነታቸው ቢሆንም እንደማንኛውም እንስሳ መታየት አለባቸው።

ስጋ በል የዱር እንስሳት ከሳር በል እንስሳት ጋር ሲወዳደሩ፣ አካላቸው በአብዛኛው በክብደትም ሆነ በመጠን አነስተኛ ነው። ሀይለኛ የሚባሉት ስጋ በል እንስሳት አንበሳ እና ነብር ሲሆኑ፣ እነሱም በአካላቸው መጠን ሳር በል ከሆኑት ከዝሆን፣ አውራሪስ፣ ጉማሬ እና ቀጭኔ ሊወዳደሩ አይችሉም። ለመቧጠጫና ለመገሽለጫ የሚያገለግሏቸው ጠንካራ ጥፍርና በከፍተኛ ፍጥነት የመሮጥ ችሎታ አላቸው። ከሳር በል እንስሳት ሻል ያለም ብልህነት ያላቸው ይመስላል። ይህ ብልህነት ሰለባቸውን አዘናግተው ለመያዝ ያስችላቸዋል።

ስጋ በል እንስሳት ከልጅነት ጀምሮ እርስ በርስ በመጫወት ሰለባን አባሮና አድፍጦ በልዩ ልዩ ዘዴ እያዘናጉ የመያዝ ችሎታቸውን ያዳብራሉ። ስጋ በሎች ከሩቅ የማሽተትና የመስማት ክህሎታቸው የላቀ ነው። ስማቸው እንደሚያሳየው ስጋ በሎች ምግባቸው ስጋ ይሁን እንጂ አብዛኞቹ እፀዋትንም ይመገባሉ።

ስጋ በል እንስሳትን አናሳና ከፍተኛ በማለት በሁለት መደቦች ከፍለው የሚያዩ ወገኖች አሉ። ከፍተኛ ስጋበሎች አብዛኞዎቹ ድመት አስተኔ ሲሆኑ አናሳዎቹ በአብዛኛው ውሻ መሳይ ናቸው።

### ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

በ “ሀ” ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎች ባዳመጡት ጽሁፍ መሠረት እንዲመልሱ ያድርጉ። እርስዎም የግል አስተያየትዎን ይሥጡና ትምህርቱን ያጠቃልሉ።

### ክፍለጊዜ ሶስት

በ “ለ” ስር የቀረቡትን የእውነት/ሀሰት ጥያቄዎች በቀረበው ጽሁፍ መሠረት በክፍል ውስጥ ተወያይተው በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። የመልሳቸውን ትክክለኛነት ግብረመልስ በመስጠት ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ አራት

በዚህ ስር የተሰጡት ቃላት ከተነበበላቸው ጽሁፍ የወጡ ናቸው። በዚህም መሠረት ለቃላቱ ትክክለኛውን ፍች በደብተራቸው ላይ ሰርተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ከዚያም ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ግብረመልስ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አምስት

## ተግባር አንድ

በዚህ ስር ስጋ በልና ሳር በል የሆኑ እንስሳት ስለአካላቸውና ስለባህሪያቸው ተወያይተው እንዲያስረዱ ታዘዋል። በዚህም በቡድናቸው ተወያይተው በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተግባሩን እንዲፈጽሙ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር ሁለት

በዚህ ስር በተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ምስል ተመልክተው ስለእንስሳቱ ስም፣ የሰውነት መጠን፣ ድርጊት እና ባህርያት ተወያይተው በተወካያቸው አማካኝነት የትገነዘቡትን በቃል እንዲያቀርቡ የታዘዙ ስለሆነ በዚሁ መሠረት ተግባሩን እንዲፈጽሙ ያድርጉ።

### መልመጃ ሁለት

በዚህ መልመጃ ስር ስማቸው የተዘረዘሩት እንስሳት ስጋ በል ወይም ሳር በል መሆናቸውን ለይተው እንዲመድቡ የታዘዙ ስለሆነ በዚሁ መሠረት መልመጃውን እነዲሰሩ ያድርጉ። ከዚያም በትክክል ስለመመደባቸው ግብረመልስ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ ሰባት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

በዚህ ስር ያሉትን ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን በመጠቀም እንዲመልሱ የታሰበ ስለሆነ ጊዜ ይሰጧቸውና እንዲወያዩበት ያድርጉ። ከዚያም የተወያዩበትን ምላሽ ካሰጡ በኋላ ትክክለኛነቱን እያረጋገጡ ግብረመልስ ይሥጧቸው።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

በዚህ ስር ያሉት ጥያቄዎች የሚመለሱት ምንባቡ እየተነበበ ሳለ በመሆኑ በቅድሚያ ምንባቡን እንዲያነቡ ያድርጉ። የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን አንቀጾች አንብበው እንዳጠናቀቁ ንባባቸውን ገታ አድርገው ጥያቄዎቹን እንዲመልስ ያድርጉ። ከዚያም ንባባቸውን ካቆሙበት እንዲቀጥሉ ያሳስቧቸው።

### ክፍለጊዜ ስምንት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሦስት

በ"ሀ" ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በተሟሉ ዓረፍተነገሮች በጽሁፍ እንዲመልሱ የታዘዙ ስለሆነ በዚሁ መሠረት እንዲሰሩ ያድርጉ።

### ክፍለጊዜ ዘጠኝ

በ"ለ" ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች **እውነት/ሐሰት** እያሉ እንዲመልሱና መልሶቻቸውንም በምክንያት እንዲያስደግፉ ያድርጉ። መልሶቻቸውንም በጽሁፍ ቢያቀርቡ የተሻለ ነው። ለሰጧቸው መልሶች ተገቢውን ግብረመልስ ይሰጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስር

## ትምህርት አራት፡ መፃፍ

## ተግባር ሦስት

በመጻፍ ተግባር በ "ሀ" ስር የቀረቡትን መነሻ ሀሳቦች ተጠቅመው ከ25 ቃላት ባላነሰ አወዳዳሪ አንቀጽ እንዲጽፉ ያድርጉ። ከዚያም በየቡድናቸው ሆነው በጻፏቸው አንቀጾች ላይ ሀሳብ በመለዋወጥ እንዲተራረሙ ያበረታቷቸው። በማወዳደር የጻፉትን ይመልከቱላቸውና አጠቃላይ እርማት ይስጧቸው። በሚጽፉበትም ጊዜ መከተል ያለባቸውን ሂደቶች መፈጸማቸውንም ያረጋግጡ።

በ "ለ" የተሰጠውን ተግባር ከላይ በ "ሀ" ስር ባለው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠረት እንዲሰሩ ያድርጉ።

### ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### መልመጃ አራት

በ "ሀ" ስር በቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን እንዲሰጡና በቃላቱ ዓረፈተነገሮች እንዲመሰርቱ የታዘዙ ስለሆነ በዚሁ መሰረት ያሰሯቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

በዚህ ክፍል በተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን የቃላት ጽንሰሀሳብ ንድፍ እንዲያሚሉና በንድፉ መሠረት ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ የታዘዙ ስለሆነ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት እንዲሰሩ ያድርጉ።

### ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

በ “ሐ” ስር የተሰጡትን ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን እንዲፈልጉና በቃላቱ ዓረፍተነገሮች መስርተው እንዲያቀርቡ ስለተፈለገ በዚህ መሠረት መልመጃውን ያሰሯቸው። የሰሩትም ትክክል ስለመሆኑ ግብረመልስ በመስጠት ያረጋግጡ።

### ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ትምህርት ስድስት፡- ሰዋስው

### መልመጃ አምስት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን በምዕላድ እንዲከፋፍሉ ታስቧል። በመሆኑም በመጽሀፋቸው ላይ ባለው ምሳሌ መሠረት የተሰጡትን ቃላት በምዕላድ እንዲከፋፍሉ ያድርጉ። መልመጃውንም በክፍል ውስጥ ያሰሯቸው፡ ደብተራቸውንም ሰብስበው በማረም ትክለኛውን ግብረመልስ ይሥጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አምስት

### መልመጃ ስድስት

በዚህ መልመጃ ስር ቃላትን በተለያየ ቅርጽ እንዲመሰርቱ ምሳሌ ተሰጥቷል። በዚህም መሠረት ተማሪዎች ምሳሌውን ተመልክተው የተለያዩ ቃላትን እንዲመሰርቱ ያድርጉ። መልመጃውንም በክፍል ውስጥ ያሰሯቸው። እርስዎም በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ።

### ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

በዚህ መልመጃ ስር ቃላትን በተለያየ ቅርጽ እንዲያረቡ ምሳሌ ተሰጥቷል። በዚህም መሠረት ተማሪዎች ምሳሌውን ተመልክተው የተለያዩ ቃላትን እንዲያረቡ ያድርጉ። መልመጃውንም በክፍል ውስጥ ያሰሯቸው። እርስዎም በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ ሰባት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶች እንዲለዩ የታሰበ ነው። ስለሆነም የተሰጠውን ማስታወሻ መሠረት አድርገው ግሶቹን እንዲለዩ ያድርጉ። መልመጃውንም በክፍል ውስጥ ያሰሯቸውና ደብተራቸውን በመሰብሰብ ያርሙላቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የራሳቸውን ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶች የያዙ አስር አስር ዓረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ የታሰበ ነው። ስለሆነም የተሰጠውን ማስታወሻና ምሳሌ መሠረት አድርገው ዓረፍተነገሮቹን እንዲመሠርቱ ያድርጉ። መልመጃውንም በክፍል ውስጥ ያሰሯቸውና ደብተራቸውን በመሰብሰብ ያርሙላቸው።

## መርጃ መሳሪያዎች

የተለያዩ የዱር እንስሳትን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ

## ግምገማ

- የማዳመጥ ተግባሮችን በትክክል መስራቸውን ማረጋገጥ
- የመናገር ተግባሮችን በትክክል መስራቸውን ማረጋገጥ
- የማንበብ ተግባሮችን በትክክል መስራቸውን ማረጋገጥ
- የማወዳደርና የማነጻጸር ስልትን ተጠቅመው አንቀጾች መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍችና ዓረፍተነገሮች መመስረት መቻላቸውን ማረጋገገጥ
- ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን በዓረፊተነገር ውስጥ መለየጥ መቻላቸውን ማረጋገጥ

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልሶች

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## አዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ለ. እውነት/ሀሰት**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሐሰት | 3. | ሐሰት | 5. | ሐሰት |
| 2. | እወነት | 4. | እውነት | | |

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### መልመጃ ሁለት

ሳርና ስጋ በል በማለት መመደብ

| ስጋ በል | ሳር በል |
|---|---|
| አነር | ድኩላ |
| ሸለምጥማጥ | ዝንጀሮ |
| ጅብ | አጋዘን |
| ጥርኝ | ቀጭኔ |
| አንበሳ | ጉሬዛ |
| ነብር | ጦጣ |

# ትምህርት ሦስት

## መልመጃ ሶስት

ለ. እውነት/ሀሰት

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. እውነት

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

# ቃላትን በምዕላድ መከፋፈል

## መልመጃ አምስት

በ-ጊዜ-አቸ-ው
አንበሳ-ዎቹ
ድንበር-ኣች-ን
በ-ጨዋታ-ው
አለ-መኖር-ኡ-ን

# ቃላትን መመስረት

## መልመጃ ስድስት

1. ዘፋኝ፣ መዝፈን፣ አዘፋፈን
2. ፈላጭ፣ መፍለጥ፣ አፈላለጥ
3. ገማች፣ መገመት ፣አገማመት

## መልመጃ ሰባት

ሀ. ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን መለየት

1. ኢ-ተሻጋሪ
2. ኢ-ተሻጋሪ
3. ተሻጋሪ
4. ተሻጋሪ
5. ተሻጋሪ
6. ኢ-ተሻጋሪ
7. ተሻጋሪ
8. ተሻጋሪ
9. ተሻጋሪ
10. ኢ-ተሻጋሪ

# ምዕራፍ ዘጠኝ፡

## ባህላዊ ጨዋታዎች (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

### 1. የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- ስለ ባህላዊ ውደድሮችና ጨዋታዎች አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ፤
- ስርአተነጥቦችን እየተረዱ ፍች በሚሰጥ መልኩ ጥቅም ላይ ያውላሉ፤
- ውስብስብ የሆኑ ቀለሞችን ያጣምራሉ፤
- ደብዳቤ ይጽፋሉ፤
- የአሁን ጊዜን ለይተው ይጠቀማሉ።

### 2. የትምህርቱ ይዘቶች

#### 2.1 ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች
- መምህራቸው የሚያነቡላቸውን ጽሁፍ በጥሞና ማዳመጥ
- ከጽሁፉ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ መስጠት

#### 2.2 ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- ከጽሁፉ ለወጡ ጥያቄዎች በቃል መልስ መስጠት
- ከራዲዮ የሰሙትን ትረካዎች በክፍል ውስጥ ለክፍሉ ተማሪዎች መተረክ
- ከቤተሰብ የሰሚቸውን ተረቶች በክፍል ውስጥ መናገር

#### 2.3 ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

- የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎችን መመለስ
- ምስሎችን አይተው ቀጣዩን ምንባብ መተንበይ
- የልጆች ጨዋታ በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በግል ማንበብ

#### 2.4 ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- ከምንባቡ ለወጡት ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ መስጠት
- ለጓደኞቻቸው አጠር ያለ ደብዳቤ መጻፍ
- የተሰጡትን ቃላት ቅርጻቸውን በመቀየር ዓረፍተነገሮችን መጻፍ

- የምንባብ ይዘት አሳጥሮ መጻፍ

## 2.5 ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ለቃላት የአገባብ ፍች መስጠት
- በክፍት ቦታዎች ተገቢ ቃላትን በማስገባት አንቀጽ ማሟላት
- ቃላትን ማርባት

## 2.6 ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

- የአሁን ጊዜን መጠቀም

### 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የማዳመጥ ተግባሮችን ክንውን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- የመናገር ተግባሮችን ክንውን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- ተማሪዎች ዳራዊ ዕውቀታቸውን እንዲጠቀሙበት ማድረግ
- የማንበብ ተግባሮችን ክንውን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- የመጻፍ ተግባሮችን ክንውን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ተዘውታሪ ከሆኑ ቃላት እንዲለዩ ማድረግ
- ከግሶች አዳዲስ ቃላትን እንዲመሰርቱ ማድረግ
- የአሁን ጊዜንና የሀላፊ ጊዜን አጠቃቀም እንዲለዩ ማድረግ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ክፍለጊዜ አንድ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

በዚህ ስር ተማሪዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን ለመቀስቀስ በቀጣይ የሚያዳምጡትን ጽሁፍ እንዲተዋወቁ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ተማሪዎቹ በጥያቄዎቹ ላይ በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጉና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው። እርስዎም የራስዎን አስተያየት ያክሉበትና በቀጣይ ያለውን ጽሁፍ ያንብቡላቸው።

የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በተመለከተ ጽሁፉ በሚነበብበት ጊዜ ተማሪዎች ምላሹን መስራት እንዲችሉ አስቀድመው ጥያቄዎችን ዋና ዋና ሀሳቦቹን በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩ ይጠቁሟቸው። የጥያቄዎቹንም መልሶች በተጨማሪ እንዲጽፉ ይንገሯቸው። ከዚያም ጽሁፉን ዝግ ባለ ፍጥነት ያንብቡላቸው። ጥያቄዎቹንም በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ።

## የገበጣ ጨዋታ

ገበጣ በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ የሚዘወተር ባህላዊ ጨዋታ ነው። ጨዋታው ጉድጓዶች ያሉት ሁለት ጣውላዎች ይፈልጋል። ሁለቱ ጣውላዎች ጎን ለጎን ሲቀመጡ በወርድ ሶስት፣ በቁመት ደግሞ ስድስት በአጠቃላይ 18 ጉድጓዶች ይኖሯቸዋል። እንዲሁም ከ18ቱ ጉድጓዶች መጨረሻ አካባቢ ትንሽ ከፍ ብሎ ሁለት ሌሎች ትላልቅ ትርፍ ጉድጓዶች አሏቸው። እነዚህ ጉድጓዶች ኪስ በመባል የሚጠሩ ሲሆን የተበሉ ዶቃዎችን ወይም ጠጠሮችን ማጠራቀሚያ ናቸው።

የገበጣ ጫወታ የራሱ የሆነ የአጨዋወት ደንብ አለው። ለጫወታው በርካታ ዶቃዎች ወይም ጠጠሮች ያስፈልጉታል። ጨዋታው በሁሉም የእድሜ ክልል ላሉ ሰዎች ቀላል ሲሆን በጣውላዎቹ ላይ በሚገኙ በእያንዳንዳቸው 18 ጉድጓዶች ውስጥ በርከት ያሉ ዶቃዎች ወይም ጠጠሮች በማድረግ ይጀመራል። ተጫዋቾች ዶቃዎቹን ወይም ጠጠሮቹን ከአንዱ ጉድጓድ በቀጣይ ወደሚገኘው ሌላ ጉድጓድ አንድ በአንድ ያንቀሳቅሳሉ። የጨዋታው አሸናፊ የሚሆነው በጨዋታው መጨረሻ በኪስ ጉድጓዶቹ ውስጥ በከፍተኛ መጠን የተበሉ ዶቃዎች ወይም ጠጠሮች ያጠራቀመ ተጫዋች ነው። የገበጣ ጨዋታን ለማሸነፍ የተለየ የአቆጣጠር ችሎታና ብልሃት ያስፈልጋል።

የገበጣ ጨዋታ በየትም ስፍራ መጫወት ይቻላል። ሁለቱ ጣውላዎች በቆዳ ጠፍር ላላ ተደርገው እንዲገናኙ ስለሚደረግ ከአንድ ስፍራ ወደሌላ ስፍራ ማንቀሳቀስ ሲፈለግ በማጠፍ ልክ እንደመጽሐፍ በእጅ አንጠልጥሎ መያዝ ይቻላል። የገበጣ ጣውላ ባይኖር እንኳን መሬት ላይ ጉድጓዶቹን በማዘጋጀት ዶቃዎችን ወይም ጠጠሮችን ለቅሞ መጫወት ይቻላል። ቤተሰቦች ለቀጣይ ትውልድ የገበጣ ጣውላዎችን የሚያስቀምጡ ሲሆን እነዚህም ለአዛውንቶችም ሆነ ለወጣቶች ኑሮ እንደ ተምሳሌት በመሆን ያገለግላሉ። በአንዳንድ ቤተሰቦች ወጣት ወንድ ሲያገባ አባቱ ከሙሽሪት ጋር እንዲጫወት የገበጣ መጨወቻ ጣውላ ያዘጋጁለታል።

### ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

በ “ሀ” ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎች ባዳመጡት ጽሁፍ መሠረት በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። እርስዎም የግል አስተያየትዎን ይሥጡና ትምህርቱን ያጠቃልሉ።
በ “ለ” ስር የቀረቡትን የእውነት/ሀሰት ጥያቄዎች በቀረበው ጽሁፍ መሠረት በክፍል ውስጥ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። የመልሳቸውን ትክክለኛነት ግብረመልስ በመስጠት ያረጋግጡ።

### ክፍለጊዜ ሶስት

በ ”ሐ ” ስር ለቀረቡት ቃላት በአዳመጡት ጽሁፍ መሰረት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በቃል እንዲሰጡ ያድርጉ። የተማሪዎችንም መልስ ትክክለኛነት ግብረመልስ በመስጠት ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ አራት

# ተግባር አንድ

በዚህ ስር ያለውን ተግባር በሚመለከት በክፍል ውስጥ ገበጣ ጫወታ መጫወት እንዲችሉ አስቀድመው ለጫወታው የሚሆን ጣውላ እንዲያዘጋጁ ይንገሯቸው። ከዚያም በክፍለጊዜው የአጨዋወት ሂደቱን ተከትለው እንዲጫወቱና እንዲያሣዩ ያድርጉ።

በ "ለ" ስር ያለውን ተግባር ተማሪዎች ከገበጣ ጫወታ ጋር የሚመሳሰል ባህላዊ የጫወታ ,አይነቶች ጠይቀው ስለአጨዋወት ህጉ እንዲገልጹ የታሰበ ስለሆነ በትዕዛዙ መሰረት ሰርተው ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አምስት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ከዳራዊ ዕውቀታቸው ተነስተው በመማሪያ መጽሃፋቸው ላይ ስላሉት ባህላዊ ጫወታዎች የሚመሩባቸውን ህጎች ተወያይተው የደረሱበትን ድምዳሜ ለክፍሉ ተማሪዎች ማብራሪያ እንዲሰጡ የታሰበ ስለሆነ በትዕዛዙ መሠረት እንዲፈጽሙ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

በ "ለ" ስር ያለውን ተግባር ለማሰራት በቅድሚያ የቀረቡትን ጫወታዎች የአጨዋወት ህግ ይግለጹላቸው። ከዚያም ከጫወታዎቹ መካከል አንዱን በመምረጥ በክፍለጊዜው ከመማሪያ ክፍላቸው ውጭ በቡድን በቡድን እየሆኑ እንዲጫወቱ ያድርጉ። አፈጻጸሙንም ተመልክተው ተገቢውን አስተያየት ይሥጧቸው።

## ክፍለጊዜ ሰባት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

# የቅድመንባብ ጥያቄዎች

በዚህ ስር ያሉትን ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን በመጠቀም እንዲመልሱ የታሰበ ስለሆነ ጊዜ ይሰጧቸውና እንዲወያዩበት ያድርጉ። ከዚያም የተወያዩበትን ምላሽ ከሰጡ በኋላ ትክክለኛነቱን እያረጋገጡ ግብረመልስ ይሥጧቸው።

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

በዚህ ስር ያሉት ጥያቄዎች የሚመለሱት ምንባቡ እየተነበበ ሳለ በመሆኑ በቅድሚያ ምንባቡን እንዲያነቡ ያድርጉ። የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን አንቀጾች አንብበው እንዳጠናቀቁ ንባባቸውን ገታ አድርገው ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ ያድርጉ። ከዚያም ንባባቸውን ካቆሙበት እንዲቀጥሉ ያሳስቧቸው።

### ክፍለጊዜ ስምንት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሦስት

በ"ሀ" ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በተሟሉ ዓረፍተነገሮች በጽሁፍ እንዲመልሱ የታዘዙ ስለሆነ በዚሁ መሠረት እንዲሰሩ ያድርጉ።

በ "ለ" ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች እውነት/ሐሰት በማለት መልሶቻቸውንም በምክንያት አስደግፌው እንዲመልሱ ያድርጉ። ለምላሾቻቸውም ተገቢውን ግብረመልስ ይሰጧቸው።

### ክፍለጊዜ ዘጠኝ

በ "ሐ" ስር ከምንባቡ የወጡትን ቃላት ተጠቅመው ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱና እንዲያሳዩ ታዘዋል። በመሆኑም በተሰጠው ምሳሌ መሠረት በቃላቱ ዓረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ያድርጉ። ዓረፍተነገር በሚመሠርቱበት ወቅት የቃላቱ ቅርጽ ሊቀየር እንደሚችል አስቀድመው ያስገንዝቧቸው። መልመጃውንም በክፍል ውስጥ ያሰሯቸውና ደብተራቸውን በማረም ትክክለኛውን ግብረመልስ ይሥጧቸው፡፤

### ክፍለጊዜ አስር

## ተግባር ሦስት

በዚህ ተግባር ስር መሐረቤን ያያችሁ ስለሚለው የልጆች ጨዋታ ከጽሁፍ አንብበው ወይም ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቀው እንዴት እንደሚከወን ጽፌው እንዲመጡ ያድርጉ። ከዚያም ጽፌው ያመጡትን በቡድን ሆነው እንዲወያዩበትና የደረሱበትን የጋራ ሀሳብ በቡድን ተወካዮቻቸው በኩል ዘገባ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። እርሰዎም ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡መጻፍ

## ተግባር አራት

በዚህ ተግባር ስር ተማሪዎች የሰላምታ ደብዳቤ እንዲጽፉ ታዘዋል። ስለሆነም ደብዳቤ ከመጻፋቸው በፊት የተሰጣቸውን ማስታወሻና የቀረበውን ናሙና ደብዳቤ በግልጽ እንዲረዱ ያግዟቸው። ከዚያም ለቅርብ ጓደኛቸው ደብዳቤ እንዲጽፉ ያድርጉ። በመጨረሻም የጻፏቸውን ደብዳቤዎች እንዲያቀርቡ በማድረግና በማየት የደብዳቤ አጻጻፍ ስርዓቶችን መከተላቸውን ያረጋግጡ። የተለየ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ካሉ ዕገዛ ያድርጉላቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

በዚህ ክፍለጊዜ ስር የልጆች ጨዋታ በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ እንደገና በማንበብ ጽሁፉ የሚያካትታቸውን ነጥቦች በመጠቀም እንዲጽፉ ታዘዋል። በመሆኑም የጽሁፉን ዋና ዋና ሀሳቦች አሳጥረው እንዲጽፉ ያድርጉ። ከዚያም የጻፉትን በመመልከት ተገቢውን አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉ።

### ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### መልመጃ ሦስት

በ "ሀ" ስር ተማሪዎች ተዘውታሪ የሆኑና ያልሆኑ ቃላትን እንዲለዩ ታስቧል። ስለሆነም በመጽሃፋቸው ላይ የተዘረዘሩትን ቃላት በደብተራቸው ላይ ገልብጠው በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት እንዲለዩ ያድርጉ።

በ "ለ" ስር የተሠጡትን ቃላት ቅርጽ በመቀየር አዳዲስ ቃላትን እንዲመሰርቱ ታዘዋል። በመሆኑም በተሰጠው ምሳሌ መሠረት የቀረበውን መልመጃ እንዲሰሩ ያድርጉ። በትክክል መስራታቸውንም አረጋግጠው አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አራት

በ "ሐ" ስር ተማሪዎች በሳጥን ውስጥ ከተሰጡት ቃላት መርጠው በክፍት ቦታዎቹ በማስገባት አንቀጹን እንዲያሟሉ ተፈልጓል። ስለሆነም መልመጃውን በክፍል ውስጥ በደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲሰሩ ያድርጉ። ከዚያም የሰሩትን ተማሪዎች ደብተር በመሰብሰብ ያርሙላቸውና ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፧

### ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### መልመጃ አራት

በዚህ ስር የአሁን ጊዜን የሚጠቁሙ ሀረጎች በመጠቀም ክፍት ቦታዎችን እንዲያሟሉ ተፈልጓል። ለስራቸውም እንዲረዳቸው የተሰጠውን ማስታወሻ በሚገባ ይግለጹላቸው። ከዚያም ተማሪዎች በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ዓረፍተነገሮቹን እንዲያሟሉ ያድርጉ። ስራቸውንም ተመልክተው ትክክለኛ ግብረመልስ ይሥጧቸው፡፧

### ክፍለ ጊዜ አስራ ስድስት

በ "ለ" ስር ተማሪዎች በሃላፊ ጊዜ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች ወደ የአሁን ጊዜ እንዲቀይሩ ታዘዋል። ስለዚህም የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች በመጠቀም በተሠጠው ትዕዛዝ መሠረት እንዲሰሩ

ያድርጉ። በትክክል መስራታቸውንም ግብረ መልስ በመስጠት ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

በ "ሐ" ስር ተማሪዎች የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች የአሁን ጊዜ ወይም ሀላፊ ጊዜ በማለት ለይተው እንዲጽፉ ታዘዋል። ስለሆነም እያንዳንዱን ዓረፍተነገር እያነበቡ በትዕዛዙ መሰረት በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ያድርጉና ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ትክክለኛነታቸውን ያረጋግጡላቸው ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

በ "መ" ስር ተማሪዎች በቀረቡት ቃላት የአሁን ጊዜን የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች እንዲመሠርቱ ተፈልጓል። ስለዚህ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በክፍል ውስጥ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያድርጉና ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ትክክለኛነታቸውን ያረጋግጡላቸው።

## መርጃ መሳሪያዎች

## ባህላዊ ጫወታዎችን ለመጫወት የሚጠቅሙ ነገሮች

## የተጻፈ ናሙና የሰላምታ ደብዳቤ

## ግምገማ

- የማዳመጥ ተግባሮችን በትክክል መስራቸውን ማረጋገጥ
- የመናገር ተግባሮችን በትክክል መስራቸውን ማረጋገጥ
- የሰላምታ ደብዳቤ መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- የምንባቡን ዋና ዋና ሀሳቦች አሳጥረው መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን መለየት መቻላቸውን ማረጋገገጥ
- ከቃላት ሌሎች ቃላት መመስረት መቻላቸውን ማረጋገጥ
- በዓረፍተነገር ውስጥ የአሁን ጊዜን የሚያመለክቱ ሀረጎች መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

**ለ. እውነት/ሀሰት**

1. እውነት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. ሐሰት

**ሐ. ተመሳሳይ ፍች መስጠት**

1. ጠጠር
2. በእጅ ከፍ አድርጎ መያዝ
3. አንድ በአንድ ማንሳት
4. ተከታይ
5. ኪስ
6. ሸብ
7. መርታት
8. ማዘዋወር
9. ቦታ
10. ብዙ

ትምህርት ሶሰት፡ ማንበብ

## መልመጃ ሁለት

**እውነት/ሀሰት**

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. ሀሰት

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ ሦስት

**ሀ. ተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን መለየት**

| ተዘውታሪ | ተዘውታሪ ያልሆኑ |
|---|---|
| • ሰፈር | ክዋኔ |
| • ቁርስ | ትርክት |
| • ከብት | እንዝርት |
| • ምግብ | እርቦ |
| • ዘፈን | |

- እንቅልፍ

**ለ. ቃላትን መመስረት**

1. ጋላቢ
2. ሐኪም
3. ፀሐፊ
4. ወራሽ
5. ጨራሽ
6. ዘናጭ
7. አርኪ
8. ጠቃሚ
9. ፈጣሪ
10. ተራኪ

**ሐ. ክፍት ቦታዎችን ማሟላት**

1. ዕውቀት
2. ለመግዛት
3. ፈንታ
4. ሂዶ
5. ሳያጠፋ
6. አገናኝታ

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

## መልመጃ አራት

**ሀ. የአሁን ጊዜን የሚጠቁሙ ሀረጎች መጠቀም**

1. እየተፈተነ ነው።
2. እየጋገረች ነው።
3. እያነጠፈች ነው።
4. እየቀነሰ ነው።
5. እያዘጋጀ ነው።
6. እያጠናሁ ነው።
7. እየሠራሁ ነው።
8. ጥላ ስር እያሳለፍኩ ነው።
9. እየተቀመጥክ ነው?

**ለ. ሀላፊ ጊዜን ወደ የአሁን ጊዜ መቀየር**

1. አበራ ልጁን እያስተማረ ነው።
2. ዋቆ ግብር እየገበረ ነው።
3. ሣራ ሊጥ እያቦካች ነው።
4. ልጆቹ ብሔራዊ መዝሙር እየዘመሩ ነው።
5. አዛውንቱ በችግኝ ተከላው ላይ እየተሳተፉ ናቸው።
6. ሕጻኑ የእናቱን ጡት እየጠባ ነው።
7. ጥናቱን ጨርሶ እረፍት እየወሰደ ነው።
8. ዝናቡ እየዘነበ ነው።
9. ልጁ ዘምሮ እየዘመረ ነው።
10. ቅዝቃዜ ስላለ ኮት እየደረብኩ ነው።

# ምዕራፍ አስር

## ስነቃል (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- ስነቃልን አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ፤
- እራሳቸውን መግለጽ ይለማመዳሉ፤
- የዝነኞችን ታሪክ አንብበው ምላሽ ይሰጣሉ፤
- ግለታሪካቸውን ይጽፋሉ፤
- የስነጽሁፍ አላባውያንን ይለያሉ።

## 2. የትምህርቱ ይዘቶች

### 2.1 ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መመለስ
- የተነበበላቸውን ምንባብ አዳምጠው ፍሬ ሀሳቡን መናገር
- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ መስጠት

### 2.2 ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- ምንባቡን አንብበው ስለ ስነቃል መናገር
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መመለስ

### 2.3 ትምህርት ሶስት፡ማንበብ

- ቃላትን ነጣጥሎ ማሳየት
- ቃላትን ማጣመር
- የቃላት ብዙ ቁጥር

### 2.4 ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- ጅምር ሀሳቦችን አሟልቶ መጻፍ
- ቃላትን ተጠቅመው የተሟሉ ዓረፍተነገሮችን መመስረት

- ከቀረበው ተረት ምን እንደተማሩ መግለጽ
- የቀረበውን ተረት ገፀ ባህርይ፣ መቼትና ጭብጥ መለየት
- ግለታሪክ መጻፍ

## 2.5 ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- የቃላት ተዋቃሪዎችን መነጣጠል
- የቃላት ተዋቃሪዎችን ማጣመር

## 2.6 ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

- ቀጥተኛ ተሳቢ.ዎችን መለየት
- ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ.ዎችን መለየት

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ቅድመማዳመጥ፣ የማዳመጥ ጊዜና ድህረማዳመጥ ተግባሮችን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- የመናገር ተግባሮችን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- ተማሪዎች ዳራዊ ዕውቀታቸውን እንዲጠቀሙበት ማድረግ
- ቅድመማንበብ፣ የማንበብ ጊዜና ድህረማንበብ ተግባሮችን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- የመጻፍ ተግባሮችን ክንውን በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ
- የቃላት ተዋቃሪዎችን በመነጠልና እና በማጣመር እንዲያሳዩ ማድረግ
- ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ.ዎችን እንዲለዩ ማድረግ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ክፍለጊዜ አንድ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

በዚህ ስር ተማሪዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን ለመቀስቀስ በቀጣይ የሚያዳምጡትን ጽሁፍ እንዲተዋወቁ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ተማሪዎቹ በጥያቄዎቹ ላይ በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጉና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው። እርስዎም የራስዎን አስተያየት ያክሉበትና በቀጣይ ያለውን ጽሁፍ ያንብቡላቸው።

የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በተመለከተ ጽሁፉ በሚነበብበት ጊዜ ተማሪዎች ምላሹን መስራት እንዲችሉ አስቀድመው ጥያቄዎቹንና ዋና ዋና ሀሳቦቹን በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩ ይጠቁሟቸው። ከዚያም ለጥያቄዎቹ እንደአጠያየቃቸው ተገቢ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ። ጽሁፉንም ዝግ ባለ ፍጥነት ያንብቡላቸው። ለጥያቄዎቹም ትክክለኛ መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ።

# ስነቃል

ስነቃል በአንድ ማሕበረሰብ ባህል ውስጥ ጥበባዊ መገለጫ ከሆኑት እድሜ ጠገብ ቅርሶች ዋነኛው ነው። "ስያሜው እንደሚያመለክተው ስነቃል የሚተላለፈው በንግግር አማካይነት ከአፍ አፍ በቅብብሎሽ ነው። የስነቃል ዓይነቶች እጅግ በጣም በርካታ ቢሆኑም፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ተረታ ተረቶች፣ እንቆቅልሾችና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። እርግማንና ምርቃቶች፣ የበዓል ዘፈኖች፣ አፈ-ታሪኮች የመሳሰሉትም ከስነቃል ዓይነቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህ ሥነቃሎች ለተፈጠሩበት ማሕበረሰብ የሚሰጡት ጠቀሜታ ከፍ ያለ ነው። በተለይም ማሕበረሰቡ "ደግና ክፉ"፣ "ጨዋና ያልታረመ" በማለት በንጽጽር የሚገልጻቸውንና እንደመርህ የሚቀበላቸውን እሴቶች ለማስተማርና ለማስተላለፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው።

ባህላዊ የስነቃል ቅርሶች ከዕለት ተዕለት ጠቀሜታቸው ባሻገር የማሕበረሰቡን የኑሮ ዘይቤ ይገልጻሉ። ብልሹ የተባሉ አሰራሮች እንዲታረሙ፣ ጠቃሚዎቹ ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉ ያደርጋሉ። የሩቅ ዘመን ታሪኮችን፣ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን፣ ልማዳዊ ስርዓቶችን ያሸጋግራሉ። ይህንንም ለማድረግ በቀልድም ሆነ በምር ወይም በጨዋታ መልክ በመቅረብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። ከዚህም የተነሳ የታሪክ ተመራማሪዎችን ትኩረት ለመሳብ በቅተዋል። የቤት እንስሳት የተናገሩ በማስመሰል ምሳሌን መመሰል ወይም ተረት መንገር በአገራችን ማሕበረሰቦች ዘንድ የተለመደ ነው። አልፎ ተርፎ፣ "ጦጢትን በብልህነቷ፣ ጅብን በሆዳምነቱ፣ አንበሳን በዱር አራዊት ንጉስነቱ ወዘተ."ይፈርጃሉ። በዚህም ሕጻናትን ማስተማር ጥንትም ሆነ ዛሬ የነበረና ያለ ነው። "ጦጣ እንዴት እንደሰው ልታወራ ቻለች? " ብሎ ተረት ተራቹን መሞገት አይቻልም። ይህም የስነቃል ባህርይ አንዱ መገለጫ መሆኑን ያመለክታል።

ስነቃል ተግባሩ ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ሰፋ ላሉ አገልግሎቶች ሲውል እናያለን። ለማስተማሪያነት፣ ለመምከር፣ በቀልድና በተረብ ለመዝናናት፣ አንዳች እውነታን ለመንገር አገልግሎት ይሰጣል። ሕዝባዊ የባህል ሀብት በመሆኑ፣ ሕዝቡ ያለከልካይ በነጻነት እየተጠቀመ ብሶቱን ያንጸባርቅበታል። የመንግስት ሥርዓትን ይተችበታል፤ እምነቱን ያለስጋት ይገልጽበታል። ስህተት አለባቸው ብሎ የሚያምንባቸውን የኃይማኖቱን ልምዶች ሳይቀር ይነቅፍበታል። ቆንጆን ያሞግስበታል፤ ሥነምግባርን ያስተምርበታል፤ ከሀዘንም ይጽናናበታል። በዚህ መልክ ያልተቋረጠ አገልግሎት እየሰጠ ዘመን ተሻጋሪ ሆኖ ኖሯል።

(ጌታቸው በለጠ፣ <u>አማርኛ ቋንቋ</u> ፣2005 ለክፍሉ እንዲመጥን ተደርጎ የተወሰደ)

### ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎች ባዳመጡት ጽሁፍ መሠረት በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። እርስዎም የግል አስተያየትዎን ይሥጡና ትምህርቱን ያጠቃልሉ።

### ክፍለጊዜ ሦስት

በ “ለ” ስር የቀረቡትን የምርጫ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ በጽሁፍ እንዲመልሱ ያድርጉ። የመልሳቸውን ትክክለኛነት እርማት በመስጠት ያረጋግጡ።

### ክፍለጊዜ አራት

## ተግባር አንድ

በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች ቀደም ሲል ከሰዎች የሰሙትን ወይም የሚያውቁትን አንድ ተረት አሳጥረው እንዲናገሩ ተፈልጓል። በቅድሚያ ተረት ሲቀርብ ተረት አቅራቢውና አድማጮች የሚሏቸውን ነገሮች ይግለጹላቸው። ከዚያም የሚያውቁትን ወይም የሰሙትን ተረት በተረት አቀራረብ ደንብ መሠረት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ።

### ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር ሁለት

በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች ቀደም ሲል ከሰዎች የሰሙትን ወይም የሚያውቁትን አንድ ተረት አሳጥረው እንዲናገሩ ተፈልጓል። በዚህም መሠረት በተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ ላይ ከ1-4 ከቀረቡት ርዕሰጉዳዮች አንዱን በመምረጥ ተረት እንዲናገሩ ያድርጉ። የተረቱንም አቀራረብ በሚመለከት በተግባር አንድ ስር በተሰጠው መመሪያ መሠረት በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲፈጸም ያድርጉ።

በ “ለ” ስር የተሰጠውን ጥያቄ በሚመለከት ተማሪዎች ተረት በሚያቀርቡበት ጊዜ ሌሎች ተማሪዎች የሚያዳምጡትን ተረት ጭብጥ በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ መዝግበው ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ። አፈጻጸሙንም እየተከታተሉ ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ ስድስት

በዚህ ስር ተማሪዎች ስለስነቃል እንዲያውቁ ተፈልጓል። ስለሆነም በቅድሚያ የሥነቃልን ምንነትና አይነቶች በሚመለከት ገለጻ ይሥጧቸው። በመቀጠልም በተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረቡትን ስነቃሎች አይነታቸውንና በምን ሁኔታ እንደሚነገሩ ሀሳባቸውን እንዲያካፍሉ ያድርጉ። እርስዎም ተማሪዎች በሚሰጡት ሀሳብ ላይ የራስዎን አስተያየት ይሰንዝሩ።

### ክፍለጊዜ ሰባት

በክፍለጊዜ ሰባት ስር በቀረበው ትዕዛዝ ጅምር ስነቃሉን አንብበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ታዘዋል። በዚህም መሠረት በቅድሚያ የቀረበውን ስነቃል እንዲያነቡ ጊዜ ይስጧቸው። ከዚያም ከስነቃሉ ስር የተሰጡት ሁለት ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት እንዲሰሩና ለጓደኞቻቸው

እንዲያቀርቡ ያድርጉ። እርስዎም የራስዎን ሀሳብ ይስጡበትና ትምህርቱን ያጠቃልሉ።

### ክፍለጊዜ ስምንት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

በዚህ ስር ያሉትን ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን በመጠቀም እንዲመልሱ የታሰበ ስለሆነ ጊዜ ይሰጧቸውና እንዲወያዩበት ያድርጉ። ከዚያም በጥያቄዎቹ ላይ የተወያዩበትን ምላሽ እንዲናገሩ ያድርጉ። ትክክለኛነቱንም እያረጋገጡ ግብረመልስ ይሥጧቸው።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

በዚህ ስር ያሉት ጥያቄዎች የሚመለሱት ምንባቡ እየተነበበ ሳለ በመሆኑ በቅድሚያ ምንባቡን እንዲያነቡ ያድርጉ። የመጀመሪያዎቹን አራቱን አንቀጾች አንብበው እንዳጠናቀቁ ንባባቸውን ገታ አድርገው ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ ያድርጉ። ከዚያም ንባባቸውን ካቆሙበት እንዲቀጥሉ ያሳስቧቸው።

### ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

በ"ሀ" ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በበጽሁፍ እንዲመልሱ የታዘዙ ስለሆነ በዚሁ መሠረት እንዲሰሩ ያድርጉ። የሰሩትንም መልሶች ተመልክተው ተገቢውን ግብረመልስ ይሥጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስር

በ "ለ" ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች እውነት/ሐሰት በማለት መልሶቻቸውንም በምክንያት አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጉ። ለምላሾቻቸውም ተገቢውን ግብረመልስ ይሰጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

### መልመጃ ሦስት

በ "ሀ" ስር የተሠጡትን ጅምር ሀሳቦች አሟልተው እንዲጽፉና ደብተራቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር በመቀያየር እንዲተራረሙ የተፈለገ ስለሆነ በትዕዛዙ መሠረት እንዲፈጸሙ ያድርጉ።

በ "ለ" ስር በቀረቡት ቃላት ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ታዘዋል። ስለሆነም ተማሪዎች የተሰጠውን ምሳሌ ዋቢ በማድረግ ዓረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ያድርጉ። እርሰዎም የመሰረቷቸውን ዓረፍተነገሮች በመመልከት ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

በ "ሐ " ስር የቀረበውን ከመስራታቸው በፊት ስለታሪክ፣ ገፀ-ባህሪና ጭብጥ ምንነት ያስረዷቸው። ከዚያም “ዝሆንና ዝንጀሮ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ተረት በድጋሚ እንዲያነቡና በተረቱ ውስጥ የተነሱትን ዋና ዋና ሀሳቦች አሳጥረው እንዲጽፉና እንዲያቀርቡ ያድርጉ። በትክክል መጻፋቸውንና በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የመነሻ ሀሳቦች ከግምት ውስጥ ማስገባታቸውን ያረጋግጡ።

### ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## ተግባር አራት

በዚህ ስር ተማሪዎች ግለታሪካቸውን እንዲጽፉ ተፈልጓል። ስለሆነም በቅድሚያ ግለታሪክ ምን እንደሆነና በግለታሪክ መካተት ስለሚገባቸው ነገሮች በማስታወሻ መልክ የተሰጠውን በተገቢው ሁኔታ ያብራሩላቸው። ከዚያም እያንዳንዳቸው ግለታሪካቸውን እንዲጽፉ ያድርጉ። እርስዎም ተገቢውን አስተያየት ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በ “ሀ” ስር የተሰጡትን ቃላት ነጣጥለው እንዲያሳዩ ምሳሌ ተሰጥቷቸዋል። በዚህም መሠረት የቀረቡትን ቃላት ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ በመጻፍ ነጣጥለው እንዲያሳዩ ያድርጉ።እርስዎም ምላሻቸውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ግብረመልስ ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ አምስት

በ “ለ” ስር የተሰጡትን ቃላት እንዲያጣምሩ ታዟል። በመሆኑም የተሰጠውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ የተነጣጠሉትን ምዕላዶች ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ በመጻፍ አጣምረው እንዲያሳዩ ያድርጉ። እርስዎም ምላሻቸው ትክክል ስለመሆኑ ግብረመልስ ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

በ “ሐ” ስር የቀረቡትን ቃላት ተጠቅመው የብዙ ቁጥራቸውን ከሰጡ በኋላ ነጣጥለው እንዲያሣዩ በቀረበላቸው ምሳሌ መሠረት እንዲሰሩ ያድርጉ። ምላሻቸውንም ተመልክተው ተገቢውን አስተያየት ይሥጧቸው።

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ አምስት

በቅድሚያ ጥያቄውን ከማሰራትዎ በፊት በቀረበው ማስታወሻ ላይ በቂ ማብራሪያ ይስጧቸው። ትምህርቱንም ለማጠናከር ምሳሌዎችን እየሠጧቸው ያለማምዷቸው። ከዚያም በትዕዛዙ መሠረት

ቀጥተኛና ኢ.ቀጥተኛ ተሳቢ. ስሞች ያላቸውን ዓረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ያድርጉ። በትክክል መስራታቸውንም ግብረመልስ በመስጠት ያረጋግጡላቸው።

### ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### መልመጃ ስድስት

በዚህ ስር በዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ቀጥተኛና ኢ.ቀጥተኛ ተሳቢ.ዎች እንዲለዩ ታዘዋል። ስለሆነም ዓረፍተነገሮቹን በደብተራቸው ላይ በመጻፍ መልሶቻቸውን ከስር በማስመር እንዲለዩ ይንገሯቸው።ከዚ.ያም በትክክል መስራታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል ደብተራቸውን ሰብስበው ያርሙላቸው።

## መርጃ መሳሪያዎች

በመቅረጸ ድምጽ የተቀረጹ የተለያዩ የሚ.ደመጡ የስነ.ቃል አይነቶች

## ግምገማ

- የማዳመጥ ተግባሮችን በትክክል መስራቸውን ማረጋገጥ
- የመናገር ተግባሮችን በትክክል መስራቸውን ማረጋገጥ
- ጅምር ሀሳቦችን አሟልተው መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ግለታሪክ መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ከቀረበላቸው ተረት ውስጥ ዋና ዋና ሀሳቦችን መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- የምንባቡን ዋና ዋና ሀሳቦች አሳጥረው መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍች መስጠት መቻላቸውን ማረጋግገጥ
- የቃላትን ተዋቃሪዎችን መነጠልና ማጣመር መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ቀጥተኛና ኢ.ቀጥተኛ ተሳቢ.ዎችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡

# በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

**ለ. ምርጫ**

1. ሐ
2. መ
3. ሀ
4. መ
5. ሀ

### መልመጃ ሁለት

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

**ለ. እውነት/ሐሰት**

1. ሐሰት
3. ሐሰት
5. እውነት

2. እውነት 4. ሐሰት

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ አራት

**ሀ. ቃላት መነጠል**

1. ዛፍ-ኦች
2. ቅጠል-ኣ-ቅጠል
3. በ-በሬ
4. አንበሳ-ዎች
5. ለ-መንግስት
6. ሰው-ኦች-ኡ
7. ሌባ-ዎች-ኡ
8. ወታደር-ኣዊ
9. በ-ቤት-ኣቸው
10. ቤት- ኧኛ

**ለ. ምዕላዶችን ማጣመር**

1. አህያዋ
2. ዘመናዊ
3. ጎረቤቶቼ
4. በመኪናው
5. እናቴ
6. ቂላቂል
7. ወዳጅነት
8. አጠራጣሪ
9. ወርቃማ
10. ጠጪት

**ሐ. ለቃላት ብዙ ቁጥር መስጠትና ነጣጥሎ ማሳየት**

| | | |
|---|---|---|
| 1. | መኪናዎች | መኪና-ዎች |
| 2. | ተራራዎች | ተራራ-ዎች |
| 3. | ካህኖች | ካህን-ኦች |
| 4. | እንስሶች | እንስስ-ኦች |
| 5. | ችግኞች | ችግኝ-ኦች |
| 6. | ፍሬዎች | ፍሬ-ዎች |
| 7. | ልብሶች | ልብስ-ኦች |
| 8. | ጀግኖች | ጀግን-ኦች |
| 9. | ምግቦች | ምግብ-ኦች |
| 10. | ልባሞች | ልባም-ኦች |

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

## መልመጃ ስድስት

| | ኢቀጥተኛ ተሳቢ | ቀጥተኛ ተሳቢ |
|---|---|---|
| 1. | ለባሏ | ሽልማት |
| 2. | ለህጻኑ ልጅ | ጡጦ |
| 3. | ለወዳጁ | ሎሚ |
| 4. | ለአባቷ | ቤት |
| 5. | ለአማቱ | ልብሶች |

# አማርኛ አንደ አፍመፍቻ ቋንቋ 5ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት

## መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ በትምህርት አሰጣጥ ፈጣንና መሻሻል በታየበት ሁኔታ እየሰራች ነው። ልዩ ትኩረት የተሰጠው "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለውን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" ላይ ነው። ይኸውም ለ21ኛው ክፍለ ዘመን እድገት እንደመሳሪያ ሆኖ በብቃት ህብረተሰቡን ወደ ፊት የሚያራምድ ነው። ይህንን ግብ ለማሳካት ትምህርት ሚንስቴር የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምሮችን በማድረግ አዲስ ስርዓተ ትምህርትን ቀርጿል። በዚህም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተትምህርት መሳሪያዎቹ (የይዘት ፍሰት፣ አነስተኛ የመማር ብቃትና መርሀትምህርት) በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ስርኣተ ትምህርት ማእቀፍ ውስጥ ተመስርተው እንዲዘጋጁ ተደርገዋል። እነዚህ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተትምህርት መሳሪያዎች ዋና መነሻቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ልህቀትን ለማሻሻል ሲሆን በአውድ የተደገፈ፣ በህጻናት እድገት ላይ በተደረገው የምርምር ማስረጃና በመማር ላይ የተመሰረተ ትምህርታዊ ስኬታማነትን እንዲያረጋግጡ ተደርገው ተቀርፀዋል። በአውዱ የተሰጡት መነሻ ልምምዶችም የተማሪውን መማር የመጨረሻ ግብ የሚያሳድጉ ናቸው ተብሎ ይታሰባል። የስርዓተ ትምህርት መሳሪዎች በዋናነት እንዲቀረፁ የተደረጉት የመማር ውጤት፣ ብቃት፣ ይዘት፣ የመማር ስልቶች፣ ምዘናና ለእያንዳንዱ ይዘት ጊዜ በመስጠት ነው።

መርሃ ትምህርቱ የተለያዩ አገር በቀል እውቀቶችን፣ ዋና ዋና ክሂሎችን፣ ለህይወት አስፈላጊ የሆኑትንና ብርቱ ብሄራዊ ጉዳዮችንና ብቃቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅቷል።

ይህም በብሄራዊና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ብቁ ዜጋ ለማፍራት ታስቦ የተሰናዳ ነው። የይዘቱ ፍሰትም ከቀላል ወደ ውስብስብ፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሚሄድ ሆኖ ተማሪዎቹ አውዳዊ ይዘቱን እንዲረዱ የሚያስችል ነው። መልመጃዎቹ ተማሪ ተኮር የሆኑ፣ አብዛኛውን እድል ለተማሪዎች የሚሰጡ፣ የታሰበውን የቋንቋ ክሂል ተለማምደው እንዲያሳድጉ የሚያስችሉ ሆነው በደረጃቸው የቀረቡ ናቸው።

በዚሁ መሰረት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በክልሉ ለሚገኙ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ ለፈቱ ተማሪዎች ይህን በትምህርት ሚኒስቴር የቀረበ ስርዓተ ትምህርት ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ አስማምቶ አቅርቦታል።

### የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ግቦችና አላማዎች
### የአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ግቦች ፡-

ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያለውን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በስኬታማነት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎቹ ቀጥለው ያሉትን ግቦችና አላማዎች እንዲያሳኩ ይጠበቃል።

# ግቦች

የመሰረታዊ ፊደላትን ክሂል ማበልጸግ የተማሪውን አእምሮታዊ፣ስሜታዊና ማህበራዊ ክሂሎችን ለማሳደግ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤

ተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎትና ስነልሳናዊ እውቀት ማስተዋወቅ ለተግባቦት ብቃት ማዳበር ስለሚያግዛቸው ሀሳባቸውንና ስሜታችውን በተለያዩ አውዶች ውስጥ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤ ተማሪዎቹን አገር በቀል እውቀትና እሴቶችን እንዲያውቁ ስለሚያደርጋቸው በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ውስጥ እንዲጠቀሙባቸው ያስችላቸዋል።

# አላማዎች

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማርና የመማር አበይት አላማዎች፡-**

- መሰረታዊ ትምህርትን በማዳበር ተማሪዎች ለወደፊት የትምህርት ግባቸው ዝግጁ እንዲሆኑ ጽናት ይሰጣቸዋል፤
- የቋንቋውን ዋና ዋና ክሂሎች መረዳት የተግባቦት ችሎታቸውን ለማሳደግ እና ሀሳባችውንና ስሜታቸውን ውጤት ባለው መንገድ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤
- የቋንቋውን ንዑሳን ክሂሎች ማወቅ የተግባቦት ችሎታቸውን ለማዳበር እንደሚረዳቸው እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል፤
- ከሳይንሳዊ ምርምር የተገኙትን የቋንቋና የስነልሳን ባህሪያት እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፤
- የቋንቋ አጠቃቀምን በትምህርት፣ በማህበራዊ ኑሮና በምጣኔ ሀብት ሁነቶች ውስጥ እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፤
- የአገር በቀል ቋንቋ ስልቶችን በተለያዩ የቋንቋ ይዘቶች በማቅረብ እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል።

# ራዕይና እሴቶች

## ራዕይ

የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርና ማስተማር ለአለም ቋንቋዎች ሁሉ ዋጋ ይሰጣል ተብሎ ስለሚጠበቅ እያንዳንዱ ሰው በተለይም ህጻናት ቋንቋውን መናገር ብቻ ሳይሆን መማር በመቻል ያንን ቋንቋ በቀላሉ ይረዳሉ። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጠንካራ መሰረቶች የሚኖሩ ከሆነ ተማሪዎች በተሻለ መንገድ ስርዓተ ትምህርቱን እየተረዱ እንደዚሁም አዎንታዊ አመለካከት ኖሯቸው ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ። ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከህጻንነታቸው ጀምሮ ጠበቅ አድርገው ማወቃቸው አስፈላጊ በመሆኑ በየክፍል ደረጃው የተሻለ ጥረት በማድረግ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ።

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የህጻናት አእምሮ ብስለትን በማሳደግ የቋንቋ ክሂሎችን፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችንና ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር ይረዳቸዋል። ይህን እሳቤ

ውስጥ በማስገባት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ተምረው ያለፉ ኢትየጵያዊ ተማሪዎች በሰላምና በመተሳሰብ አብሮ በመኖር ፡-

- ብቃት ያለው የቋንቋ ክሂል ባለቤት፣ ባህልንና ማንነትን አክባሪ፣የማሰብና የመፍጠር ባለቤት፣ በራስ የሚተማመኑ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ትጉኃን፣ ትኩረት ሰጪዎች፣ ምክንያታዊያን ተባባሪና ራስን በመስጠት የሚሰሩ ይሆናሉ፤

# እሴቶች

እሴቶች አስፈላጊና ፍትሃዊ ስለሆኑ ነገሮች ያሉን እምነቶች ናቸው። እሴቶች ድርጊታችንንና ውሳኔያችንን ይመራሉ፤ ስለዚህ ይህ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት የተዘጋጀው ጽሁፍ ተማሪዎቹ፡-

አገር በቀል እወቀቶችን አክባሪና ተጠቃሚ፣ የህብረተሰቡን የግጭት አፈታት ባህሎችን የሚተገብሩ፣ የስርዓተ ጾታ እኩልነትን ተግባራዊ የሚያደርጉ፣ የመረዳዳት መንፈስ ያላቸው፣ የመቻቻል ባህል የተላበሱ፣ ብሄራዊና አለማቀፋዊ ቅርስ የሚንከባከቡ፣ በልዩነት ውስጥ አንድነት የሚቀበሉ፣ እርስ በእርስ የሚከባበሩ፣ ጠንክሮ የመስራት ባህል ያላቸው፣ በላቀ ሁኔታ የሚያስቡ፣ የፈጠራ ችሎታን የተላበሱ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ስለአካባቢ ጥበቃ የሚያስቡ እንዲሆኑ የሚያበረታታ መሆን አለበት።

# የአንደኛ መንፈቀ አመት
# ምዕራፍ አንድ ፡

## ጓደኝነት (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

የሚጠበቀው ውጤት፡- ተማሪዎቹ የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ስለጓደኝነት ያዳመጡትን በተመለከተ አድናቆታቸውን ይገልፃሉ
- የቀረበላቸውን ፅሑፍ በማንበብ ዋናውን ሃሳብ ይገልፃሉ
- ስለጓደኞቻቸውና ስላሳለፉት ጊዜ ቀለል ያሉ አረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንቀፅ ይፅፋሉ
- ያነበቡትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ተዛማጅ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ
- የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺዎች ይናገራሉ
- የወልና የተፀውዖ ስሞችን ይለያሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• አዳምጠው የተሰማቸውን ይናገራሉ/ያንፀባርቃሉ<br>• የቀረበ ምንባብን በዝምታ አንብበው ዋናውን ሀሳብ ይለያሉ<br>• የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ<br>• አንቀፅን ለማስፋፋት የሚረዱ አላባዎችን ይለያሉ<br>• የወል ስሞችንና የተፀውዖ ስሞችን ይለያሉ | • ማዳመጥና መናገር<br>•<br>• ማንበብ<br>•<br>• ቃላት<br>•<br>• መፃፍ<br>•<br>• ሰዋስው | • ተማሪዎች ሰዎች ትርፍ ጊዜያቸውን በተመለከተ የሚናገሩትን አዳምጠው በቅደም ተከተል ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ያሰፍራሉ<br>• ተማሪዎች ሩ እርስ በርሳቸው በመተዋወቅ ለመምህር ያቀርባሉ<br>• ተማሪዎች መምህራቸውን እየተከተሉ ማህበራዊ አገላለፆችን ደግመው ይላሉ፣ ከቀኑ ጊዜ ጋር ያዛምዳሉ<br>• በትምህርቱ መግቢያና መጨረሻ ላይ የአንቀፅ አላባዊያንን ይለያሉ<br>• ተማሪዎች የስፖርት ስዕሎችን እና የትርፍ ጊዜ ተግባራትን ከቃላት ወይም ከተዘጋጁ ስዕሎች ጋር ያዛምዳሉ | ተማሪዎች ምንባብን አዳምጠው ስለሰዎች የትርፍ ጊዜ አጠቃቀም ጥያቄዎችን ይመልሳሉ<br><br>ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው ምን እንደሚያደርጉ ይፅፋሉ<br><br>ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ የተገለፁትንና በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ያከናወኗቸውን ተግባራት በውሎ ማስታወሻቸው ላይ ይፅፋሉ |

# ምዕራፍ ሁለት፡

## ንፅህናና ፅዱነት (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ከምንባቦች የወጡ ጥያቄዎችን አዳምጠው ይመልሳሉ
- ተማሪዎች ፅዳትን በተመለከተ ሰዎች የሚያከናውኑትን ይናገራሉ
- በክፍል ደረጃው ትክክለኛ ንባብን ይለማመዳሉ
- ተገቢ ርዕስን በመጠቀም አጭር አንቀፅ ይፅፋሉ
- የይዘትና አዳዲስ ቃላትን ያስተዋውቃሉ/ይወያያሉ
- ተማሪዎች የቀለም መዋቅርንና ምዕላድን ይረዳሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡ በቡድን ውይይት ይሳተፋሉ<br>• በክፍል ደረጃው ትክክለኛነትን በንባብ አማካኝነት ይለማመዳሉ<br>• አጭር አንቀፅ ይፅፋሉ<br>• የይዘትና አዳዲስ ቃላትን ያስተዋውቃሉ/ይወያያሉ<br>• የተማሯቸውንና ከፍ ያለ ውስብስብነት ያላቸውን የቀለማት መዋቅሮችንና ምዕላዶችን በማጣመርና በመነጠል ቃላትን ይለያሉ | • ማዳመጥና መናገር<br>•<br>• ማንበብ<br>•<br>• ቃላት<br>•<br>• መፃፍ<br>•<br>• ሰዋስው | • የቡድን ውይይት፡ ተማሪዎች በማዳመጥና በቡድን ውይይት በመሳተፍ ቀጥሎም ሰዎች ስለሚከውኑት በመናገር ግንዛቤያቸውን ያዳብራሉ<br>• ሰዎች ንፅህናን ለመጠበቅ የት እንደሚሄዱና ምን እንደሚያደርጉ የሚገልፅ ዕለታዊ ፅሑፍን ያነብባሉ<br>• ተማሪዎች ሰዎች በክፍል ውስጥ ምን እንደሚከውኑ ይናገራሉ<br>• ተማሪዎች በጥንድ በመሆን የተጓደለ መረጃ ያላቸውን ተግባራት ያሟላሉ<br>• አንድ ተማሪ ንፅህና መጠበቅን በተመለከተ በምልክት ይገልፃል ሌሎቹ በምልክት የተገለጸውን ይገምታሉ | በውይይታቸው የተነሳውን አጠቃላይ ጉዳይ በተመለከተ አዳምጠው መልሰው ይናገራሉ<br><br>ታሪክን አንብበው ተግባራትን ይሰራሉ፤ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ<br><br>ሰዎች እንዴት ንፅህናቸውን እንደሚጠብቁ አጭር አንቀፅ ይፅፋሉ<br><br>ተማሪዎች ከቀረበ ምንባብ የይዘት ቃላትንና ሌሎች አዳዲስ ቃላትን ያጎለብታሉ |

# ምዕራፍ ሦስት፡ ትውፊት

(የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ታሪክን አዳምጠው መልሰው ይናገራሉ
- በተገቢው ቅላፄ ድምፅን ከፍ አድርገው ያነባሉ
- የአንቀፅ አይነቶችን ይለያሉ
- ለቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ
- ተውሳከ ግሶችን ከአረፍተ ነገሮች ውስጥ ይለያሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡<br>• አዳምጠው ታሪክን ይተርካሉ<br>• ተቀባይነት ባለው ቅላፄ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ምንባብ ያነባሉ<br>• የአንቀጽ አይነቶችን ይለያሉ<br>• ለቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ<br>• ተውሳከ ግሶችን ከአረፍተ ነገሮች ውስጥ ይለያሉ | ማዳመጥና መናገር<br><br>ማንበብ<br><br>ቃላት<br><br>መፃፍ<br><br>ሰዋስው | ምልልስን ያዳምጡና ትውፊት/ልማድ ምን እንደሆነ መግለፅ<br><br>ተጨማሪ ማብራሪያ፡ -ተማሪዎች ያነበቡት ፅሁፍ ላይ የተከሰቱ አደናጋሪ ነገሮችን በተመለከተ ማብራሪያ እንዲጠይቁ ማበረታታት<br><br>የጥያቄ-መልስ ግንኙነቶች<br><br>ከቀረበው ፅሑፍ ድህረ ምንባብ ተግባራት ማዘጋጀት፤ አራቱን መመሪያዎች ባካተተ መልኩ<br><br>ትክክለኛው ምላሽ እዚያው ይገኛል! (ምላሹን በአንደኛው አረፍተ ነገር ውስጥ እናገኘዋለን)<br><br>• ማሰብ ማሰስ (ምላሹ ምንባቡ ውስጥ ይገኛል ግን መረጃው የሚገኘው በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ነው) | ተማሪዎች ስለአንድ ባህላዊ መሳሪያ እንዲያዳምጡ በማድረግ ስለጠቀሜታው እንዲገልፁ ማድረግ<br><br>መምህሩ ሁለትምልልሶችን ያነባሉ ቀጥሎ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን መለየት፣ መጠቀም<br><br>• ተማሪዎች ስለጥሩና መጥፎ ልማዳዊ ድርጊቶች መፃፍ |

# ምዕራፍ አራት፡

## የመንገድ ደህንነት (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ምልልስን አዳምጠው የምልልሱን ጠቀሜታ መልሰው ይናገራሉ
- ፍች ላይ ለመድረስ የተለያዩ አዳምጦ የመረዳት ብልሃቶችን ይጠቀማሉ
- ማህበራዊ አገላለፆችን ይጠቀማሉ (ግብዣ መጋበዝ፣ ሲጋበዙ ደግሞ መልስ መስጠት)
- የቀረበውን አንቀፅ ጭብጥ፣ ፍች እና/ወይም አላማ ያስረዳሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• ለክፍል ደረጃው ተቀርፀው የቀረቡ ማስተማሪያዎችን ያዳምጣሉ<br>• የቀረበውን ፅሑፍ በማንበብ ዋናውን ሀሳብ መዘው ያወጣሉ<br>• ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን አዳምጠው ይመልሳሉ<br>• የቀረቡላቸውን ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች ይፅፋሉ<br>• የሁኔታ ተውሳከ ግሶችን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ<br>• ገላጭ አንቀፅን ይፅፋሉ | ማዳመጥና መናገር<br><br>ማንበብ<br><br>ቃላት<br><br>መፃፍ<br><br>ሰዋስው | • ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ስዕሎች ላይ ምን እንዳዩ ይገልፃሉ (ስዕሎቹ የትራፊክ አደጋን ያመለክታሉ)<br>• የትራፊክ ህጎችን በተመለከተ ተማሪዎቹ ጥያቄ ይጠይቃሉ ምላሽ መስጠት፡፡ በመንገድ ላይ ምን ያደርጉ እንደ ነበር/ እንደሚያደርጉ ማስረዳት<br>• አንድን ሰው ወደ ሰሌዳው መጋበዝን የሚያሳይ አጭር ምልልስ መምህር ማሰናዳት<br>• ተማሪዎች አንዱን የአረፍተ ነገር ክፍል ከሌላኛው /ከቀሪው/ ክፍል ጋር ማዘመድ | መምህር የትራፊክ ደህንነትን የተመለከቱ ምልክቶችን እያሳዩ ገለፃ ማቅረብ፣ ተማሪዎቹ ጠቀሜታቸውን በተመለከተ ምላሽ መስጠት<br><br>ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ፅሑፍ መረዳታቸውን ለመመዘን የተለያዩ ራስን መገምገሚያ ብልሃቶች ማጎልበታቸውን መቀጠል<br><br>የትራፊክ ደህንነትን በተመለከተ አረፍተ ነገሮችን መፃፍ<br><br>መጋበዝንና ለግብዣ ምላሽ መስጠትን አስመልክቶ የቀረቡ አረፍተ ነገሮችን ማንበብ |

# ምዕራፍ አምስት፡

## አከባቢ ጥበቃ (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ፅሑፍ ከቀደመ እውቀታቸውና ልምዶቻቸው ጋር ያዛምዳሉ
- መዝገበ ቃላትን ወይም የቃላት ዝርዝርን በመጠቀም የሆሄያት አሰዳደርን፣ ፍችንና የቃላት እርባታን ይለያሉ
- በክፍል ደረጃው የመፃፍ ተግባር ወቅት ድምፀት አመላካቾችን ይጠቀማሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| **ተማሪዎች፡-**<br>• ያዳመጡትን በቃል መልሶ መተረክ<br>• ቃላትን በምዕላድ ደረጃ በመነጠልና በማጣመር ማንበብ<br>• የአንቀፅ ሀይለቃልን ለይቶ ማውጣት<br>• በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞችን ለይቶ ማመልከት | • ማዳመጥና መናገር<br>•<br>• ማንበብ<br>•<br>• ቃላት<br>•<br>• መፃፍ<br>•<br>• ሰዋሰው | • **ቃላትን ማደን**<br>• በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉ ወይም በስዕሉ የተወከሉ ቃላትን እና በሌሎች ቃላት ውስጥ ያሉ የቃላት ክፍሎችን (ምዕላዶችን) ምሳሌዎች ለይቶ ለማመልከት ተማሪዎች የዕለታዊ ትምህርቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ አሰሳ ያደርጋሉ<br>• **ራስን ችሎ ለማንበብ እድል መስጠት** ራስን ችሎ ማንበብ ተማሪዎች ከምንባቡ ጋር የተገናኙ አዳዲስ ቃላትን እንዲያነቡና የቃላት ማጎልበቻ ብልሃቶችን እንዲያዳብሩ እድል ይፈጥርላቸዋል<br>• ተማሪዎች ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ፅሑፍ መረዳታቸውን ለመመዘን ራስ መገምገሚያ ብልሃቶችን ያጎለብታሉ | **ምልከታ** ተማሪዎች ክፍለ ጊዜው እየተካሄደ ወይም ክፍለ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ በቡድን ወይም በተናጠል ሲሰሩ አጫጭር ማስታወሻዎችን መፃፍ<br>**አቅርቦት**<br>ተማሪዎች እያጎለበቱ ያሉትን የቃላት እውቀት ለመምህሩ ወይም ለክፍሉ በተግባር እንዲገልጡ/እንዲያሳዩ እድል ይሰጣቸዋል<br>**የርስ በርስ ግምገማ** ተማሪዎች ፅሑፋዊ ተግባራትን ካጠናቀቁ በኋላ፣ የመምህርን መመሪያ መሰረት በማድረግ የፃፉትን እየተለዋወጡ የእርስ በርስ እርማት ያካሂዳሉ። በመጨረሻም መምህሩ ወረቀቶቹን በመሰብሰብ አፈፃፀሙን መገምገም<br>ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው ፅሁፍ ውስጥ የቀረቡ ሀሳቦችን ለማደራጀት ስዕላዊ መግለጫዎችን መጠቀም |

# ምዕራፍ ስድስት፡

## ፀረ አደንዛዥ እና ንጥረነገሮች (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- አደገኛ እፆችን ማስወገጃ መንገዶችን በተመለከተ አዳምጠው ይረዳሉ
- የቀረበላቸውን ፅሑፍ አውድ ይተነብያሉ
- አንድን ፅሑፍ ለመረዳት ምልክቶችን፣ መግለጫዎችንና ወካዮችን ያነባሉ
- የአረፍተ ነገር መሸጋገሪያዎችን ይገነዘባሉ
- ቃላት ያጎለብታሉ፣ ፍቻቸውን ይናገራሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| **ተማሪዎች፡-**<br>• በቃል ውስጥ የሚገኑ ቀለሞችን አዳምጠው ይለያሉ<br>• የሚያነቡትን ፅሑፍ ይዘት ይገምታሉ<br>• አገባባዊ ፍቻቸውን በመጠቀም ለቃላት ፍች ይሰጣሉ<br>• የአረፍተ ነገሮች መሸጋገሪያዎችን በአንቀፅ ውስጥ ይጠቀማሉ<br>• ስሞችንና ግሶችን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ | • ማዳመጥና መናገር<br>• ማንበብ<br>• ቃላት<br>• መፃፍ<br>• ሰዋስው | • **ግልፅ ማድረግ፡-** ተማሪዎች በንባብ ወቅት የገጠሟቸውን አደናጋሪ ጉዳዮች በተመለከተ ተጨማሪ ገለፃ ከመጠየቅ እንዳይታቀቡ ማበረታታት<br>• ተማሪዎች በቀጥታ ለተገለፁ ቀጥተኛ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት<br>• **ድህረ ምንባብ ጥያቄዎች አራቱን አይነቶች ጨምሮ-** እዚያው ያለ (የጥያቄውን መልስ በአንደኛው አረፍተ ነገር ውስጥ እናገኘዋለን)<br>• አንቀፅ ሲፅፉ የተማሯቸውን መሸጋገሪያ ምዕላዶች፣ አያያዥ ቃላት እና ሀረጋትን ይጠቀማሉ<br>(ቋንቋ ላይ የተመሰረተ)<br>• **ማሰብ ማሰስ፡-** ( ምላሹ በቀረበው ፅሑፍ ውስጥ ይገኛል ነገር ግን ከአንድ በላይ የሆኑ አረፍተ ነገሮችን ማየት ይጠይቃል) | • ጥያቄዎችን ይመልሳሉ ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን አስታውሰው ያጋራሉ:: መምህር በዚህን ወቅት ያገኙትን መረጃ የዕለቱ ትምህርት አካሄድን ለመወሰን ይጠቀሙበታል::<br>• **ካርዶችን ማውጣት:**<br>- ተማሪዎች የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ካርዶች በማውጣት ለጥያቄዎች የተለያዩ ምላሾችን ይሰጣሉ (ለምሳሌ እንቁላል ቢባል እነሱ ካርዳቸውን እያወጡ እስማማለሁ/አልስማማም ማለታቸውን በካርዶቹ ይገልፃሉ)<br>• **ኢ-መደበኛ ቁጥጥር-** መምህር ክፍል ውስጥ በመዘዋወር የትኛው ተማሪ እንደተረዳና የትኛው ተማሪ እገዛ እንደሚያስፈልገው ይከታተላሉ<br>• ዳራዊ እውቀትንና መረጃን የሚሹ የአንድምታ ጥያቄዎች ይመልሳሉ |

# ምዕራፍ ሰባት፡

## ምግብ (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- አስረጅ ፅሑፍን አዳምጠው ይረዳሉ
- ስርዓተ ነጥቦችን ለይተው በማወቅ ይጠቀሙባቸዋል
- ተገቢ ፊደላትን ተጠቅመው ይፅፋሉ ስርዓተ ነጥቦችን በቦታቸው ይጠቀማሉ
- ሂደታዊ ትንተና አንቀፅን ይረዳሉ
- ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ለማንበብ የምዕላዳዊ ትርጉሞችን እውቀት ይጠቀማሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• በሚደመጠው ነገር ውስጥ የሚገኙ ሀሳቦችን ያወዳድራሉ፣ ያነፃፅራሉ<br>• ሂደታዊ ትንተና አንቀፅን ያነባሉ፣ ይፅፋሉ<br>• የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች ይሰጣሉ<br>• የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞችን በመለየት ይጠቀማሉ | • ማዳመጥና መናገር<br>•<br>• ማንበብ<br>•<br>• ቃላት<br>•<br>• መፃፍ<br>•<br>• ሰዋስው | ተማሪዎች ስለርዕሰ ጉዳዩ አስቀድመው የሚያውቁትን ለጓደኞቻቸው ማጋራት<br><br>ተማሪዎች ምን መማር እንደሚፈልጉ መናገር በመጨረሻም ምን እንደተማሩ እየከለሱ ማቅረብ<br><br>➢ **የዋና ሀሳብ መግለጫ ሰንጠረዥ** ስለ ምንድን ነው? ዝርዝሮቹ ምንድን ነበሩ?<br><br>➢ **ንድፍ፡-** ዋና ዋና የታሪኩን ሁነቶች ለመመዝገብ<br><br>➢ **ቬን ዲያግራም፡-** ሁለት ነገሮችን ለማወዳደርና ለማነፃፀር (መፃህፍት፣ ገፀ ባህሪያት፣ ወቅቶች፣ ስራዎች)- መንስዔና ውጤት | ተማሪዎች አጠገባቸው ወዳሉ አንድ ወይም ሁለት ተማሪዎች በመዞር ምላሻቸውን ያጋራሉ<br><br>ሂደቱን ለመከታተል መምህሩ በክፍሉ ውስጥ ይዘዋወራሉ<br><br>ተማሪዎቹ ምዕራፉን ሲያጠናቅቁ፣ ግሚሱን የክፍል ተማሪዎች በቅርበት ይዞ ክለሳ ማካሄድና ምጋቤ ምላሽ መስጠት፣<br><br>ቀሪዎቹን ተማሪዎች ደግሞ ብዙም ሳይቀርቡ ክለሳውን ማካሄድ<br><br>(በቀጣዩ ጊዜ የፅሑፍ ስራ ሲኖር ቡድኑን ማቀያየር) |

# ምዕራፍ ስምንት፡

## የዱር እንስሳት (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የተማሯቸውን ውስብስብ የቀለም መዋቅሮች እንዴት እንደሚያጣምሩ አዳምጠው ይረዳሉ
- ውስብስብ የቃላት መዋቅሮችን ያነባሉ
- አንቀፅን በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት ተረድተው ይፅፋሉ
- የስነምዕላዳዊ ፍች እውቀታቸውን ይጠቀማሉ (የእርባታና የምስረታ)
- ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን ይጠቀማሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• በፅሁፍ ውስጥ የሚያገኟቸውን አዳዲስ ስሞች ያዳምጣሉ፣ ይዘረዝራሉ<br>• የቀረበውን ምንባብ አንብበው ከህይወት ልምዳቸው ጋር ያዛምዳሉ<br>• በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት አንቀፅ ይፅፋሉ<br>• የቃላትን ተመሳሳይ ፍች ይሰጣሉ<br>• ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን ይለያሉ | • ማዳመጥና መናገር<br>•<br>• ማንበብ<br>•<br>• ቃላት<br>•<br>• መፃፍ<br>•<br>• ሰዋስው | **ቃል መመስረት፡-** ተማሪዎች የቃላት መዋቅሮችን (ቅድመ፣ ድህረ) በመጠቀም አዳዲስ ቃላትን ማንበብና መፃፍ መለማመድ ወይም አዳዲስ ቃላትን መመስረት<br><br>**ቃል ማደን፡** በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉ ወይም በስዕሉ የተወከሉ ቃላትን እና በሌሎች ቃላት ውስጥ ያሉ የቃላት ክፍሎችን (ምዕላዶችን) ምሳሌዎች ለይቶ ለማመልከት ተማሪዎች የዕለታዊ ትምህርቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ አሰሳ ማድረግ<br><br>**መለየት (ማነፃፀር)፡** ተማሪዎች የቃል መዋቅርን ወይም የሆሂያት ቅደም ተለተሎችን ማነፃፀር (ይህም ተዘውታሪዎቹን ቃላት ተዘውታሪ ካልሆኑት ማነፃፀርንም ይጨምራል) | ትምህርቱን ለማካሄድና የተማሪዎቹን የእድገት ደረጃ ለመከታተል ስልታዊ የሆነ አተገባበርን መከተል<br><br>**መደበኛ ያልሆነ ክትትል**<br><br>መምህሩ ክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ የትኛው ተማሪ እንደተረዳና የትኛው ተማሪ ተጨማሪ እገዛ እንደሚያስፈልገው መለየት<br><br>**ምሪታዊ ክለሳ፡** የቀደመውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት መነሻ በማድረግ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ የተማሩትን ያጋራሉ፤ መምህሩ ይህንን መረጃ የዕለቱን ትምህርት አካሄድ ለመወሰን ይጠቀሙበታል |

# ምዕራፍ ዘጠኝ፡-

## ባህላዊ ጨዋታዎች (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡

- ስለባህላዊ ውድድሮችና ጨዋታዎች አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ
- ስርዓተ ነጥቦችን እየተረዱ ፍች በሚሰጥ መልኩ ጥቅም ላይ ያውላሉ
- ውስብስብ የሆኑ ቀለሞችን ያጣምራሉ
- ደብዳቤ መፃፍ ይችላሉ
- የአሁን ጊዜን ለይተው ይጠቀማሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡<br>• አዳምጠው በባህላዊ ጨዋታዎች ይሳተፋሉ<br>• ስለተለያዩ ጨዋታዎች (ውድድሮች) አንብበው ዘገባ ያቀርባሉ<br>• ደብዳቤ ይፅፋሉ<br>• በአረፍተ ነገር ምስረታ ውስጥ የአሁን ጊዜን ይጠቀማሉ | • ማዳመጥና መናገር<br>•<br>• ማንበብ<br>•<br>• ቃላት<br>•<br>• መፃፍ<br>•<br>• ሰዋስው | **ተዘውታሪ ቃላትን ተዘውታሪ ካልሆኑ ቃላት ማነፃፀር።**<br>ትምህርቱ ቀደም ሲል በትምህርትነት የቀረቡ ቃላት መዋቅሮችን አሁን በመጠናት ላይ ካሉት ቃላት መዋቅሮች ጋር ማነፃፀርን የሚጨምር መሆን አለበት።<br>**በዝርዝር የቀረቡ ቃላትን በመዋቅራቸው ወይም አሰዳደራቸው ለይቶ ማመልከት**<br>ቃላትን ባላቸው የጋራ መዋቅርና አሰዳደር መሰረት ማቧደን<br>ተማሪዎች በቀረበው መዋቅር መሰረት የተዋቀሩ ቃላትን ማሰብ፣ መዘርዘር | **ኢ-መደበኛ ክትትል**<br>መምህሩ ክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ የትኛው ተማሪ እንደተረዳና የትኛው ተማሪ ተጨማሪ እገዛ እንደሚያስፈልገው መረዳት<br>**አቅርቦት**<br>ተማሪዎች እየገነለበተ ያለውን ግንዛቤያቸውን ለመምህራቸው ወይም ለክፍላቸው ማሳየት<br>**ማጠቃለያና ፅብረቃዎች**<br>ተማሪዎች ቆም እያሉ ፅብረቃ ማቅረብ፣ ስለሰሙት ወይም ስላነበቡት ነገር ትርጉም መስጠት፣ ከመማር ልምዳቸው በመነሳት የራሳቸውን ትርጉም መስጠት |

# ምዕራፍ አስር፡

## ስነቃል (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ስነቃልን አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ
- እራሳቸውን መግለፅ ይለማመዳሉ
- የዝነኞችን ታሪክ አንብበው ምላሽ ይሰጣሉ
- ግለታሪካቸውን ይፅፋሉ
- የስነፅሑፍ አላባዊያንን ለይተው ያውቃሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• አዳምጠው ልምዳቸውን መሰረት ያደረጉ ታሪኮችን ይናገራሉ<br>• ታሪኮችን አንብበው በቃላቸው ይተርካሉ<br>• ግለታሪክን ይፅፋሉ<br>• ቀለምን ይነጥላሉ፣<br>• ያጣምራሉ<br>• ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎችን ይለያሉ | • ማዳመጥና መናገር<br>•<br>• ማንበብ<br>•<br>• ቃላት<br>•<br>• መፃፍ<br>•<br>• ሰዋስው | ➢ አነስተኛ ቁጥር ያለው የተማሪዎች ቡድን በተናጠል ወይም ደረጃ በደረጃ የቀረበውን ቃለ ተውኔት አዳምጦ ልምምድ ማድረግ፤ በመጨረሻም ለተመልካች እየተተወነ ይቀርባል<br>➢ አነስተኛ ቁጥር ያለው የተማሪዎች ቡድን ወይም ተማሪዎች በየግላቸው የቀረበውንና በስተመጨረሻ ለተመልካች የሚቀርበውን የፅሑፍ ክፍል መለማመድ፤ ስለሆነም ገላጭና የተቀላጠፈ ንባብን ማበረታታት ይገባል<br>➢ ተማሪዎች አጠር ያለ ምንባብን ደጋግመው ማንበብ፤ ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎችን መለየት | **አቅርቦት**<br>ተማሪዎች እየጎለበተ ያለውን ግንዛቤያቸውን ለመምህራቸው ወይም ለክፍላቸው ማሳየት<br>**የርስበርስ ግምገማ** ተማሪዎች ፅሑፋዊ ተግባራትን ካጠናቀቁ በኋላ፣ የመመህርን መመሪያ መሰረት በማድረግ የፃፉትን እየተለዋወጡ የእርስ በርስ እርማት ማካሄድ። በመጨረሻም መምህሩ ወረቀቶቹን በመሰብሰብ<br>**የግል ስራ**<br>ተማሪዎች ግላዊ አስተያየትን መሰረት ያደረገ ክርክርን መነሻ አድርጎ የቀረበ ፅሑፍ ውስጥ የሚገኝን ተጠየቃዊና ተጨባጭ እውነታን ለይተው ማውጣት |